ሠንዱማ!

እውነታው፣

እደጋዎቹ እና

ሠዘዞቹ

በሳጅት አማል

መንዙማን በተመለከተ የተሰሩ የድምፅ ፋይሎችን ከሚከተለው የቴሌ ግራም ቻናል አውርደው ያድምጡ

https://t.me/Menzuma

15 አደጋ ያላቸው ሰንሾች የተዳሰሱበት

የመጅመሪያ እትም

ሸዕባን 1438 ዓ. ሂ. /

ሚያዝያ 2009 በኢትዮጵያ አቆጣጠር

ምስጋና

ከሁሉም በፊት አስቀድሜ ለባሪያዎቹ መመሪያ የሆነውን ቁርኣን ያወረደልን፣ ለአማኞች ከነፍሳቸው በላይ የሆኑትን የነብያት መደምደሚያ ነብዩ (ﷺ) የላከልንን፣ ከፍጡራኑ ሁሉ በላይ ከአርሽ በላይ ያለውን፣ እውቀቱ፣ ማየቱ፣ መስማቱ፣ ፍጡራኑን ሁሉ ያካበበውን ሃያል ብቸኛ ጌታ አንድ አምላክ የሚገባውን ያህል ስፍር ቁጥር የሌለው ምስጋና ይድረሰው።

በመቀጠል “ፍጡርን የማያመሰግን ፈጣሪን አያመሰግንም” ተብሏልና ለስኬቴ ሁሉ ሰበብ የሆኑ አካላትን ማመስገን እውዳለሁ፡፡ በተለይም “የእዝነትን ክንፍን ዝቅ አድርጉላቸው” የተባልነውን በልጅነቴ ከእኔ ምንንም ጥቅም ሳይፈልጉ በእዝነትና በጭንቀት እራሳቸውን ጥለው ያሳደጉኝን ወላጆቼን ታላቅ ባለውለታዎቼ ናቸውና ከልብ አመሰግናለሁ።

ይህንን ማስታወሻ በመገምገም እና እርማት በመስጠት ለተባበራችሁኝ ኡስታዝ ዩሱፍ አህመድ፣ ወንድሜ ኢብኑ ሙነወር እና ሌሎችም ወንድሞች የልብ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። አላህ ምንዳችሁን እጥፍ ድርብ አድርጎ ይክፈልልኝ። ወንድም ሰኢድ ሙሐመድ የመፅሀፍ ሽፋን በመስራት ለተባበርከኝ ጌታዬ አላህን በዱንያም በአኺይራም መልካም የተባለውን ነገር ላንተም ለእኛም እንዲለግሰን እማፀነዋለሁ።

በመጨረሻም በጣም ላመሰግናቸው የምወደው በቅርቤና በዙርያዬ ያሉ ቤተሰቦቼን እና የሱና ወንድም እና እህቶቼን በጠቅላላ ነው።

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

1. የሰው ልጆች እንዴት በአላህ ላይ ማጋራት ጀመሩ?..... 1
2. ነብዩ (ﷺ) ወደ ምን አይነት ሰዎች ነበር የተላኩት? 6
3. ነብያዊ መልእክት ወደ የመን..... 12
4. ነብዩ (ﷺ) ስልጣናቸው እና ደረጃቸው ምን ደረሰ ነው?. 15
5. ፈጣሪ እና ፍጡሮቹ..... 19
6. ህያው የማይሞት አላህ እና ሙታን ፍጡሮቹ..... 20
7. አላህ የሚመጣብ እና የማይመጣብ ነው።..... 22
8. እነሱ “መቃረቢያ” ሲሉት፣ አላህ ሺርክ ሲል ጠራው።..... 23
9. የአላህ ወልይ ማን ነው?..... 24
10. ረመዳንን ምንዳውን ምን ያጓድለዋል? 26
11. መንዙማ እና መውሊድ..... 28
12. ሰርጋችን..... 29
13. መንዙማ ድሮ እና ዘንድሮ..... 30
14. ሰለዋት ማውረድ ኢባዳ ነው..... 31
15. በነብዩ (ﷺ) ላይ ሰለዋት መቼ እና እንዴት እናወርድ ... 36
16. ሀሙስ ማታ!..... 37

ክፍል ሁለት 38

17. ከአላህ ጌትነት ጋር የሚጋጩ ስንኞች..... 38
18. አላህ ከፍጡሮቹ ስልጣኑን አሳልፎ የሰጠው አለን?..... 45
19. ከአላህ አምላክነት ጋር የሚጋጩ ስንኞች..... 48

20. በጭንቀት ጊዜ ማንን ይለምናሉ? 65
21. ምልጃን ከማን እንጠይቅ? 68
22. ከአላህ ውጭ መመኪያ አለን? 68
23. ስንታመም የሚያድነን ማን ነው? 70
24. በአላህ እና መልከተኛው ላይ መዋሸት 71
25. ከኢልመል ገይብ ጋር የሚጋጩ ስንኞች 73
26. ውሸቶች እና ተረተረቶች 77
27. ጫት እና መንዙማ 79
28. ሌሎች 81
29. “ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል” 83
30. ነብዩን (ﷺ) ማሞገስ ለንግድ መጠቀም 84
31. ማጠቃለያ 86

<u>መግቢያ</u>

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርሕሩሕ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው። እናመሰግነዋለን፣ እገዛን እንጠይቀዋለን፣ ምህረትንም እንጠይቀዋለን። ከነፍሳችን ተንኮል፣ ከመጥፎ ስራዎቻችንም በአላህ እንጠበቃለን። አላህ የመራውን ሰው የሚያጠመው የለም፣ ያጠመመውን የሚመራው የለም።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٢ ﴾ آل عمران: ١٠٢

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት። እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጅ አትሙቱ።" [አሊ ዒምራን: 102]

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفۡسٖ وَٰحِدَةٖ وَخَلَقَ مِنۡهَا زَوۡجَهَا وَبَثَّ مِنۡهُمَا رِجَالٗا كَثِيرٗا وَنِسَآءٗۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِي تَسَآءَلُونَ بِهِۦ وَٱلۡأَرۡحَامَۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَيۡكُمۡ رَقِيبٗا ١ ﴾ النساء: ١

"እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁን ከእርሰዋም መቀናጀዋን (ሐዋን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ። ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ። አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና።" [አን-ኒሳእ: ١]

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَقُولُواْ قَوۡلٗا سَدِيدٗا ٧٠ يُصۡلِحۡ لَكُمۡ أَعۡمَٰلَكُمۡ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۗ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ فَقَدۡ فَازَ فَوۡزًا عَظِيمًا ٧١ ﴾ الأحزاب: ٧٠ – ٧١

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ። ሥራዎቻችሁን ለእናንተ ያሳምርላችኋልና። ሃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምርላችኋል። አላህንና

መልክተኛውን የሚታዘዝም ሰው በእርግጥ ታላቅን እድል አገኘ።" [አል አሕዛብ፡ 70 - 71]

በመቀጠልም ከንግግር ሁሉ በላጭ የአላህ ንግግር ነው። ምርጥ የሚባለው መመሪያ የሙሐመድ ﷺ መመርያ ነው። ከነገሮች ሁሉ የከፋው (በዲን ላይ) ፈጠራ ነው። ፈጠራ የተባለ ሁሉ ቢድዐ ነው። ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነው። ጥመት ሁሉ የእሳት ነው።

ይህች አጠር ያለች መፅሐፍ በአላህ ፍቃድ አብዛኛው ሰው ዘንድ የሚደመጠው **"መንዙማ"** ውስጥ የተገኙትን የክህደት፣ በአላህ ላይ ማጋራት (ሺርክ)፣ ከአላህ ጌትነት፣ አምላክነት፣ ስምና መገለጫዎች ጋር የሚጋጩ፣ በአላህ ላይ እና በሸሪዓተል ኢስላም ላይ የተዋሹ ቅጥፈቶችን የያዙ ስንኞችን እና ሌሎችንም በማስረጃ መልስ የምሰጥባቸው እና ማህበረሰቡ ከዚህ አስከፊ አደጋ እራሱን እና ቤተሰቡን ይጠብቅ ዘንድ አቅጣጫ የምጠቁምባት ናት። በአላህ ፍቃድ እና እገዛ ይህችን አጠር ያለች መልእክት ሳዘጋጅ የተጠቀምኩት ቋንቋ እና መልእክት በተቻለ መጠን ለህዝበ ሙስሊሙ የሚገባ እና ቀላል ለማድረግ ጥሬያለሁ።

ከምንም በፊት እምነትን ማስተካከል ይቀደማል። እምነት ደግሞ በአላህ አንድነትና ብቸኝነት በማመን እና ከእርሱ ውጭ በሚመለኩት በጠቅላላ በመካድ ቢሆን እንጂ ሊስተካከል አይችልም። አላህ እንዲህ ይላል

﴿ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ

لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ٢٥٦ ﴾ البقرة: ٢٥٦

<u>በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን</u> ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ። አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።

ማስረጃዎቼን ከስህተት ከፀዳው የአላህ ቃል ቁርኣን፣ የአላህ ጥበቃ ከማይለያቸው መልክተኛው ﷺ ሱና፣ ከመልካም ቀደምቶች እና የነሱን መልካም አርዓያ የተከተሉትን አስተምህሮት ለማድረግ መርጫለሁ። ምክንያቱም ከጥመት የመዳኛው ብቸኛው መንገድ ይህ ስለሆነ። የአላህ ባርያዎች ሆይ! አላህ ዲንን እንዲያስገነዝበን እየለመንኩ፣ የሰው ስራ ከስህተት አይጠራምና መፅሐፉን አስመልክቶ ስህተት ካገኛችሁ በሚከተለው የኢሜል አድራሻዮ ብትጠቁሙኝ ደስተኛ ነኝ።

sadatkemal@gmail.com

ክፍል አንድ

በአላህ ፈቃድ ይህችን አጭር ማስታወሻ በውስጣቸው አርእስቶች የያዙ ሁለት ዋና ክፍሎች አድርጌ አዘጋጅቻታለሁ። በክፍል አንድ መግቢያ እና መንደርደሪያ፣ የተፈጠርንለትን አላማ (ተውሒድን)፣ እዚህ ምድር ላይ የሰው ልጆች እንዴት በአላህ ላይ ማጋራት እንደጀመሩ፣ በፍጡራን እና በፈጣሪ አላህ መሃል ያለው ታላቅ ልዩነት፣ አምልኮ ለማን እንደሚገባው እና ከማንስ ላይ መግፈፍ (መንፈግ) እንዳለብን፣ ነብያት በምን መልእክት እንደተላኩ፣ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ለምን አይነት ሰዎች እንደተላኩ፣ የሺርክን አስከፊነት በአጭሩ የተቃኘበት ክፍል ነው።

ክፍል አንድ ላይ የተዘረዘሩት አንኳር ነጥቦች ክፍል ሁለት ላይ ያሉት የሺርክ፣ የክህደት ስንኞች ምን ያህል አደገኛ እንደሆኑ ለሙስሊሙ ኡማ ማስገንዘቢያ የሚሰጡ መንደርደሪያ ናቸው። አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) ሀቅን በሃቅነቱ እንዲያሳየን የምንቀበለውም እንዲያደርገን፣ ባጢልን በባጢልነቱ እንዲያሳየን የምንርቀውም እንዲያደርገን ጌታችንን አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላ) እለምነዋለሁ።

1. የሰው ልጆች እንዴት በአላህ ላይ ማጋራት ጀመሩ?

ወንጀልን ወንጀል ይበልጠዋል። ለምሳሌ ዝሙት ከታላላቅ ወንጀሎች ውስጥ ነው። አንድ ሰው ከሌላ ሴት ጋር ዝሙት መስራቱ እና ከእናቱ ጋር ዝሙት መስራቱ በጣም ልዩነት አለው። እናቱን መገናኘቱ ይከፋል። ልክ እንደዚሁ የሰው ልጅም ይሁን ኢጋንንት የተፈጠሩበት ዋና አላማ አላህን በብቸኝነት ለመገዛት ነው። ይህንን የተፈጠሩለትን ታላቅ አላማ ተቃርነው በእርሱ (በአላህ) ላይ ቢያጋሩ ታላቁን በደል ሰርተዋል። የነብያት ሁሉ መደምደሚያ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከወንጀሎች ሁሉ ታላቁ እና የከፋው የትኛው

እንደሆነ ሲጠየቁ **“እሱ አላህ ፈጥሮህ ሲያበቃ በእርሱ (አላህ) ላይ ብጤን (ሸሪካን) ልታደርግለት ነው”** ብለዋል። [ቡኻሪ፡ 4477፣ ሙስሊም፡ 86]

አላህ ዘንድ ታላቁ ወንጀል ምን እንደሆነ በሰፊው ሊዳሰስ ይገባል። አላህ በእያንዳንዱ ህዝብ መሃል መልክተኞቹን መጽሀፍ አስይዞ የሚልክበት ዋና መልእክት በምን እንደሚደፈርስ ሊታወቅ ይገባዋል። በምን ምክንያት የሰው ልጆች የተፈጠሩለትን አላማ ተቃርነው፣ የአባታችንን አደም ንጹህ የተውሒድ መንገድ ተቃርነው፣ በብቸኛው ፈጣሪያችን እና አምላካችን አላህ ላይ ፍጡራንን አማልክት አድርገው ያዙ?

ከሰው ልጆች ሁሉ አባት ነብዩላህ አደም (ዐለይሂ-ስሰላም) እስከ መጀመርያዉ መልክተኛ ኑሕ (ዐለይሂ-ስሰላም) ድረስ አስር ክፍለ ዘመን ነበር። በዚህ ወቅት የሰው ልጆች ሁሉ በአንድ ሃይማኖት በእስልምና ውስጥ ነበሩ። ችግሩ የተፈጠረው አንድነቱ የፈረሰው ኑሕ (ዐለይሂ-ስሰላም) የተላኩባቸው ሰዎች በደጋጎች ላይ ድንበር አልፈው የባእድ አምልኮት ላይ ሲወድቁ ጊዜ ነው።

በዚህም የተነሳ አዛኙ አላህ እነዚያ ህዝቦች የተፈጠሩለትን አላማ ያውቁ ዘንድ የመጀመርያውን መልክተኛ ኑሕን (ዐለይሂ-ስሰላም) ወደ ተውሒድ እንዲጠሯቸው ላካቸው። ኑሕም (ዐለይሂ-ስሰላም) ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አመት የተውሒድ ጥሪ እንዲቀበሉ ይህን የተቀበለም ብስራት እንዳለው፣ ከአላህ ውጭ ላለ አካል የሚፈፅሙትን አምልኮ እንዲርቁ ይህን ካላደረጉ ከባድ አደጋ እንደሚያጋጥማቸው በማስጠንቀቅ ተጣሩ።

ልብ እንበል የሰይጣን ወጥመዱ ከባድ ነው። በአንድ ሃይማኖት ላይ የነበሩትን ህዝቦች በታተናቸው። አብዛኛዎቹ የመጀመርያውን መልክተኛ ኑሕ ጥሪ አንቀበልም ብለው ለጥፋት ተዳረጉ።

አላህ (ሱብሓነሁ ወተዓላም) የነዚህን አጋሪያን (መጥፎ ፍጡሮች) መጨረሻ ከባድ የሆነ ቅጣት ቀጥታቸው ከባድ አደጋንም ተከናነቡ። ጥፋታቸው ከባድ ስለነበር በአላህ ትእዛዝ ሰማይ የያዙትን ውሃ ለቀቀች፣ ምድር የያዙትን ውሃ ተፋች፣ ተራራ የሚያካክሉ ማእበሎች ተነስተው እነዚህ ሁሉ አመጸኞች ውርደትን ቀመሱ። በሁለት አገርም ተዋረዱ።

በሌላ ጎኑ ድል ለአላህ፣ ለመልክተኛው እና ለአማኞች ነውና አላህ ነብየላህ ኑሕን (ዐለይሂ-ስሰላም) በጣም ጥቂት ከሆኑ ተከታዮቻቸው ጋር ከእንስሳ ጥንድ ጥንድ በመሆን እዛች መርከብ ላይ ተጭነው በዚህ ምድራዊ ህይወት ከመስመጥ ተጠበቁ። በአላህ ፍቃድ የሚቀጥለው አለም ላይ ካለው አሳማሚ ቅጣት ተጠብቀው የሰላም አገር የሆነችው ጀነት ውስጥ ይገባሉ። ይህ ከባድ የሆነ የሰይጣን ወጥመድ ትኩረት ይሻልና እስቲ ትንሽ ጠለቅ ብለን እንየው፡-

የሰው ልጆች ከአንድነታቸው በኋላ የተበታተኑት በአላህ ላይ በማጋራታቸው ነው። አላህ ይህን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡-

﴿ كَانَ ٱلنَّاسُ أُمَّةً وَٰحِدَةً فَبَعَثَ ٱللَّهُ ٱلنَّبِيِّـۧنَ مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ وَأَنزَلَ مَعَهُمُ ٱلْكِتَٰبَ بِٱلْحَقِّ لِيَحْكُمَ بَيْنَ ٱلنَّاسِ فِيمَا ٱخْتَلَفُوا۟ فِيهِ ۚ وَمَا ٱخْتَلَفَ فِيهِ إِلَّا ٱلَّذِينَ أُوتُوهُ مِنۢ بَعْدِ مَا جَآءَتْهُمُ ٱلْبَيِّنَٰتُ بَغْيًۢا بَيْنَهُمْ ۖ فَهَدَى ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لِمَا ٱخْتَلَفُوا۟ فِيهِ مِنَ ٱلْحَقِّ بِإِذْنِهِۦ ۗ وَٱللَّهُ يَهْدِى مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٢١٣﴾ ﴾ البقرة: ٢١٣

<u>“ሰዎቹ ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ፤ (ተለያዩ)። አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርጎ ላከ። ከእነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎቹ መካከል በዚያ በርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ።</u> በእርሱም (በሃይማኖት) ግልጽ አሰረጂዎች ከመጡላቸው በኋላ በመካከላቸው ለሆነው ምቀኝነት እነዚያው የተሰጡት እንጂ

አልተለያዩበትም። አላህም እነዚያን ያመኑትን ሰዎች ለእዚያ ከእውነት በርሱ ለተለያዩበት በፍቃዱ መራቸው። አላህም የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል።"
[አል-በቀራህ፡ 213]

<u>ከአንድነት በኋላ የተለያዩት በሺርክ ነው</u>። እነዚያ **<u>ኑሕ የተላኩባቸው ህዝቦች የፈፀሙት ደግሞ ይህን የበደሎች ሁሉ ታላቅ በደል የሆነውን ሺርክ ነው</u>**። ወደ ሺርክ ደግሞ የወሰዳቸው ከአላህ እዝነት የተባረረው ሸይጧን እነሱን ቢድዐ በማሰራት ነው።

﴿ وَقَالُواْ لَا تَذَرُنَّ ءَالِهَتَكُمۡ وَلَا تَذَرُنَّ وَدّٗا وَلَا سُوَاعٗا وَلَا يَغُوثَ وَيَعُوقَ وَنَسۡرٗا ﴿٢٣﴾ ﴾ نوح: ٢٣.

<u>"አሉም፦ አምላኮቻችሁን አትተዉ</u>። ወድንም፣ ሱዋዕንም፣ የጉሥንም፣ የዑቅንም ነሰርንም አትተው።" [ኑህ: 23]

እነዚህ አምስት **<u>"አማልክት"</u>** ተብለው የተጠሩ ግለሰቦች እነማን ናቸው? እነዚህ ግለሰቦች በታላቁ ሶሐባ ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ (ረድየላሁ ዐንሁማ) አንደበት **"ሷሊሆች (መልካም የአላህ ባርያዎች)"** መሆናቸው የተመሰከረላቸው ናቸው። እነዚህ አምስት ሷሊሆች ሲሞቱ ሸይጧን ለህዝቦቻቸው አዛኝ መስሎ **<u>"ይቀማመጡ የነበረበት ቦታ ላይ ሃውልት ብታደርጉላቸው"</u>** አላቸው። እነሱም እሺ ብለው ተቀበሉት።

ልብ በሉ በዚህ ግዜ አማልክት ተብለውም አልተጠሩም። ሸይጧን ግቡን ለማሳካት ሩቅ ነው የሚያልመው። ከዚያም ይህ ትውልድ አልፎ ሌላ ትውልድ ሲተካና፣ እውቀትም ሲጠፋ **<u>"አባቶቻችሁ ዝናብ ሲቸግራቸው እነሱን ነበር የሚጠይቁት"</u>** ብሎ ታላቁ ወጥመዱ ውስጥ ከተታቸው። ከዚያም ተቀበሉት። በዚህም ምክንያት አላህ ለምድር ህዝቦች የመጀመርያውን መልክተኛ ኑሕን (ዐለይሂ-ስሰላም) ላከ።

ታላቁ መልክተኛ ኑሕ በቀንም በማታም፣ በድብቅም በግልፅም፣ በተለያየ ስልት ህዝባቸውን **“ህዝቦቼ ሆይ! አላህን በብቸኝነት አምልኩት ከእርሱ ውጭ በሃቅ የሚመለክ የለምና”** በማለት 950 አመት ተጣሩ። በጣም ጥቂቶች እንጂ ለጥሪያቸው መልካምን መልስ አልሰጡም።

ነብየላህ ኑሕ 950 አመት ህዝቦቹን በቀንም በማታም በድብቅም በግልጽም ካስጠነቀቁ በኋላ የህዝቦቹ መልስ የሚከተለው ነበር

﴿ وَقَالُواْ لَا تَذَرُنَّ ءَالِهَتَكُمۡ وَلَا تَذَرُنَّ وَدّٗا وَلَا سُوَاعٗا وَلَا يَغُوثَ وَيَعُوقَ وَنَسۡرٗا ٢٣ ﴾ نوح: ٢٣

አሉም “አምላኮቻችሁን አትተዉ። ወድንም፣ ሱዋዕንም፣ የጉሥንም፣ የዑቅንም ነስርንም አትተው።” [ኑሕ፡ 23]

ይህን ጉድ ተመልከቱ። ብቸኛው ፈጣሪ፣ የሁሉ ቀላቢ፣ የፍጡራኑ ሁሉ መጠጊያ፣ ብቸኛ አምላክ አላህ በድንበር አላፊዎች እና የተፈጠሩለትን አላማ በረሱ ህዝቦች **“አማልክት”** በተባሉ ፍጡራን ተተካ። የአላህ መብት ተቆርሶ የተሰጣቸው አምስቱ ሰዎች **ወድ፣ ሱዋዕ፣ የጉሥ፣ የዑቅ** እና **ነስር** በመባል ይታወቃሉ።

አርእስቱን ስናጠቃልል የአላህ ባሪያዎች ሆይ! ፍጡራንን ማንም ይሁን ማን መላኢካም ይሁን ነብይ አላህ ከሰጠው ደረጃ በላይ ከፍ ማድረግ አላህ ለጠላው ሺርክ ይዳርጋል። ፍጡራን ፍጡር ናቸው። ምንም ይሁኑ ማን ጉዳትን ከራሳቸው ላይ መከላከል አይችሉም። መጥቀምም መጉዳትም የሚችለው የፍጡራን ሁሉ መጠጊያ የሆነው አንድ አላህ ብቻ ነው ። እዚህ መጸሀፍ ላይ የምናየው የሺርክ ስንኞች አብዛኛዎቹ በነብዩ (ﷺ)፣ በወሊዮች እና ወልይ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሰዎች ላይ ድንበር በማለፍ የተፈፀሙ ናቸው።

2. ነብዩ (ﷺ) ወደ ምን አይነት ሰዎች ነበር የተላኩት?

ሁሉም ነብይ ወደ የህዝቡ ሲላክ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ግን ባጠቃላይ ለአለማት እዝነት ተደርገው ነው የተላኩት።

ነብዩ (ﷺ) ለምን አይነት ህዝቦች እንደተላኩ ማወቃችን ወሳኝ ነጥብ ነው። ምክንያቱም ዛሬ አብዛኞች የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ተከታዮች ነን እያሉ በተግባር ግን ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተዋጓቸውን የነ አቡ ጀህልን መንገድ ሲከተሉ ይታያሉና።

ከላይ **"የሰው ልጆች እንዴት አላህ ላይ ማጋራት ጀመሩ"** የሚለውን ዋና ነጥብ አይተን ነበር። በነጥቡ ላይ የሺርክን አደገኝነት እና የመጀመርያው ሺርክ በምን ምክንያት እና በማን ሰባኪነት እንደተፈጸመ አይተናል። አሁን ደግሞ ነብዩ (ﷺ) ለምን አይነት ሰዎች ተልከው እንደነበር ማወቃችን የሺርክ አደገኝነት አውቀን በአላህ ፍቃድ ከባድ ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዘናል፣ ይረዳናል።

ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተላኩባቸው ህዝቦች ሐጅ የሚፈጽሙ፣ ምጽዋት የሚለግሱ እና ሌሎችንም ስራዎች የሚተገብሩ ነበሩ። ግና ይህ ተግባራቸው እስልምና ውስጥ አላስገባቸውም። ምክንያቱም አምልኮ ሲፈጽሙ በአላህ ላይ ኢጋርን ይጨምሩ ነበርና። በዚህም ነው ነብዩ (ﷺ) የተጋደሏቸው።

ነብዩ (ﷺ) የተላኩባቸው ህዝቦች አላህ ብቸኛው የሁሉ ፈጣሪ፣ ሁሉን አስተናባሪ፣ ሲሳይ ሰጪ መሆኑን ያምኑ ነበር። ለዚህም የሚከተሉት የቁርአን አንቀጾች ግለጽ ማስረጃ ናቸው።

﴿ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَسَخَّرَ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۖ فَأَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ ﴿٦١﴾ ﴾ العنكبوت: ٦١

<u>ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው “በእርግጥ አላህ ነው” ይሉሃል። ታድያ እንዴት ይመለሳሉ?!</u>

﴿ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّن نَّزَّلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَحْيَا بِهِ ٱلْأَرْضَ مِنۢ بَعْدِ مَوْتِهَا لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۚ قُلِ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ ﴿٦٣﴾ ﴾ العنكبوت: ٦٣

ከሰማይም ውሃን ያወረደና በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ያደረጋት ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው “አላህ ነው” ይሉሃል። “ምስጋና ለአላህ ነው” በላቸው። ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።

﴿ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَهُمْ لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۖ فَأَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ ﴿٨٧﴾ ﴾ الزخرف: ٨٧

ማን እንደፈጠራቸውም ብትጠይቃቸው “በእርግጥ አላህ ነው” ይላሉ። ታዲያ (ከእምነት) ወዴት ይዞራሉ?

﴿ قُل لِّمَنِ ٱلْأَرْضُ وَمَن فِيهَآ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿٨٤﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِ ۚ قُلْ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٨٥﴾ قُلْ مَن رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ ٱلسَّبْعِ وَرَبُّ ٱلْعَرْشِ ٱلْعَظِيمِ ﴿٨٦﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِ ۚ قُلْ أَفَلَا تَتَّقُونَ ﴿٨٧﴾ قُلْ مَنۢ بِيَدِهِۦ مَلَكُوتُ كُلِّ شَىْءٍ وَهُوَ يُجِيرُ وَلَا يُجَارُ عَلَيْهِ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿٨٨﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِ ۚ قُلْ فَأَنَّىٰ تُسْحَرُونَ ﴿٨٩﴾ ﴾ المؤمنون: ٨٤ - ٨٩

"ምድርና በውስጥዋ ያለው ሁሉ የማን ነው? የምታውቁ ብትሆኑ (ንገሩኝ)" በላቸው። "በእርግጥ የአላህ ነው" ይሉሃል። "ታዲያ አትገሰጹምን?" በላቸው። "የሰባቱ ሰማያት ጌታና የታላቁ ዐርሽ ጌታ ማን ነው?" በላቸው። "በእርግጥ አላህ ነው" ይሉሃል። "እንግዲያ አትፈሩትምን?" በላቸው። የነገሩ ሁሉ ግዛት በእጁ የሆነ እርሱ የሚጠብቅ በእርሱ ላይ የማይጠበቅ ማን ነው? የምታውቁ እንደሆናችሁ (መልሱልኝ)" በላቸው። "በእርግጥ አላህ ነው" ይሉሃል። "ታዲያ እንዴት ትታለላላችሁ?" በላቸው። [አልሙእሚኑን፡ 84-89]

ልብ በሉ የአላህ ባሪያዎች እነዚህ አጋሪያን የአላህን ጌትነት ማመናቸው ወደ ነብያት ሁሉ ሀይማኖት ኢስላም አላስገባቸውም። ይህም የሆነው አምልኮን በጠቅላላ ለአንድ አላህ ብቻ ስላልፈጸሙ እና አላህንም ከእርሱ ውጭ ያሉትንም ያመልኩ ስለ ነበር ነው።

ከአጋሪያን ተግባር ውስጥ የሚጠቃለለው ለእርሱ ብቻ የሚገባውን አምልኮ በእርሱ ላይ ሌላን ምንንም ማድረግ የማይችሉ፣ የማይጠቅሙ፣ የማይጎዱ፣ ጥቅምን ለራሳቸው ማምጣት የማይችሉ፣ እራሳቸውን ከጉዳት መከላከል የማይችሉትን ፍጡራን መገዛታቸው ነው። ለዚህም ማስረጃው የሚከተለው አንቀጽ ነው።

﴿ وَمَا يُؤۡمِنُ أَكۡثَرُهُم بِٱللَّهِ إِلَّا وَهُم مُّشۡرِكُونَ ١٠٦ ﴾ يوسف: ١٠٦

"አብዛኞቻቸውም፤ እነሱ (በአምልኮ የተውሒድ ክፍል) አጋሪዎች ሆነው እንጂ በአላህ (ጌትነት) አያምኑም።" [ዩሱፍ፡ 106]

የዚህ አንቀጽ ትንታኔ እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ አጋሪዎች የአላህን ጌትነት፣ ፈጣሪነት፣ ሲሳይን ለጋሽነት እና አስተናባሪነት ያጸድቁ እንደነበር ነው። ግና አላህን

በጌትነቱ እንደነጠሉት በአምላክነቱ አልነጠሉትም። ለብቸኛው ፈጣሪ የሚገባውን አምልኮ ከእርሱ ውጭ ለሆኑ ፉጡራን በማካፈል ነበር አምልኮ የሚፈጽሙት። የአላህን ጌትነት አምነው ተቀብለው በአምላክነቱ ላይ በማጋራታቸው ደግሞ **“አማኝ” አላስባላቸውም**።

ለዚህች አንቀጽ ቁርኣን ተርጓሚ የሆኑትን ሶሐባዎች እና ታቢዒዮች የሰጡትን ትርጉም እንመልከት፡-

ኢብን ዐባስ (ረድየላሁ ዐንሁማ) እንዲህ ይላሉ፡- **“ከኢማናቸው ውስጥ ሰማይን ማን ፈጠረው? ምድርን ማን ፈጠረው? ተራራን ማን ፈጠረው? (ተብለው) ከተጠየቁ አላህ ብለው ይመልሳሉ፣ እነሱ ግን አጋሪ ናቸው።”**

ኢክሪማ ደግሞ እንዲህ አሉ፡ **“ማን ፈጠራችሁ፣ ሰማያትና ምድርን ማን ፈጠረ ብለህ ትጠይቃቸዋለህ? የእነሱም መልስ አላህ ይሆናል። ይህም ነው በአላህ ላይ ያላቸው እምነት። ከእርሱ (ከአላህ) ውጭ ግን ያመልካሉ።”**

ሙጃሂድ ደግሞ እንዲህ ይላሉ፡- **“እምነታቸው አላህ ፈጠረን፣ ሲሳይ ይለግሰናል፣ ይገድለናል ብለው መናገራቸው ነው። ይህ ነው እምነታቸው ከእርሱ ውጭ እያመለኩ.....”**

ዐብዱረሕማን ኢብን ዘይድ ኢብን አስለም ደግሞ **“በአላህ ላይ አንድም የሚያጋራ የለም አላህ ጌታው፣ አላህ ፈጣሪው እና ሲሳይ ሰጪው መሆኑን እያወቀ እና እያመነ ቢሆን እንጂ።** ኢብራሂም ምን እንዳሉ አታይምን?

﴿ قَالَ أَفَرَءَيْتُم مَّا كُنتُمْ تَعْبُدُونَ ﴿٧٥﴾ أَنتُمْ وَءَابَآؤُكُمُ ٱلْأَقْدَمُونَ ﴿٧٦﴾ فَإِنَّهُمْ عَدُوٌّ لِّىٓ إِلَّا رَبَّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٧٧﴾ ﴾ الشعراء: ٧٥ - ٧٧

<u>ትግገዙት የነበራቸሁትን አስተዋላችሁን? እናንተም የቀድሞዎቹ አባቶቻችሁም (የተግገዛችሁትን)። እነሱም (ጣዖቶቹ) ለእኔ ጠላቶች ናቸው። ግን የዓለማት ጌታ ሲቀር (እርሱ ወዳጄ ነው)። (እርሱ) ያ የፈጠረኝ ነው። እርሱም ይመራኛል።</u>" [አሸዑራእ፡ 75-77]

እንግዲህ ኢብራሂም ዳዕዋ ያደረጉላቸው ሰዎች አላህን እና ከእርሱ ውጭ ያሉትን ያመልኩ ነበር። ኢብራሂም **"<u>እነሱም (ጣዖቶቹ) ለእኔ ጠላቶች ናቸው። ግን የዓለማት ጌታ ሲቀር (እርሱ ወዳጄ ነው)</u>"** አሉ።

ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተላኩባቸው ህዝቦች ነብዩ ዒሳን (ዐለይሂ-ስሰላም)፣ እናታቸው መርየምን፣ ዑዘይርን፣ ላትን[1]፣ ኡዛን፣ መናትን፣ ሺዕራን[2]፣ ፀሀይ እና ጨረቃን፣ መላእክትን፣ ጂኖችን፣ ዛፎችን፣ ወዘተ በመጣራት በአላህ ላይ ያጋሩ ነበር፡

[1] ይህ ግለሰብ ለሀጅ የሚመጡ ሰዎችን በሶ በማበስበስ ይመግብ እንደነበር ይነገርለታል።

[2] ከብዙ ኮከቦች አንዷ ሺዕራ ብለው ለይተው የሚያመልኳት ነበረች። አላህም እሷን እንዳያመልኩ እና የሷ ጌታ መሆኑን እንዲህ ሲል ጠቆማቸው

﴿ وَأَنَّهُۥ هُوَ رَبُّ ٱلشِّعْرَىٰ ﴿٤٩﴾ ﴾ النجم: ٤٩

"<u>እነሆ እርሱም የሺዕራ ጌታ ነው።</u>" አል ነጅም 49

ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከአላህ ውጭ የሚመለኩትን በጠቅላላ አንዱን ከአንዱ ሳይለዩ መቃወማቸው እና አምልኮን ለብቸኛው አላህ ብቻ ይሁን ማለታቸው የሺርክን አስከፊነት እና ከባድነት የሚያሳይ ነው። ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ ያየ ከአላህ ውጭ ያለን ማንንም ይሁን ማን ማምለክ ሺርክ እንደሆነ ይገነዘባል። **ነብዩ (ﷺ) ሁሉንም ከአላህ ውጭ የሚፈጸም አምልኮ መቃወማቸው ፀሀይ እና ጨረቃን በሚያመልከው ሰው እና ዒሳን በሚያመልከው ሰው መሃል ልዩነት እንደሌለ እና ሁለቱም አጋሪያን እንደሆኑ ያስገነዝበናል።** ይሄ ሺርክ ማለት ምን እንደሆነ ሰፋ ባለ ሁኔታ እንድንረዳ ያደርገናል።

አንድ ሙስሊም ነበዩላህ ኢሳ ዐለይሂ-ስሰላም አይመለኩ ሲል እኝህን ውድ የአላህ ነብይ ጠልቶ አይደለም። ነገር ግን የብቸኛው ፈጣሪ፣ የአንድ አምላክ አላህ ብቸኛ መብት፣ ከፍጡራን ለማንም ሊሰጥ ስለማይገባ ነው። ልክ እንደዚሁ በአላህ ላይ ማንም ከተጋራበት ትክክለኛ አምልኮ ተብሎም አይጠራም። የሚመለከው እንጨት፣ ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ጂን፣ ሙት፣ በህይወት ያለ፣ አላህ ዘንድ እንደ መልአክ እና ነብይ ታላቅ ቦታ ያለው ቢሆንም ጉዳዩን ከሺርክነት አያወጣውም። አምልኮ የአንድ አላህ ሐቅ ነውና። ይህንንም አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَنَّ ٱلۡمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدۡعُواْ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدٗا ١٨ ﴾ الجن: ١٨

"እነሆ መሰጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውሰጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ።"
[አልጂን፡ 18]

ይሄ አንቀጽ አምልኮ ለአላህ ብቻና ብቻ እንደሚገባ ከሚያመለክቱ ዋና ዋና አንቀጾቸ ውስጥ አንዱ ነው። አንቀጹ ላይ መስጂድ ለተባለው ከተሰጡ ትርጉሞች ውስጥ በጥቂቱ

1) ሰባቱ የሱጁድ አካላት (ፊት፣ ሁለቱ እጆች፣ ሁለቱ ጉልበቶች እና ሁለቱ እግሮች) ማለት ተፈልጎበት ነው ተብሏል።

2) በአላህ ቤቶች ወይንም መስጂዶች ሺርክ አትፈፅሙባቸው።

ልብ ሊባል የሚገባው የአላህ መልክተኛ (ﷺ) ሺርክን በሁሉም አይነቱ ነው የተዋጉት። ወንድሜ ሙሐመድ አሕመድ ኢብን ሙነወር **"<u>የሺርክ ቡላና ዳልቻ የለውም</u>"** ብሏል። አዎን እውነቱን ነው።

በብቸኛው ፈጣሪ አላህ ላይ ጂብሪልም፣ ሚካኢልም፣ ኢሳም፣ መርየምንም፣ ነብዩ ሙሐመድም፣ አልይም፣ ሁሴንም፣ ፀሀይም፣ ጨረቃም፣ ጂንም፣ የሚታይም የማይታይም፣ ባጠቃላይ ፍጡራን ቢመለክ ሺርክ ነው። ማንኛውንም ፍጡር ማምለክ ሺርክ ነው።

ለአላህ ብቻ የሚገባውን አምልኮ ከአላህ ውጭ ላለ ለማንም አካል የሰጠ አጋሪ ነው። በአላህ ላይ እያጋሩ የተሰራ ስራ ተቀባይነት የለውም። ጭራሽ ሌሎች በአላህ ላይ ሳይጋሩ የተሰሩ ስራዎችን ሁሉ ድምጥማጣቸውን ያጠፋል። በአላህ ላይ እያጋሩ የሞተ ሰው መኖርያው ጀሃነም ነው። ለበደለኞች ምንም ረዳት የላቸውም። አላህ ከሺርክ ይጠብቀን።

3. <u>ነብያዊ መልእክት ወደ የመን</u>

ነብዩ (ﷺ) ባልደረባዎቻቸውን መልእክትን አስይዘው ወደ ተለያዩ ህዝቦች ይልኳቸው ነበር። ከላኳቸው ባልደረባዎች ውስጥ የዚህ ኡማ ሃላል እና ሀራሙን የሚያውቅ የተባለላቸው ሙዓዝ ኢብን ጀበል (ረድየላሁ አንሁ) አንዱ ናቸው። የአላህ መልክተኛ (ﷺ) ሙአዝን ወደ የመን ሲልኳቸው እንዲህ ነበር ያሏቸው፡-

"إِنَّكَ تَقْدَمُ عَلَى قَوْمٍ مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ فَلْيَكُنْ أَوَّلَ مَا تَدْعُوهُمْ إِلَى أَنْ يُوَحِّدُوا اللَّهَ تَعَالَى فَإِذَا عَرَفُوا ذَلِكَ فَأَخْبِرْهُمْ أَنَّ اللَّهَ فَرَضَ عَلَيْهِمْ خَمْسَ صَلَوَاتٍ فِي يَوْمِهِمْ وَلَيْلَتِهِمْ، فَإِذَا صَلُّوا فَأَخْبِرْهُمْ أَنَّ اللَّهَ افْتَرَضَ عَلَيْهِمْ زَكَاةً فِي أَمْوَالِهِمْ تُؤْخَذُ مِنْ غَنِيِّهِمْ فَتُرَدُّ عَلَى فَقِيرِهِمْ، ... ".

"አንተ ከመፅሐፉ ባለቤቶች የሆኑ ሰዎች ዘንድ ትሄዳለህ። የመጀመሪያ የምትጠራቸው አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ ነው። ይህንን ካወቁ በሌሊትና በቀናቸው ውሰጥ አላህ አምስት ሶላቶችን እንደደነገባቸው ንገራቸው። ከሰገዱ ከሃብታሞቻቸው ላይ ተወሰዶ ለድሆቻቸው የሚሰጥ ሰደቃ (ዘካን) አላህ ግዴታ እንዳደረገባቸው ንገራቸው።..." [ቡኻሪ፡ 1458፣ ሙስሊም፡ 19]

ከዚህ ሐዲሥ እንደምንረዳው አህለል ኪታቦች ተውራት እና ኢንጂል የወረደላቸው "የመጸሀፍቱ ባለቤቶች" ተብለው ቢጠሩም የተውራት እና የኢንጂል ዋና መልክት የሆነውን ተውሒድ በሺርክ እና በኩፍር ስለ ለወጡት አላህ መልክተኛውን (ﷺ) ልኮ ወደ ሁሉ ነብያት መንገድ እንዲመለሱ ጥሪ እንዲደረግላቸው አዘዘ። ለዚያም ነው ነብዩ (ﷺ) ሙዓዝን ወደ መጸሀፍቱ ባለቤቶች የላኩት።

ዛሬም አለም ላይ አላህ ካዘነላቸው ውጭ አብዛኛው ሰው እራሱን ሙስሊም ነኝ እያለም፣ ቁርአን እና ሀዲስ እንደሚከተል እያስተጋባም፣ የነብዩ (ﷺ) ተከታይ ነኝ እያለም፣ ቁርአን እና ሀዲስ የእስልምና ምንጮች እንደሆኑ እያመነም፣ ትክክለኛውን የነብያት መንገድ ተቃርኖ የሺርክ አምልኮ ውስጥ ገብቷል።

በዚህ ሀዲስ መሰረት ከምንም ነገር በፊት እምነትን የማስተካከል ነገር ይቀደማል። ወደ አላህ መንገድ እንጣራለን የሚሉ ሁላ ነብዩ (ﷺ) ለሙኣዝ የሰጡትን ትእዛዝ፣ ሙአዝ በተግባር ያሳዩትን መንገድ ተቀብሎ ወደ ተውሒድ ጥሪ ከምንም በፊት ሊያደርግ

ይገባዋል። እምነቱ ያልተስተካከለ ሰው የሰራውን ያህል ቢሰራ አላህ ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

ለዚህም ማስረጃው ኢማሙ ሙስሊም የዘገቡት ታሪክ ነው። የሆኑ ሰዎች ከበስራ (ኢራቅ) አካባቢ ለሀጅ መጡ። ሶሐባው ዐብደላህ ኢብን ዑመርን (ረድየላሁ ዐንሁማ) አገኙ። ከዚያም በአካባቢያቸው ቀደርን (የአላህን ውሳኔ) የሚያስተባብሉ ሰዎች እንዳሉ ነገሯቸው። በዚህን ጊዜ ኢብኑ ዑመር "**ንገሯቸው እኔም ከነሱ አይደለሁም፣ እነሱም ከእኔ አይሉም**። በቀደር እስከሚምኑ ድረስ **<u>በአላህ መንገድ ላይ የኡሁድ ተራራን የሚያክል ወርቅ ቢሰጡ አላህ አይቀበላቸውም</u>**" በማለት መለሱላቸው።

ይህ ታሪክ የሚያስረዳን እምነት ሳይስተካከል የተሰራ ስራ የኡሁድ ተራራን የሚያክል ወርቅ በአላህ መንገድ ላይ ቢለግሱ እንኳን ተቀባይነት እንደሌለው ነው። ለዚህም ነው ከምንም በፊት እምነትን፣ አቂዳን፣ ተውሒድን ማስተካከል ግድ የሆነበት ምክንያት።

መልካምን ነገር ሌላ መልካም ነገር ይበልጠዋል። የመልካም ነገሮች ሁሉ ቁንጮ ተውሒድ እምነትን ማስተካከል ስለሆነ የመጀመሪያው ጥሪ የተደረገው በዚህ ጉዳይ ላይ ነው። ከዚያም ነብዩ (ﷺ) **<u>"ይሄን እሺ ካሉህ"</u>** በማለት ወደ ሁለተኛው መልካም ትእዛዝ ጠቆሙ። መልካም ስራዎች ሁሉ የሚገነቡት ተውሒድ የሚባለው ታላቁ መሰረት ሲስተካከል ነው። ለዚያም ነው **<u>"የመጀመሪያ የምትጠራቸው ከአላህ በስተቀር (እውነተኛ) አምላክ እንደሌለ እና እኔም የአላህ መልክተኛ መሆኔን እንዲመሰክሩ"</u>** በሌላ ዘገባ **<u>"አላህን በብቸኝነት በአምልኮ እስኪነጥሉት ድረስ"</u>** የሚል ነብያዊ ተእዛዝ ለሙአዝ የተላለፈው። እሱም እንደታዘዘው የፈጸመው።

4. ነብዩ (ﷺ) ስልጣናቸው እና ደረጃቸው ምን ደረሰ ነው?

ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባልደረባዎቻቸውን **"እኔ ባርያ ነኝ። ስለዚህ የአላህ ባርያ እና መልክተኛው በሉ"** ብለዋል። ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የአላህ ባርያ እና መልክተኛ መሆናቸውን አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ سُبۡحَٰنَ ٱلَّذِيٓ أَسۡرَىٰ بِعَبۡدِهِۦ لَيۡلٗا مِّنَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ إِلَى ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡأَقۡصَا ٱلَّذِي بَٰرَكۡنَا حَوۡلَهُۥ لِنُرِيَهُۥ مِنۡ ءَايَٰتِنَآۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ ١ ﴾ الإسراء: ١

"ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኼደው(ጌታ) ጥራት ይገባው። ከተዓምራቶቻችንል ናሳየው(አስኼድነው)። እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው ተመልካቹው ነው።" [አልኢስራእ፡ ١]

መልክተኛው ስለመሆናቸውም እንዲህ ይላል፡-

﴿ مُّحَمَّدٞ رَّسُولُ ٱللَّهِۚ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ أَشِدَّآءُ عَلَى ٱلۡكُفَّارِ رُحَمَآءُ بَيۡنَهُمۡ ﴾ الفتح: ٢٩

"ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ ነው።" [አልፈትሕ፡ 29]

የአላህ መልክተኛ (ﷺ) የሩቅን አያውቁም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُل لَّآ أَقُولُ لَكُمۡ عِندِي خَزَآئِنُ ٱللَّهِ وَلَآ أَعۡلَمُ ٱلۡغَيۡبَ وَلَآ أَقُولُ لَكُمۡ إِنِّي مَلَكٌۖ إِنۡ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّۚ ﴾ الأنعام: ٥٠

"ለእናንተ የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልልም። ሩቅንም አላውቅም። ለእናንተም እኔ መልአክ ነኝ አልልም። ወደእኔ የሚወረድልኝን እንጅ ሌላን አልከተልም" በላቸው።" [አል-አንኣም 50]

የአላህ መልክተኛ (ﷺ) ከሰዎች ልቦና ውስጥ መቀናትን (ሂዳያን) ማስረፅ አይችሉም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّكَ لَا تَهۡدِي مَنۡ أَحۡبَبۡتَ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَهۡدِي مَن يَشَآءُۚ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِٱلۡمُهۡتَدِينَ ٥٦ ﴾ القصص: ٥٦

<u>"አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽመህ ታቀናዎ</u>ም። ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል እርሱም ቅኖቹን ዐዋቂ ነው።" [አልቀሶስ፡ 56]

የአላህ መልክተኛ (ﷺ) እራሳቸውን ከጉዳት መጠበቅ አይችሉም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَإِن يَمۡسَسۡكَ ٱللَّهُ بِضُرّٖ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَۖ وَإِن يَمۡسَسۡكَ بِخَيۡرٖ فَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ١٧ ﴾ الأنعام: ١٧

<u>"አላህም በጉዳት ቢነካህ ለእርሱ (ለጉዳቱ) ከእርሱ (ከአላህ) በቀር ሌላ አስወጋጅ የለም</u>። በበጎም ነገር ቢነካህ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።" [አልአንዓም፡ 17]

<u>ሰው ናቸው</u>፡- አንዳንድ አላዋቂዎች እንደሚሉት ብርሃን ወይንም ከብርሀን የተፈጠሩ አይደሉም። ከአባታቸው ዐብደላህ እና ከእናታቸው አሚና የተወለዱ ሰው ናቸው። አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው ጌታችን አላህ አልተወለደም።

---

[3] ይህ አንቀጽ የወረደው ነብዩ (ﷺ) አጎታቸው አቡ ጧሊብ እንዲመራ በመፈለጋቸው ሰበብ ነው። አላህም አንተ እኮ የፈለግከውን ሰው አታቀናም። ነገር ግን አላህ የሚሻውን ሰው ይመራል ሲል የሳቸውን ድርሻ ነገራቸው። የሳቸውም ድርሻ ሐቁን ማስተላለፍ እና ለሰው ልጆች ማድረስ ነው።

ይታመማሉ:- ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ብዙ ጊዜ ታመው የነበሩባቸው ክስተቶች ነበሩ። ሞት አፋፍ ላይ ሆነውም ከባድ ትኩሳት በሽታ አጋጥሟቸው ነበር። አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው ጌታችን ግን የታመመን ሁሉ የሚያድነው እሱ ብቻ ነው።

ይረሳሉ:- ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ይላሉ **"እናንተ እንደምትረሱት እኔም እረሳለሁ። ስረሳ አስታወሱኝ።"** አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው ጌታችን አላህ ግን ምንንም ነገር አይረሳም።

ይራባሉ:- ነብዩ (ﷺ) በአንድ አጋጣሚ እሳቸው፣ አቡበክር እና ኡመር (ረድየላሁ ዐንሁማ) ተርበው ነበር። አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው ጌታችን አላህ ግን የሚመግብ እና የማይመገብ ነው።

ይተኛሉ:- ነብዩ (ﷺ) እንቅልፍ ወስዷቸው ፈጅር ሰላት አምልጧቸው ያውቃሉ። አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው ጌታችን አላህ ግን አያንጎላጅም አይተኛም።

ሞተዋል:- ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሞተዋል። በብቸኝነት አምልኮ የሚገባው ጌታችን ግን ህያው እና የማይሞት ነው። ከነብያት ቀጥሎ ምርጥ ሰው የሆኑት አቡበክር ሲዲቅ (ረድየላሁ ዐንሁ) የአላህ መልክተኛ (ﷺ) የሞቱ ጊዜ እንዲህ ብለዋል **"ሙሐመድን የሚያመልክ ከነበረ ሙሐመድ በእርግጥ ሞተዋል። አላህን የሚያመልክ አላህ ህያው እና የማይሞት ነው።"**

አግብተዋል ወልደዋል:- ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አግብተው ሰባት ልጆች ወልደዋል። አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው ጌታችን አላህ ደግሞ ሚስት የለውም። አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው ጌታችን አላህ አልወለደም።

ፍጡር ናቸው፡- ፈጣሪ ብቸኛው አንድ አምላክ አላህ ሲሆን ከርሱ ውጭ ያሉት በጠቅላላ ፍጡር ናቸው። ይህን በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈለገበት ምክንያት ብዙ ሰው ለአላህ ብቻ የሚገባውን አምልኮ ለነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አሳልፎ ሲሰጥ ስለሚታይ ነው። ለምሳሌ

- **“ነብዩ ልጅ ስጡን”** በማለት የሚለምኑ፣
- **“ነብዩ ያለፈውን እና መጪ ወንጀላችንን ምረውናል”** የሚሉ፣
- **“መገን ነቢ የሁሉ ቀላቢ”** እያሉ ሲሳይ እንደሚቸሩ የሚያምኑ፣
- **“ልቤ ባንቱ በእርሶ ተመካ”** እያሉ በሳቸው የሚመኩ፣
- **“ኹዝ ቢየዲ” የድረሱልን ተማፅኖ የሚያሰሙ**
- **“አብሽር ወንድሜ ግባ በቶሎ፣ ማን ነው ያፈረው ያ ነቢ ብሎ”** እና የመሳሰለውን እያሉ የአላህን ብቸኛ መብት ለነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የሚሰጡ አሉ። ይህ በእርግጥ ሺርክ ነው። ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) እንደ ሌሎች ነብያት ሁሉ ይዘውት የመጡት መልእክት አላህን በብቸኝነት እንድናመልክ። ከእርሱ ውጭ በሚመለኩት የውሸት አማልክት በጠቅላላ እንድንክድ ነው።

ኢሳ (ዐለይሂ-ሰላም) የአላህ ነብይ እና ከ 5 የቁርጠኝነት ባለቤት መልክተኞች ውስጥ ከመሆናቸው ጋር ምንም አምልኮ አይገባቸውም ብለን አፋችንን ሞልተን እንናገራለን። ምክንያቱም ሃላፊነታቸው ከአላህ የተላከውን መልእክት ማድረስ እንጂ ከአላህ ከጌትነትም ይሁን ከአምላክነት ምንም ድርሻ የላቸውም፣ ሸሪካም አይደሉም፣ ረዳትም አይደሉም፣ አላህ ከፈቀደ በኋላ ቢሆን እንጂ አያማልዱም። ልክ እንደዚሁ ነብዩም (ﷺ) የአላህ መልክተኛ እና ባሪያው ናቸው። ይሁን እንጂ ከአላህ የተላኩትን መልእክት ከማድረስ ባሻገር ከጌትነትም ይሁን ከአምላክነት ምንም ድርሻ የላቸውም፣ ሸሪካም አይደሉም፣ ረዳትም አይደሉም፣ አላህ ከፈቀደ በኋላ ቢሆን እንጂ አያማልዱም።

5. <u>ፈጣሪ እና ፍጡሮቹ</u>

የሁሉ ጌታ፣ ብቸኛው ፈጣሪ አንድ አምላክ አላህ ብቻ ነው። አላህ ከእርሱ ውጭ ያሉትን ሁሉ የፈጠረ የአለማቱ ሁሉ ጌታ ነው። አላህ እንዲህ ይላል

﴿ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ۝٢ ﴾ الفاتحة: ٢

"ምስጋና ለአላህ ይገባው <u>የዓለማት ጌታ ለሆነው</u>።" [አልፋቲሐህ፡ 2]

የሰው ልጅ ፈጣሪውን ትቶ ልክ እንደሱ ፍጡር የሆኑትን ቢያመልክ የኪሳራዎች ሁሉ ከባድ ኪሳራ ውስጥ ወድቋል። ያለመውንም ሳያገኝ ከጌታውም ጋር ተጣልቷል። ምክንያቱም ፍጡራን ከላይ እስከ ታች ሁሉም ከአላህ ከጃዮች ናቸውና። ደግሞም ደረጃቸው ቢለያይም ሁሉም የፍጡር ድንበርን የማይሻገሩ ባርያዎች ናቸው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَمۡ خُلِقُواْ مِنۡ غَيۡرِ شَيۡءٍ أَمۡ هُمُ ٱلۡخَٰلِقُونَ ۝٣٥ ﴾ الطور: ٣٥

<u>"ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን</u> ? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን ?"

[አጥቡር፡ 35]

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ عِبَادٌ أَمۡثَالُكُمۡۖ فَٱدۡعُوهُمۡ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ۝١٩٤ ﴾ الأعراف: ١٩٤

"<u>እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው (እነሱም) ብጤዎቻችሁ ተገዢዎች (ባሪያዎች) ናቸው</u>። እውነተኞችም እንደሆናችሁ ጥሩዋቸውና ለእናንተ ይመልሱላችሁ፤ (መመለስ ግን አይችሉም)።" [አልአዕራፍ፡ 194]

ጂብሪል (ዐለይሂ-ሰላም) የመላእክቶች አለቃ ነው። ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ደግሞ የነብያት ሁሉ ኢማም ናቸው። ሁለት የፍጡራን ቁንጮዎች። ከመሆኑም ጋር ነብዩ (ﷺ) ጂብሪል **"ምን ነው እንደበፊቱ ቶሎ ቶሎ አትመጣም?"** ብለው ሲጠይቁት እንዲህ ነበር ያለው፡-

﴿ وَمَا نَتَنَزَّلُ إِلَّا بِأَمْرِ رَبِّكَ ۖ لَهُۥ مَا بَيْنَ أَيْدِينَا وَمَا خَلْفَنَا وَمَا بَيْنَ ذَٰلِكَ ۚ وَمَا كَانَ رَبُّكَ نَسِيًّا ﴿٦٤﴾ ﴾ مريم: ٦٤

"(ጂብሪል አለ) "<u>በጌታህም ትእዛዝ እንጅ አንወርድም</u>። በፊታችን ያለው፣ በኋላችንም ያለው በዚህም መካከል ያለው ሁሉ የርሱ ነው። ጌታህም ረሺ አይደለም።" [መርየም፡ 64]

ተመልከቱ እንግዲህ የመለእክቶች አለቃ ጂብሪል ካለበት ቦታ ያለ አላህ ፍቃድ መንቀሳቀስ አይችልም።

6. <u>ህያው የማይሞት አላህ እና ሙታን ፍጡሮቹ</u>

አላህ ከምንም በፊት መጀመሪያ የነበረ ነው። ሁሉም ሞተው ብቻንም ቀሪ ነው። ነብዩን (ﷺ) የየመን ሰዎች **"እንዴት ይሁ ሁሉ ነገር ጀመረ?"** ብለው ጠየቁ። ነብዩም (ﷺ) እንዲህ አሉ፡- ***"<u>መጀመሪያ አላህ ነበር</u>። <u>ከእርሱም ጋር ምንም ነገር አልነበረም</u>። <u>አርሹም ውሃው ላይ ነበር</u>። ከዚያም ሰማያትእና ምድሮችን ፈጠረ።"*** ቡኻሪ ዘግበውታል

እንግዲህ አላህ ስለ እራሱ እንዲህ ሲል ይነግረናል

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْحَىُّ ٱلْقَيُّومُ ۚ ﴾ البقرة: ٢٥٥

"አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። <u>ሕያው</u> ራሱን ቻይ ነው።" [አልበቀራህ፡ 255]

ነብዩ (ﷺ) ደግሞ ጌታችንን አላህ እንዲህ ሲሉ ያወድሱታል፣ ይለምኑታል።

يَا حَيُّ يَا قَيُّومُ بِرَحْمَتِكَ أَسْتَغِيثُ أَصْلِحْ لِي شَأْنِي كُلَّهُ ، وَلَا تَكِلْنِي إِلَى نَفْسِي طَرْفَةَ عَيْنٍ

"<u>ህያው የሆንከው</u>፣ ፍጡራንህን የምታብቃቃው በራሰህ የምትብቃቃው (አላህ) በእዝነትህ እርዳታን እለምንሃለሁ። ሁለመናዮን አሳምርልኝ። እኔን ለነፍሴ ለቅጽበት ታክለ እንኳን አትተወኝ።" [ሰሂህ አ-ተርጊብ ወተርሂብ፡ 661]

ሁሉም ጠፍተው የልቅና እና የክብር ባለቤት የሆነው አላህ እንደሚቀር እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ كُلُّ مَنْ عَلَيْهَا فَانٍ ﴿٢٦﴾ وَيَبْقَىٰ وَجْهُ رَبِّكَ ذُو الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ ﴿٢٧﴾ ﴾ الرحمن: ٢٦ - ٢٧

"በእርሷ (በምድር) ላይ ያለው ሁሉ ጠፊ ነው። <u>የልቅናና የልግሥና ባለቤት የሆነው የጌታህ ፊትም ይቀራል።"</u> [አርረሕማን፡ 26-27]

ነብዩ (ﷺ) ሁሉም ፍጡራን ሞተው አላህ ብቻውን እንደሚቀር እና **"እነዚያ አምባ ገነኖች እነዚያ ኩራተኞች የት አሉ?"** እንደሚል ነግረውናል። [ሙስሊም፡ 2788]

የአላህ ባሪያዎች ሆይ! ስለዚህ አምልኮ የሚገባው ህያው ለሆነው አላህ እንጂ ለሞቱት ወይም ለሚሞቱት ኢሳ (ዐለይሂ-ስሰላም) ወይንም ለሞቱት ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ)፣ መርየም፣ ፋጢማ (ረድየላሁ አንሃ)፣ አልይ (ረድየላሁ አንሁ)፣ ሁሴን (ረድየላሁ አንሁ) እና መሰሎቻቸው አይደለም። እነዚህን ታላላቅ የአላህ ባሪያዎች የጠቀስኩት

ለምሳሌነት ነው። እነሱን ከአላህ ውጭ ማምለክ ካልተቻለ፣ ሌሎቹንማ ይበልጥ አይቻልም። አንድ አንቀጽ ልጨምር፡-

﴿ وَتَوَكَّلْ عَلَى ٱلْحَيِّ ٱلَّذِى لَا يَمُوتُ وَسَبِّحْ بِحَمْدِهِۦ ۚ وَكَفَىٰ بِهِۦ بِذُنُوبِ عِبَادِهِۦ خَبِيرًا ﴿٥٨﴾ ﴾ الفرقان: ٥٨

"<u>በዚያም በማይሞተው ሕያው አምላክ ላይ ተመካ</u>። ከማመሰገንም ጋር አጥራው። በባሮቹ ኀጢአቶችም ውስጠ ዐዋቂነት በእርሱ በቃ።" [አል ፉርቃን፡ 58]

በየትኛውም ዘመን ከአላህ ውጭ የሚመለኩት ሁሉ ይህንን የሚያሟሉ አይደሉም። **<u>ሁሉም የአላህ ፍጡሮችናቸው</u>፣ <u>ሁሉም ሟቾች ናቸው</u>፣ <u>ሁሉም ጠፍተው የልቅናና የልግሥና ባለቤት የሆነው የጌታ አላህ ፊት ይቀራል</u>።**

7. <u>አላህ የሚመግብ እና የማይመገብ ነው።</u>

የአላህ ባሪያዎች ሆይ! አምልኮ የሚገባው ሁሉን መጋቢ ለሆነው ፈጣሪ እንጂ ለተመጋቢ ፍጡራን አይደለም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلْ أَغَيْرَ ٱللَّهِ أَتَّخِذُ وَلِيًّا فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَهُوَ يُطْعِمُ وَلَا يُطْعَمُ ۗ قُلْ إِنِّىٓ أُمِرْتُ أَنْ أَكُونَ أَوَّلَ مَنْ أَسْلَمَ ۖ وَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٤﴾ ﴾ الأنعام: ١٤

"ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ከሆነው አላህ <u>እርሱ የሚመግብ የማይመገብም ሲሆን ሌላን አምላክ እይዛለሁን?</u>" በላቸው። "እኔ መጀመሪያ ትእዛዝን ከተቀበለ ሰው ልሆን ታዘዝኩ። ከአጋሪዎችም ፈጽሞ አትሁን (ተብያለሁ)" በላቸው። [አል-አንዓም፡ 14]

8. <u>እነሱ “መቃረቢያ” ሲሉት፣ አላህ ሺርክ ሲል ጠራው።</u>

የላቀው አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَ مَا نَعۡبُدُهُمۡ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلۡفَىٰٓ ﴾ الزمر: ٣

“እነዚያም ከእርሱ ሌላ ረዳቶች የያዙት <u>“ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም”</u> (ይላሉ)።” [አዝዙመር፡ 3]

ሸይኽ ሷሊህ አል-ፈውዛን አላህ ከከፉ ይጠብቃቸውና እንዲህ አሉ፡-

<u>ሺርክን ለመስራት አላሰቡም ነበር</u>። <u>አላማቸውም አልነበረም</u>። <u>እነሱ አምልኮን ማሚያ ለመፈጸም እና በዚህም ወደ አላህ ለመቃረብን ብቻ ነበር ያሰቡት</u>። ሸይጧን የአደም ልጆችን ለማሳሳት እንዴት እንደሚቀርባቸው እና ከሰው ሰይጣናት ውስጥ የሆኑት የአደም ልጆችን እንዴት ይህንን (የሺርክ) ተግባር አሳምረው እንደሚያቀርቡላቸው ተመልከት።

እኛም እንላቸዋለን፡- **ጣአቶቹን በቀጥታ ላታመልኩ ትችላላችሁ። ነገር ግን ጻድቃንን በናንተ እና በአላህ መካከል (ድልድይ) አድርጋችኋል። <u>ይህም ቢሆን አላህ ዘንድ ሺርክ ነው</u>።** አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمۡ وَلَا يَنفَعُهُمۡ وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا عِندَ ٱللَّهِۚ قُلۡ أَتُنَبِّـُٔونَ ٱللَّهَ بِمَا لَا يَعۡلَمُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِۚ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ١٨ ﴾ يونس: ١٨

"ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውንም ይግዛሉ። "<u>እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው</u>" ይላሉ። "አላህን በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን?" በላቸው። ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፤ ላቀም።" [ዩኑስ፡ 18]

ተመልከቱ አላህ **<u>"አላህ ከሁሉም ጠራ፤ ላቀም"</u>** ሲል ከነሱ እና ከተግባራቸው እራሱን ነጻ እንዳደረገ። "**<u>ከሚያጋሩት</u>**" ሲል ደግሞ ተግባራቸውን ሺርክ ብሎ እየጠራው ነው።" የሸይኽ ፈውዛን ንግግር እዚህ ላይ አበቃ።

ዛሬ ሺርክ የሚፈጽሙ ሰዎች ይህንኑ ነው ማማካኛ አድርገው የሚወስዱት። ተመሳሳይ ጥፋት። ተመሳሳይ ማመካኛ።

9. <u>የአላህ ወልይ ማን ነው?</u>

ወልይነት (ወዳጅነት ረዳትነት)፡- የጠላትነት ተቃራኒ ነው። የወልይነት መሰረቱ መውደድ እና መቃረብ ነው። የጠላትነት መሰረቱ መጥላት እና መራቅ ነው። "ዊላያ" በሙያዊ ፍቺው አንድ ባርያ አላህን በመታዘዙ አላህ ያን ባርያ መቅረቡ ነው። ወልይነት ኢማን እና አላህን መፍራት የተባሉትን ሁለት መስፈርቶች ይጠይቃል። አላህ አንዲህ ይላል፡-

﴿ أَلَآ إِنَّ أَوۡلِيَآءَ ٱللَّهِ لَا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ وَلَا هُمۡ يَحۡزَنُونَ ٦٢ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَكَانُواْ يَتَّقُونَ ٦٣ ﴾ يونس: ٦٢ - ٦٣

"ንቁ! የአላህ ወዳጆች በእነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም። <u>(እነሱም) እነዚያ ያመኑትና ይፈሩት የነበሩ ናቸው።</u>" [ዩኑስ፡ 62-63]

ስለዚህ አንድ ሰው በአላህ አምኖ አላህን እስከፈራ ድረስ ወልይ ነው። በመስፈርቱ መሰረትም፡-

<u>አባት</u>፡- በአላህ አምኖና እሱን ፈርቶ በስሩ የሚተዳደሩትን ቤተሰቦች በአግባቡ ከያዘ ይህ የአላህ ወልይ ነው።

<u>እናት</u>፡- በአላህ አምና እና እሱን ፈርታ፣ የባሏን ሃቅ ጠብቃ፣ ልጆቿን በስነ ስርዐት ካሳደገች የአላህ ወልይ ናት።

<u>ልጅ</u>፡- ልጆች በአላህ አምነውና እሱን ፈርተው፣ ለወላጆቻቸው ታዛዥ ሆነው፣ ወላጆቻቸውን ካገዙ የአላህ ወልዮች ናቸው።

<u>ነጋዴው</u>፡- ኢማንና ተቅዋን አስገኝቶ ንግዱን በአግባቡ ነግዶ፣ ከሃላል ከስቦ፣ ዘካውን ካወጣ ይህ የአላህ ወልይ ነው። ወዘተ....

ደግሞም ወልዮች የሚበላለጡት በኢማናቸው እና ለአላህ ባላቸው ፍራቻ ነው። ታላላቆቹ የአላህ ወልዮች ነብዮች ናቸው። ከነብዮቹም ውስጥ መልክተኞቹ ናቸው። ከመልክተኞቹም ውስጥ አምስቱ የቁርጠኝነት ባለቤቶች የሚባሉት ቁንጮዎች ናቸው። ከአምስቱ የቁርጠኝነት ባለቤቶች ውስጥ ደግሞ የሁሉ ቁንጮ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ናቸው።

ለምን ይህን አርእስት እዚህ መጸሀፍ ላይ ማንሳት አስፈለገ? ምክንያቱም አገራችን ላይ በብዛት ከአላህ ውጭ አምልኮ የሚፈጸምላቸው **<u>“ወልዮች”</u>** ተብለው የሚገመቱ ሰዎችን ነው። አንዳንዶች በድፍረት **<u>“ወልዮች ነብያትን ይበልጣሉ”</u>** ሁሉ ይላሉ። ይሄ የሰዎቹ ቅጥፈትና ድፍረት የት እንደደረሰ የሚያሳይ ነው።

ዛሬ በተገላቢጦሹ ማህበረሰባችን ዘንድ ከእምነት ክፍል ብዙ የሚያጓድሉ፣ ክህደትን እና ሺርክን (ለምሳሌ የሚጠነቁሉና ትንቢት ተናጋሪ ነን የሚሉ፣ የሚያጓሩ) እያጨማለቁ፣ በኢስላም ንፅህና የኢማን ግማሽ ሆኖ ሳለ በተገላቢጦሽ ንፅህናቸውን የማይጠብቁ፣ ሶላት ወይ ከነጭራሹ የማይሰግዱ ወይም ደግሞ ጀመአ የማይገኙ ወልይ ተብለው የሚገመቱ ብዙ ወንበዴዎች አሉ። እንዲህ አይነቱ የሰይጣን ወልይ እንጂ በፍፁም የአላህ ወልይ አይደለም።

10. <u>ረመዳንን ምንዳውን ምን ያጓድለዋል?</u>

ረመዳን ከአምስቱ የእስልምና ማዕዘናት ውስጥ አንዱ ነው። ረመዳን የቁርአን ወር ነው። ረመዳን የሰደቃ ወር ነው። ረመዳን ተራዊህ የሚሰገድበት ወር ነው። ረመዳን ብዙ መልካም ስራዎች የሚሰሩበት ወቅት ነው። ረመዳን ቁርአን የወረደበት ወር ለመሆኑ አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል

﴿ شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ ١٨٥ ﴾ البقرة: ١٨٥

“የረመዳን ወር ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች ሲሆን <u>ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው</u>።” [አልበቀራህ: 185]

በዚህ በተከበረ የቁርአን ወር የአላህ መልክተኛ (ﷺ) ከጂብሪል ዐለይሂ-ስሰላም ጋር አንድ ጊዜ እየተቃሩ ሙሉ 30 ጁዝ ቁርአንን ይጨርሱ ነበር። የሞቱ አመትም ሁለት ጊዜ ጨርሰዋል።

አላህ ሙሉ ምንዳ የሚከፍለው ረመዳንን አምኖ፣ ሂሳቤን አላህ ይከፍለኛል ብሎ፣ መልካምን በመስራት ከአልባሌ ነገሮች በመራቅ ነው። የአላህ መልክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡-

قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم "مَنْ لَمْ يَدَعْ قَوْلَ الزُّورِ وَالْعَمَلَ بِهِ فَلَيْسَ لِلَّهِ حَاجَةٌ فِي أَنْ يَدَعَ طَعَامَهُ وَشَرَابَهُ ".

“አንድ ባሪያ የቅጥፈት <u>ወሬንእና በሱ መስራትንም ያልተወ ሰው ምግቡንና መጠጡን ከመተው አላህ ደንታ የለውም</u>።” አል- ቡኻሪ

ተራ ቅጥፈቶች ለዚህ የሚዳርጉ ከሆነ ሺርክ እና ቢድአ ደግሞ ከነዚህ ሁሉ የባሰ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። **ይህ ሆኖ ሳለ ዛሬ በሃገራችን በተውሒዱ ወር በረመዳን ሰው ቁርኣን እየቀራ እንዳያሳልፍ መንዙማ ባዮች በየቋንቋው ሺርክ፣ ጭፈራ እና ብዙ ጉድ ያለባቸውን መንዙማዎች ይዘው በየመስጂዱ እና ገበያ ቦታ ላይ ከታላቅ ማስታወቂያ ጋር ብቅ ይላሉ።** ሀስቡነላህ ወኒእመል ወኪል። ይሄ እንደዋዛ ሊታይ የማይገባው አደገኛ ጥፋት ነው። ብዙዎቻችን ግን ጥፋቱ ከመንሰራፋቱ፣ ዘወትር ከመሰማቱ የተነሳ ጆሯችን ለምዶት ውስጣችን እስከማይደፈርስ ደርሷል።

ሌላው አገራችን ላይ አንዳንድ መስጊዶች ለአፍጥር ሰኣት 30 ደቂቃ ሲቀረው በሚያሳዝን ሁኔታ ማይክሮፎን ከፍተው በአላህ ላይ የማጋራትን ንግግር በአንድነት በዜማ ሲያስተጋቡ ይስተዋላሉ። ለምሳሌ እንዲህም ይላሉ፡-

“ኹዝ ቢየዲ ያረሱለላህ፣ አጊስና ያረሱለላህ”

ትርጉሙም

“አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ! እጄን ያዙኝ። አንቱ የአላህ መልክተኛ ሆይ! እርዱን (አጠጡን?)።”

ዶሞ ውሎ በሺርክ ማፍጠር ምንኛ ልብ ያደማል?!

፲፩. <u>መንዙማ እና መውሊድ</u>

መውሊድ ማለት የአንድን ግለሰብ የተወለደበት ቀን አመት ጠብቆ ማክበር ማለት ነው። የነብያት ሁሉ ሃይማኖት እስልምና የማንም ግለሰብ የልደት በአል እንዲከበር አልደነገገም። በእስልምና አንድ ሰው ልጅ ሲወለድለት ለጌታው ምስጋና ለማቅረብ እና ደስታውን ለመግለጽ ልጅ በተወለደለት በሰባተኛው ወይንም በአስራ አራተኛው ወይንም በቻለ ጊዜ ወንድ ከተወለደለት ሁለት በግ ወይንም ፍየል፣ ሴት ከተወለደለት አንድ በግ ወይንም ፍየል ያርዳል። ከወዳጅ ከዘመዶቹም ጋር በጋራ ይመገበዋል። አላህ የደነገገው እንግዲህ ይህን ነው።

ከዚህ ውጭ ያለውና ከሱና ባፈነገጡት ሺአዎች የተጀመረው የሺርክ መነሀሪያ የሆነው መውሊድ ግን ቢድአ ነው። እዚሁ መውሊድ የሚሉት ላይ **“ሀድራ”**፣ **“መንዙማ”** እየተባለ እዚሁ መፅሀፍ ላይ ወደፊት የምናያቸው በርካታ ጥፋቶች ይፈፀማሉ። የአላህ መልክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡-

“ከንግግር ሁሉ በላጭ የአላህ ንግግር ነው፣ ምርጥ የሚባለው መመሪያ የሙሐመድ ﷺ መመርያ ነው፤ ከነገሮች ሁሉ የከፋው (በዲን ላይ) ፈጠራ ነው፤ ፈጠራ የተባለ ሁሉ ቢድዐ ነው፤ ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነው፤ ጥመት ሁሉ የእሳት ነው።” [ሙስሊም፡ 867]

12. <u>ሰርጋችን</u>

እስልምና ውብና የተሟላ የህይወት መመሪያ ነው። ትልልቅ የህይወታችን ክፍሎች ቀርቶ ትንንሽ የሚባሉት እራሱ ዝርዝር መመሪያ ተቀምጦላቸዋል። **<u>አንዳንዶች ግን ይህን እውነታ በመዘንጋት ወይም ችላ በማለት ከሸሪአው መመሪያ ወጥተው በራሳቸው ሲጓዙ ያጋጥማሉ።</u>** ለምሳሌ ሰርግን ብንወስድ ምን መምሰል እንዳለበት፣ ምን መባል እንዳለበት፣ ሙስሊሞች በሰርግ ላይ እንዴት መደሰት እንዳለባቸው ሸሪአ ጠቁሞናል። ሆኖም ግን ዛሬ ከሳቸው ንግግር እና ከኢስላም በተቃራኒ **ኢስላማዊ ዲጄ** እየተባለ፣ **የሺርክ መንዙማዎች እየተዜሙ፣ ወንዶች እየጨፈሩ እና እያጨበጨቡ፣ ሴቶች ባልተፈቀደላቸው የሙዚቃ መሳሪያ እየጨፈሩ፣ ሴት እና ወንድ ተቀላቅለው እየጨፈሩ፣ እያቋጩ** ወዘተ ታላቁን የደስታ ቀን አላህን በማመጽ የሚያሳልፉት አሉ።

የአላህ ባሪያዎች ሆይ! ይህን ታላቅ የደስታ ቀን ኒካሁ እንደታሰረ ለሙሽራው እና ለሙሽሪቷ **<u>"ባረከላሁ ለኩማ ወባረከ አለይኩማ ወጀመአ በይነኩማ ፊ ኸይር"</u>** ተብሎ ዱአ እንደሚደረግላቸው ከውዱ ነብይ (ﷺ) ፈለግ ተምረናል። ይህንን ዱአ ያደረጉት ለኡመቱ ታማኝ እና አዛኝ መካሪ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ናቸው። ልብ እንበል! አሁንም ይህንኑ ዱአ በሙዚቃ መሳሪያ እና በጭፈራ **<u>"ባረከላሁ ለኩማ"</u>** ብለን ካልቀወጥነው **<u>"ለቅሶ ቤት እኮ አይደለም የመጣነው"</u>**፣ **<u>"የእነእገሌ ዘፋኝን ከመስማት አይሻልም ወይ?"</u>** የሚሉ አሉ። ይሄ አደብ የቀለለው አነጋገር ነው። ሙስሊም ማለት ለፈጣሪው ህግ እጅ የሚሰጥ ነው። ሙስሊም ማለት የሶሐቦችን አርአያ የሚከተል ነው። ሶሐቦች ሰርጋቸውን የጋጠ ወጦች አይነት ካላደረግን **"ለቅሶ ቤት"** ይሆንብናል የሚሉ ግብዞች አልነበሩም። የደስታ ቀንን እንዴት ጌታቸውን እያመሰገኑ ማሳለፍ እንዳለባቸው ስለሚያውቁ በነብዩ (ﷺ) ሱና መሰረት ነው የተጓዙት።

13. <u>መንዙማ ድሮ እና ዘንድሮ</u>

አብዛኞች ከሚሸወዱባቸው ነገሮች ውስጥ **“የድሮ መንዙማ እና የአሁን መንዙማ ይለያያሉ”፣ “የድሮ መንዙማዎች ሺርክ አለባቸው”፣ “ድቤ አላቸው”፣ “የአሁኖቹ ደግሞ እንጎርጉሮ የሆነም አለ”፣ “ድቤ ያለውም ከሽርክ የጸዳ ነው”** የሚሉ አሉ።

እውነታው ግን አዲስ እየተባሉ የወጡ መንዙማዎች አብዛኛዎቹ ግጥማቸውም ይሁን ዜማቸው ከድሮዎቹ የተቀዱ ናቸው። ስለዚህ የድሮዎቹ ላይ ችግር እንዳለ ከታመነ በተጨባጭ ከነችግራቸው እየተወረሱ ነው።

“ድቤም ቢኖረው ከሺርክ የጸዳ ነው” የሚሉትም ከእውነት የራቀ ነው። ለዚህ በምዕራፍ ሁለት ብዙ ምሳሌዎችን እንመለከታለን።

በየሰርግ ቤቱ በየአጋጣሚው የሚባሉ የሺርክ ስንኞችን ድሮም ይባሉ ዘንድሮ፣ በድቤም ይሁን በእንጉርጉሮ፣ ስቱድዮ ውስጥም ይሁኑ መስጂድ ውስጥ ከአላህ ውጭ ያሉ አካላት እስከተጠሩበት ድረስ ሁሉም ሺርክ ነው። አብዛኛው እዚህ መፀሃፍ ላይ የሰበሰብኳቸው የሺርክ ስንኞች 70 ፐርሰንቱ ያህል በዚህ ዘመን ነሺዳ፣ እንጉርጉሮ እየተባሉ ከሚለቀቁት ላይ ነው።

“ሺርክና የሙዚቃ መሳሪያ የሌለበት” የሚሉት ነሺዳም ይሁን መንዙማ ሙስሊሙን ኡማ ቁርአንን ከመቅራት፣ ቁርአንን ከመስማት፣ ቁርአንን ከመሀፈዝ፣ በሸሪዓ የተደነገጉ ዚክሮችን ከመዘከር እና ሸሪኣዊ እውቀትን ከመፈለግ አዘናግቷል። ይህም የጥፋት መንገድ ለመሆኑ ከበቂ በላይ ነው። ሸይኽ አልባኒ (ረሂመሁላህ) እንዲህ ብለዋል “.....ነሺዳ ሀራም በሆኑ ላይ ሁለት ነገር ማስረጃ ማድረጋችን በቂ ነው። አንደኛው ሰለፉነ ሷሊህ በዚህ መንገድ አይጠቀሙም ነበር። ሁለተኛው በተጨባጭ የማየው እና የምመሰክረው እሱም ቢሆን አደገኛ ነገር ነው። ይህም የሙስሊም ወጣቶች የሚረኩት

በኢስላማዊ ነሺዳ ነው። በእሷም ይዘፍናሉ። ... ሁል ጊዜ። ይህም ተግባራቸው ቁርአን ከመቅራት፣ አላህን ከማውሳት፣ ነብዩ ላይ ሶለዋት ከማውረድ አዘናጋቸው።...." ምንጭ አልበያን አል-ሙፊድ አን ሁክሚ አተምሲሊ ወል አናሺድ ሸይኽ ሷሊህ አል-ፈውዛን ሀፊዘሁላህ ያዩለት የአብደላህ አስ-ሱለይማኒ መፀሀፍ።

14. <u>ሶለዋት ማውረድ ኢባዳ ነው</u>

ሶለዋት ማውረድ ታላቅ አምልኮ ነው። ነብዩ (ﷺ) እኛ ላይ ካላቸው መብቶች አንዱ እሳቸው ላይ ሶለዋት ማውረዳችን ነው። ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ይላሉ **"በኔ ላይ አንድ ሶለዋት ያወረደ አላህ በእሱ ላይ አስር ያወርድበታል።"** [ሙስሊም፡ 384] በሳቸው ላይ ሶለዋት እንድናወርድ አላህም እንዲህ ሲል ያዘናል

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيۡهِ وَسَلِّمُواْ تَسۡلِيمًا ٥٦ ﴾

الأحزاب: ٥٦

"አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ። የማከበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ።" [አልአሕዛብ፡ 56]

የአላህ ባሪያዎች ሆይ! ተመልከቱ የአላህ መልክተኛ (ﷺ) አላህ ዘንድ ያላቸው ደረጃ እና ማዕረግ በጣም ታላቅ መሆኑን ከዚች አንቀጽ እንገነዘባለን። አላህ እና መላእክቱ የሚያደርጉት ሶለዋት ምንድን ነው? ታላቁ ሶለፍ አቡል ዐሊያ (ረሒመሁላህ) እንዲህ ይላሉ፡-

- ሶለዋት "ከአላህ ሲሆን አላህ በላይኛው ነዋሪዎች (መላእክቶች) ዘንድ ነብዩን ማወደሱ ነው።"

- የመላእክት ሶለዋት ደግሞ “ዱዐ ማድረጋቸው ነው።” [ቡኻሪ፡ 6/120]

እሳቸው ላይ ከምናወርደው የሰለዋት አይነቶች ውስጥ በላጩ እሳቸው ለሶሐባዎቻቸው በላጭ ነው ሲሉ ያስተማሩት ነው። ይህም የተለያዩ ቅርፆች ያሉት ሲሆን የሚከተለው አንዱ ነው፡-

"اللهم صل على محمد وعلى آل محمد كما صليت على آل إبراهيم إنك حميد مجيد، وبارك على محمد وعلى آل محمد كما باركت على آل إبراهيم إنك حميد مجيد"

“አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ እዝነትህን እንዳሰፈንከው ሁሉ በሙሀመድና በቤተሰቦቻቸው ላይም እዝነትህን አስፍን፣ አንተ ምስጉንና የላቅክ አምላክ ነህ። አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ በረከትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ በሙሀመድና በቤተሰቦቻቸው ላይም በረከትህን አዉርድ። አንተ ምስጉንና የላቅክ አምላክ ነህ።” [ቡኻሪ፡ 3369፣ ሙስሊም፡ 406]

ስለዚህ በመልእክተኛው (ﷺ) ላይ ሰለዋት ማውረድን የሚሻ ሰው በማስረጃ በመጣው መሰረት ሊያደርገው ይገባል። ምክንያቱም አምልኮ ተውቂፊይ ነውና።

<u>ተውቂፊይ ማለት ምን ማለት ነው?</u>

አምልኮ ተውቂፍይ ነው ሲባል አላህ እና መልክተኛው (ﷺ) ባዘዙበት መልኩ ብቻ የሚፈጸም ነው ማለት ነው። ለምሳሌ ሰላትን ብንወስድ የምንሰግደው በመልእክተኛው (ﷺ) በታዘዝነው መሰረት ነው። ለዚህም እራሳቸው **<u>“ስሰግድ እንዳያችሁኝ ስገዱ”</u>** ማለታቸው ዋቢ መሆን ይችላል። ልክ ሶላታችንን እሳቸው ባስተማሩት መልኩ ሳይሆን እኛን ባሰኘን መልኩ እንደማንፈፀምው ሌሎች ዒባዳዎችንም ስለአፈፃፀማቸው በመጡት ማስረጃዎች ላይ ተገድበን ልንፈፅም ይገባል። **ያለበለዚያ**

መልክተኛ (ﷺ) ***<u>"የእኛ ትእዛዝ የሌለበትን ሰራ የሰራ ሰው ሰራው ተመላሽ ነው (ተቀባይነት አይኖረውም)</u>"*** ሲሉ ካስጠነቀቁት ውስጥ እንወድቃለን።

ሶለዋትን በተመለከተም ተመሳሳይ ቀመር ልንከተል ይገባል። እውነት አላህ በስራችን ምንዳን እንዲሰጠን እና ከቁጣው መራቅን ከፈለግን ሸሪዐው ባዘዘው መልኩ ልንፈፅም ይገባል። በሃገራችን የሚታየው ግን በብዙ መልኩ ከዚህ አደብ ጋር የሚፃረር ነው። በመልክተኛው እና ቤተሰባቸው ላይ አላህ እዝነቱን፣ ሰላሙን፣ በረከቱን እንዲያወርድ በውዝዋዜና በጭፈራ አጅቦ ሲለመን ማየት ለአስተዋዮች ያሸማቅቃል። ይባስ ብሎም ይህ ታላቅ አምልኮ ከሺርክ እየተቀላቀለ መፈፀሙ ነው። አንዳንዱ ቦታ ጭራሽ ወንድ እና ሴት የሚቀላቀሉበት ሁኔታም አለ። ይህ ተግባር የአላህን ቁጣ የሚያከናንብ፣ ምንዳን ሳይሆን ኪሳራ የሚያስከትል ጥፋት ነው።

<u>አምልኮ እና ጭፈራ የተለያዩ ናቸው።</u>

ዛሬ ዛሬ በአምልኮታዊ ስንኞች እያጨበጨቡ የሚጨፍሩ መመልከት የተለመደ ሆኗል። አምልኮትን ለጭፈራና ዘዛታ ማዋል ሰቅጣጭ ጥፋት ነው። እስኪ አስቡት አንድ ሰው ቁርአንን ለጭፈራ ሲጠቀምበት። ታዲያ ትልቁ ጥፋት እነዚህን በመንዙማም ሆነ በነሺዳ ስም የሚፈፀሙ ውዝዋዜዎች እንደ መቃረቢያ መቁጠራቸው ነው።

በዛዛታና በዘፈን የሚጨፍር ሰው "ተው" ተብሎ ሲመከር ወንጀል መሆኑን አውቆ "አላህ እንዲያላቅቀኝ ዱዓ አድርጉልኝ" ይላል እንጂ አጅር አገኝበታለሁ ብሎ አይሞግትም። በተገላቢጦሹ በሶለዋት ስም በየሰርጉ ላይ፣ በየሐድራው፣ በየመውሊዱ የሚሸበሸቡ ዜማዎች ግን እንደ መቃረቢያ ስለሚታሰቡ የሚጨፍሩት ሰዎች "ተዉ አላህን ፍሩ ሶለዋት ኢባዳ ነው፣ ኢባዳ (አምልኮ ደግሞ) በጭፈራ አይከናወንም" ሲባሉ አይደለም ዱዓ አድርግልኝ ሊሉ ቀርቶ ሸይጧን የሚሰሩትን ጥፋት አሳምሮላቸው

በሚቃወማቸው ሰው ላይ “**የነብዩ ሙሃባ የሌላቸው**”፣ “**ወሃቢይ**”፣... ወዘተ እያሉ ስም ይለጥፋሉ።

ሰለፎቻችን “**ቢድዓ ኢብሊስ ዘንድ ከወንጀል በላይ ይበልጥ ተወዳጅ ናት**” ማለታቸው ምንኛ እውነት ነው?! የአላህ ባሪያዎች ሆይ! እስኪ ግን እናስተውል!

- ቁርአን መቅራት፣ ዱዓ ማድረግ አምልኮ ናቸው ወይንስ አይደሉም?
  መልሳችንም “አዎ” እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።
- ታድያ የአላህን ቃል ቁርአን ስንቀራ አንድም ቀን ጨፍረን እናውቃለን?
- ዱዓ ስናደርግስ ጨፍረን እናውቃለን?
  መልሳችን “ኧረ በፍፁም” ይሆናል።
- ታድያ ለምን ይሆን ነብዩ (ﷺ) ላይ ሰለዋት ስናወርድ የምንጨፍረው?
  ሰለዋትስ አምልኮ (ሂባዳ) አይደለምን? መልሳችን እንዲያውም ከታላላቅ ሂባዳዎች መሃል ነው ይሆናል።

ስለዚህ የአላህ ባርያዎች ሆይ! የእውነት አላህን እንፍራ!! ሸይጧን እንዲጫወትብን እድል አንስጠው።

ሶሐባዎች ከማንም በላይ የነብዩ ﷺ ወዳጆች ናቸው። አላህ እና መልክተኛው ያላዘዙትን፣ ሶሐባዎች የማያውቁትን በሶለዋት ስም በሸሪዐ ያልተደነገጉ ሺርክ በተቀላቀለባቸው ስንኞች ማዜም፣ ማጨብጨብ፤ ማፏጨት እና መጨፈር ነገ ከአላህ ፊት እንዳንጠየቅበት በጊዜ ልንርቅ ይገባል። ብልጥ ማለት በነብዩ (ﷺ) ሱና የተብቃቃ ነው። የመካ ኢጋሪያን ካዕባ ዙርያ ያፏጩና ያጨበጭቡ ነበር። ይህም አስወግዟቸዋል። ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَا كَانَ صَلَاتُهُمْ عِندَ ٱلْبَيْتِ إِلَّا مُكَآءً وَتَصْدِيَةً ۚ فَذُوقُوا۟ ٱلْعَذَابَ بِمَا كُنتُمْ تَكْفُرُونَ ﴿٣٥﴾ ﴾ الأنفال: ٣٥

"በቤቱ ዘንድም (በከዕባ) <u>ሰግደታቸው ማፏጨትና ማጨብጨብ እንጂ ሌላ አልነበረም</u>። ትክዱት በነበራችሁትም ነገር ቅጣትን ቅመሱ (ይባላሉ)።" [አልአንፋል፡ 35]

ዛሬ ሰይጣን መጥፎ ስራቸውን አሳምሮ ያሳያቸው ሰዎች መስጂድ ውስጥ ሲያጨበጭቡ የማንን ፈለግ ነው እየተከተሉ ያሉት?! አስተዋይ ልብ ይበል!!

እንዲህ አይነቱ አካሄድ ሃይማኖትን መዝናኛና መቀለጃ አድርጎ መያዝ ነው። አላህ ውድ መልክተኛውን (ﷺ) እነዚያ ሃይማኖታቸውን ቀልድ እና ጨዋታ አድርገው ከያዙ ሰዎች እንዲርቁ እንዲህ ሲል ያዛቸዋል፡-

﴿ وَذَرِ ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُوا۟ دِينَهُمْ لَعِبًا وَلَهْوًا وَغَرَّتْهُمُ ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا ۚ ﴿٧٠﴾ ﴾ الأنعام: ٧٠

"<u>እነዚያንም ሃይማኖታቸውን ጨዋታና ላግጣ አድርገው የያዙትን ቅርቢቱም ሕይወት ያታለለቻቸውን ተዋቸው</u>።" [አልአንዓም፡ 70]

ወገኖቼ! ለምንሰራቸው ስራዎች ጥሩ ኒያ መሰነቃችን ብቻውን እንዳይሸውደን። አፈፃፀማችንም ከነብዩ (ﷺ) አፈፃፀም ጋር የሚገጥም መሆኑን ከመፈተሽ እንዳንዘናጋ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلْ هَلْ نُنَبِّئُكُمْ بِٱلْأَخْسَرِينَ أَعْمَٰلًا ﴿١٠٣﴾ ﴾ الكهف: ١٠٣

"በሥራዎች በጣም ከሳሪዎቹን እንንገራችሁን?" በላቸው። [አልከህፍ፡ 103]

﴿ ٱلَّذِينَ ضَلَّ سَعۡيُهُمۡ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُمۡ يَحۡسَبُونَ أَنَّهُمۡ يُحۡسِنُونَ صُنۡعًا ١٠٤ ﴾ الكهف: ١٠٤

"እነዚያ እነሱ ሥራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ በቅርቢቱ ሕይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው።" [አልከህፍ፡ 104]

ስለዚህ ሃቅ ለእኛ የመሰለን ሳይሆን ሸሪዓ ያዘዘበት፤ መለኮታዊ ራዕይ የወረደበት ነው። አላህን እንፍራ፣ በተለይ አሁን በየሰርግ ቤቱ በሶለዋት የሚጨፍሩ ሰዎች አላህን ፍሩ፣ ይህን መጥፎ መንገድ በማስተዋወቃችሁ፣ ሱናን በማጠልሸታችሁ ወደ አላህ በተውበት ካልተመለሳችሁ አደጋው ከባድ ነው። ሰርግ ቤት፣ መውሊድ፣ ሀድራ የሚባለው ላይ የሚሰራው ስራ ሸር ለመሆኑ ምንም እነሱ ጥሩ አስበን ነው (የነቢ ውዴታ ይዞን ነው) ቢሉም የመልክተኛውን ፈለግ መቃረኑ ብቻ ጥመት ለመሆኑ በቂ ማሳያ ነው።

አምልኮ ሊፈፀም የሚገባው አላህ እና መልክተኛው ባዘዙት መልኩ ሶሐባዎች በተረዱት አረዳድ ነው። መልካሙን ነገር ሁሉ ነብዩ (ﷺ) አሳይተዋል። ከመጥፎ ነገሮች ሁሉ ከልክለዋል። ሶሓባዎች የተብቃቁበት ሱና ለእኛም ይብቃን።

15. <u>በነብዩ (ﷺ) ላይ ሰለዋት መቼ እና እንዴት እናውርድ</u>

ሰለዋት ማውረድ ማለት ምን እንደሆነ ከላይ አይተናል። አላህ በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ላይ የእዝነት ሰላምታውን እንዲያወርድባቸው እየጠየቅነው ነው። ሱናውን ገጥመን በነብዩ (ﷺ) ላይ ሰለዋት በምን አይነት ሁኔታዎች ላይ ነው የምናወርድባቸው? መስጊድ ስንገባ፣ ከመስጊድ ስንወጣ፣ ከአዛን በኋላ፣ ተሸሁድ (አተሒያቱ ላይ)፣ ዱዐ መክፈቻ፣ ዲን ትምህርት እየተማርን እና እያስተማርን ሐዲሳቸውን ስናነብ፣ ዱዐ ሲጠናቀቅ፣ ጁምዐ ቀን በበለጠ ሁኔታ፣ የዳዕዋ መክፈቻ ላይ የሳቸውን ስም እናነሳለን፣ ጁመዐ ኹጥባ ላይ፣ የሞተ ሰው ላይ ስንሰግድ፣ ወዘተ።

16. <u>ሀሙስ ማታ!</u>

በሃገራችን አንዳንድ አካባቢዎች ብዙ ቤቶች ላይ ሀሙስ ማታ **"የአምዋት ቡና (ለሞቱ ሰዎች የሚፈላ ቡና)"** በማለት **<u>ጫት ተዘርግቶ</u>**፣ ቡና ተፈልቶ፣ እጣን እያጫጫሱ የሚያሳልፉ ሰዎች አሉ። ሌሎች ደግሞ በመስጊድ ደረጃ ሀሙስ ማታ ከመግሪብ እስከ ኢሻ በጀመአ ሰለዋት እናወርዳለን የሚሉም አሉ። ከዚህም አልፈው ሌሊቱን በቂምሃ (በጫት መቃም) የሚያሳልፉት ብዙ ናቸው። በጣም የሚገርመው ቁጭ ብለው በጀመአ ሲሉ የነበረውን "**ሶለዋት**" ብለው የሚጠሩትን **<u>"መርሃባ ነቢ መርሃባ (እንኳን ደህና መጡ ነቢ እንኳን ደህና መጡ!)"</u>** የሚለው ላይ ሲደርሱ ከተቀመጡበት ብድግ የሚሉ መኖራቸው ነው። በሰዓቱ ከሚባሉ የመንዙማ ስንኞች የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

- ✂ **<u>"ነበው ዲጅዋ ዲጂ ነብዮ ዲጅዌ</u>" (በሀደሪኛ)**
- ✂ **<u>"አርሂቡ ነቢ አርሂቡ ነቢ</u>" (በአማርኛ)**
- ✂ **<u>"ግቡልን የተንቢ</u>" (በጉራጊኛ)**

ይህንንም የሚያደርጉት ነብዩ (ﷺ) ይመጣሉ ብለው ስለሚገምቱ ነው። ኢናሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂኡን! ነብዩ (ﷺ) የትም አይመጡም። መዲና ተቀብረዋል። እኛ እሳቸው ላይ ሸሪአ ባዘዘው መልኩ ሰለዋት ስናወርድ መላኢካ ያደርስላቸዋል። ከዚያ ውጭ የትም አይመጡም።

ነብዩ (ﷺ) አይደለም ሞተው በህይወት እያሉ እንኳን ሰው ከተቀመጠበት ሲነሳላቸው አይወዱም ነበር። ያው በዲን ላይ የሚጨመር ፈጠራ መጨረሻው ይህ ነው። ወደ አላህ እቃረባለሁ ብሎ ከአላህ መራቅ እና ቁጣውን መከናነብ። ነብዩ (ﷺ) ***"<u>የእኛ ትእዛዝ የሌለበትን ሰራ የሰራ ሰው ስራው ተመላሽ ነው</u> (ተቀባይነት የለውም)።"*** ብለዋል። በሃገራችን በተለምዶ **"ኽሚስ"** እየተባለ ሀሙስ ለጁሙዐ ሰዎች የሚሰባሰቡበት ምሽት ማስረጃ የማይደግፈው በሶሐባዎች ያልተፈፀመ ተግባር ነው። እንዲያውም ነብዩ

(ﷺ) በሐዲሣቸው **ጁሙዐን ቀኑን በፆም ሌሊቱን በመቆም ከሌሎች ቀናት እንዳትለዩት** ካሉት ማስረጃ ጋር የሚቃረን ነው። [ሙስሊም፡ 1144]

ክፍል ሁለት

በአላህ ፍቃድ በክፍል ሁለት መፀሀፉ በዋናነት የተዘጋጀበት አርእስት ግልፅ ብሎ የሚወጣበት ይሆናል። እሱም አገራችን ላይ ያሉ መንዙማዎች እና መፀሀፍት ላይ የሚገኙ ክህደቶች፣ ሺርኮች፣ በአላህ እና መልክተኛው ላይ የተዋሹ ውሸቶች፣ ተረተረቶች እና መንዙማ ምን ያህል አገራችን ላይ የሙስሊሙን እምነት የሚንዱ ስንኞች እንዳሉት የሚዘረዘሩበት እና በአላህ ፍቃድ ሸሪአዊ መልስ የሚቀርብባቸው ይሆናሉ። እነዚህን መንዙማዎች በዋና ዋና አርእስት ስር ከፋፍያቸዋለሁ። ትኩረት የሚሻቱትን ስንኞች አስምሬባቸዋለሁ።

በአላህ ፍቃድ እነዚህን እና መሰል ከኢስላም ጋር የሚጋጩ ስንኞችን እኛም ተጠንቅቀን፣ ቤተሰባችንን እና ማህበረሰቡን ልናስጠነቅቅ ይገባል።

17. ከአላህ ጌትነት ጋር የሚጋጩ ስንኞች

መፍጠር፣ ህያው ማድረግ፣ መግደል፣ ማብላት፣ ማጠጣት፣ መሾም፣ መሻር፣... የአላህ ብቻ ችሎታዎችና ስልጣኖች ናቸው። እነዚህ መገለጫዎች ተውሒዱ አርኑቡቢያ ማለትም የአላህ የጌትነቱ ተውሒድ አንኳር ነጥቦች ናቸው። ሊሰመርበት የሚገባው ነገር

ቢኖር የመካ ኣጋሪያን በአመዛኙ የአላህን ጌትነት፣ ሁሉን አስተናባሪነት አልካዱም ነበር። የነሱ ከባድ ችግር በአላህ ጌትነት አምነው ነገር ግን አምልኮትን ልክ ለአላህ እንደሚሰጡት ለሌሎች ፍጡርም መስጠታቸው ነው።

በሚያሳዝን ሁኔታ ዛሬ ወገናችን የአላህን የጌትነቱን ስልጣን ሳይቀር ለፍጡር እየሰጠ ነው። መንዙማን እንደምሳሌ ብንወስድ ከአላህ ጌትነት ጋር በሚጋጨ፣ ለብቸኛው ፈጣሪ አላህ ብቻ የሚገባውን መብት ከእርሱ ውጭ ላሉ ፍጡራን በሚሰጡ በርካታ የጥፋት ስንኞች የታጨቀ ነው። አስተዋዮች ያስተውሉ ዘንድ ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት፡-

- **“አላሁመሰሊ አላ ሙሐመዲ፣**
  <u>መግን ነቢ የሁሉ ቀላቢ</u>”
- **“<u>ለካም አንቱ ነሁ ያነቢ</u>፣**
  <u>ለመላው ኸልቅ ቀላቢ</u>፣
  ብትን ያለውን ሰብሳቢ፣ በሶፋ ቡራቅ ጋላቢ”

እውን ነብዩ (ﷺ) የሁሉ ቀላቢ ናቸው? ይሄ የለየለት ቅጥፈት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوْ كَذَّبَ بِـَٔايَٰتِهِۦٓ ۗ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٢١﴾ وَيَوْمَ نَحْشُرُهُمْ جَمِيعًا
ثُمَّ نَقُولُ لِلَّذِينَ أَشْرَكُوٓا۟ أَيْنَ شُرَكَآؤُكُمُ ٱلَّذِينَ كُنتُمْ تَزْعُمُونَ ﴿٢٢﴾ ثُمَّ لَمْ تَكُن فِتْنَتُهُمْ إِلَّآ أَن قَالُوا۟ وَٱللَّهِ رَبِّنَا مَا
كُنَّا مُشْرِكِينَ ﴿٢٣﴾ ٱنظُرْ كَيْفَ كَذَبُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ ۚ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟ يَفْتَرُونَ ﴿٢٤﴾ ﴾ الأنعام: ٢١ - ٢٤

“<u>በአላህም ላይ ውሸትን ከቀጣፈ ወይም በአንቀፆቹ ካስተባበለ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው?</u> <u>እነሆ በደለኞች አይድኑም</u>። ሁላቸውንም የምንሰበስብበትንና ከዚያም ለእነዚያ ለአጋሩት እነዚያ ተጋሪዎች ናቸው ብላችሁ ታሰቧቸው የነበራችሁት ተጋሪዎቻችሁ የት

ናቸው? የምጫበትን ቀን (አስታውሱ)። ከዚያም መልሶቸው በጌታችን በአላህ ይሁንብን አጋሪዎች አልነበርንም ማለት እንጂ ሌላ አትሆንም። በነፍሳቸው ላይ እንዴት እንደዋሹና ይቀጣጥፉት ነበሩት ነገር ከእነሱ እንዴት እንደተሰወረ ተመልከት።" [አልአንዓም፡ 21-24]

ነብዩ (ﷺ) በህይወት በነበሩ ጊዜ አይደለም የሁሉ ቀላቢ የራሳቸውም ቀላቢ አልነበሩም። እሳቸውንም ሆኑ ፍጡራኑን ሁሉ የሚቀልበው፣ ከእርሳቸው በፊትም ይሁን ከእርሳቸው በኋላ ያሉትን ፍጡሮቹን የሚቀልበው አላህ ብቻ ነው። የሁሉ ቀላቢ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَا مِن دَآبَّةٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ إِلَّا عَلَى ٱللَّهِ رِزۡقُهَا وَيَعۡلَمُ مُسۡتَقَرَّهَا وَمُسۡتَوۡدَعَهَاۚ كُلّٞ فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٖ ٦ ﴾ هود: ٦

<u>"በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም ምግቧ በአላህ ላይ ያለ ቢሆን እንጂ። ማረፊያዎንም መርጊያዎንም ያውቃል። ሁሉም ግልጽ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ ነው።"</u> [ሁድ፡ 6]

ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ይላሉ **"<u>አንዲት ነፍስ ሲሳይዋን ተመግባ ሳትጨርስ አትሞትም</u>።"** እስቲ የአላህ ባሪያዎች ሆይ! አላህ በሰጠን ንፁህ አእምሮ እናስበው። እንዴት ብሎ ነው እነዚህ የራሳቸውን ሲሳይ በልተው ጨርሰው የሄዱ ሰዎች ቀብር ውስጥ ገብተው ከስራቸው ተገናኝተው ሲያበቁ **<u>"ዱንያ ስጡን"</u>** እየተባሉ የሚጠየቁት? ሲሳይ የሚጠየቀው ሲሳይ የማያልቅበት አላህ ብቻ ነው።

ሌላ ጉድ ይመልከቱና ህዝባችን ያለበትን ጉድ ይታዘቡ፡-

✂ **"<u>አገር የጀበል፣ ጊዜው የጀበል፣</u>**
<u>ደውላው የጀበል፣ እባክህ ጀበል በል፣</u>
<u>በፍቅሩ ታጠብ ጠጣ ወተቱ</u>"

<u>እዚህ ደግሞ አገር ምድሩ፣ ጊዜው ሳይቀር ሁሉ ነገር ለአቡ ጀበል ተሰጥቷል።</u>

ሁሉ በእጁ የሆነው ጌታ ግን እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ مَا يَمۡلِكُونَ مِن قِطۡمِيرٍ ﴿١٣﴾ ﴾ فاطر: ١٣

"<u>እነዚያም ከእርሱ ሌላ የምትግገዟቸው</u> <u>የተምር ፍሬ ሽፋን እንኳን አይኖራቸውም።</u>"

[ፋጢር፡ 13]

ወገኔ ሆይ! ከላይ ባለመንዙማው **"እባክህ ጀበል በል"** እያለ የሚጎትትህን እንዳትሰማ። መቀመቅ ይከትሃል። "አቡል ጀበል" **<u>ጥቅምና ጉዳት ቀርቶ የተምር ፍሬ ሽፋን የለውም</u>** እያለን ነው የኔም ያንተም የጀበልም ጌታ። ባለ ጀበሉ ይቀጥላል፡-

✂ **"<u>ጥንትም እሱ ነው፣ አሁንም እሱ፣</u>**
<u>ዛሬም ወደፊት እሱ ነው እሱ፣</u>
<u>ይኖራል ነግሶ አለምን ገዝቶ</u>"

ይሄ በምንም መልኩ ህያው የሆነው ፈጣሪ መገለጫ እንጂ የደካማውና ሙት የሆነው አቡል ጀበል መገለጫ አይደለም። እንዲህ አይነቱን የኩፍር ቃላት ላኢላህ ኢልለላህ ከሚል ሰው መስማት እጅጉን ያማል። እንዲህ አይነቱን ፅንፍ የደረሰ ጥፋት የተውሒዱን ሃይማኖት ኢስላምን የሚከተል ሰው በፍቅር ሲያዳምጠው መመልከት ውስጥን ያቆስላል። ሁሉን ቻዩ እና የሁሉ ፈጣሪ አላህ ግን ምን ነበር ያለው?

﴿ لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ يُحۡيِۦ وَيُمِيتُۖ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ﴿٢﴾ هُوَ ٱلۡأَوَّلُ وَٱلۡأٓخِرُ وَٱلظَّٰهِرُ وَٱلۡبَاطِنُۖ وَهُوَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ ﴿٣﴾ ﴾ الحديد: ٢ - ٣

“<u>የሰማያትና የምድር ንግስና የርሱ ብቻ ነው</u>። ህያው ያደርጋል፤ ይገድላልም። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው። እርሱ ፊትም ያለ፣ ኋላም ቀሪ፣ የበላይ፣ ቅርብም ነው። እርሱ ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው።” [አልሐዲድ፡ 2-3]

አቡል ጀበል ካልነበር የተገኘ ነውና ጥንት አልነበረም። ፍጡር ነውና ይሄው ሞቷል። ዛሬም የለም። አላህ ከቀብር እስከሚቀሰቅሰው ድረስም ቂያማ ድረስ አይኖርም። ታዲያ “<u>ይሞራል ነግሶ አለምን ገዝቶ</u>” ማለት ምን የሚሉት ቅጥፈት ነው?!! አይደልም አቡል ጀበል ነብዩ (ﷺ) እንኳን ሞተዋልኮ።

✂ **“የልቅናው እማ አሁን ልፈስረው፣**
<u>የአላህ ሹም እኮ ነው ሸልሞ የፈጠረው</u>፣
<u>በፊት የሰራው ጉድ አሁን ልናገረው</u>፣
<u>የአደም ጭቃ ነው እጁን ያጠቆረው</u>፣
<u>ነበር ያሳመረ ሌሎች ሲያቦኩ</u>፣
አቡል ጀበል ግርማ አለው ለመልኩ”

ኢንና ሊላሂ ወኢንና ኢለይሂ ራጂዑን!! እስቲ አሁን ይሄ ብልግና አይደለም ወይ?!!

﴿كَبُرَتۡ كَلِمَةٗ تَخۡرُجُ مِنۡ أَفۡوَٰهِهِمۡۚ إِن يَقُولُونَ إِلَّا كَذِبٗا ٥﴾ الكهف: ٥

“<u>ከአፎቻቸው የምትወጣው ቃል ምንኛ ከበደች</u>!! <u>ውሸትን እንጂ አይናገሩም</u>።” [አልከህፍ፡ 5]

አላህ ግን አደምን (ዐለይሂ-ስሰላም) በሁለት እጆቹ እንደፈጠረ እንዲህ ሲል ይነግረናል።

﴿ قَالَ يَٰٓإِبۡلِيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسۡجُدَ لِمَا خَلَقۡتُ بِيَدَيَّۖ أَسۡتَكۡبَرۡتَ أَمۡ كُنتَ مِنَ ٱلۡعَالِينَ ٧٥ ﴾ ص: ٧٥

(አላህም) "ኢብሊስ ሆይ! <u>በሁለት እጆቼ ለፈጠርኩት (አደም) ከመስገድ ምን ከለከለህ? (አሁን) ኮራህን? ወይስ (ፊቱኑ) ከትዕቢተኞቹ ነበርክ?"</u> አለው። [ሷድ፡ 75]

አቡል ጀበል አይደለም አደም ሲፈጠር ሊኖር ቀርቶ የራሱንም አፈጣጠር አላየም። ለዚህም ማስረጃችን የሚከተለው የጌታችን አላህ ቃል ነው

﴿ مَّآ أَشۡهَدتُّهُمۡ خَلۡقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَا خَلۡقَ أَنفُسِهِمۡ وَمَا كُنتُ مُتَّخِذَ ٱلۡمُضِلِّينَ عَضُدٗا ٥١ ﴾ الكهف: ٥١

"የሰማያትንና የምድርን አፈጣጠር አላሳየኋቸውም። <u>የነፍሶቻቸውንም አፈጣጠር (እንደዚሁ)</u>። አሳሳቾችንም ረዳቶች አድርጌ የምይዝ አይደለሁም።" [አልከህፍ፡ 51]

ሌላው ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

✂ **"<u>ይመነጥቁታል ያወጡታል ከጭንቅ</u>"**

እውን ከጭንቅ የሚያወጡት እነሱ ናቸው?

﴿ أَمَّن يُجِيبُ ٱلۡمُضۡطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكۡشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجۡعَلُكُمۡ خُلَفَآءَ ٱلۡأَرۡضِۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ قَلِيلٗا مَّا تَذَكَّرُونَ ٦٢ ﴾ النمل: ٦٢

"<u>ወይስ ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል፣ መከራንም የሚያስወግድ፣</u> በምድርም ላይ ምትኮች የሚያደርጋችሁ (ይበልጣልን ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ጥቂትን እንጂ አትገሰፁም?" [አንነምል፡ 62]

✂ **“<u>የቦረናው ጌታ ነው እንደ ጡላጊ፤</u>**
<u>ትንሹን ጠቃሚ ትልቅ አሳዳጊ</u>”

ትንሹን ጠቃሚ ትልቁን አሳዳጊ አላህ ብቻ ነው። አላህ ግን እንዲህ ይላል፦

﴿ قُلِ ٱللَّهُمَّ مَٰلِكَ ٱلۡمُلۡكِ تُؤۡتِي ٱلۡمُلۡكَ مَن تَشَآءُ وَتَنزِعُ ٱلۡمُلۡكَ مِمَّن تَشَآءُ وَتُعِزُّ مَن تَشَآءُ وَتُذِلُّ مَن تَشَآءُۖ بِيَدِكَ ٱلۡخَيۡرُۖ إِنَّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٢٦ ﴾ آل عمران: ٢٦

(ሙሐመድ ሆይ!) በል፦ “የንግስና ባለቤት የሆንክ አላህ ሆይ! <u>ለምትሻው ሰው ንግሥናን ትሰጣለህ</u>። <u>ከምትሻውም ሰው ንግሥናን ትገፍፋለህ</u>። <u>የምትሻውንም ሰው ታልቃለህ</u>። <u>የምትሻውንም ሰው ታዋርዳለህ</u>። መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ (በችሎታህ) ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና።” [አሊ ዒምራን፡ 26]

ይሄ ስንኝ በግልፅ የአላህን መብት አሳልፎ ለቦረናው ሸይኽ እየሰጠ ነው። **ጠቃሚ ጎጂ፣ ሰጪ ነሺ አላህ ብቻ ነው።**

✂ **“<u>ይሁንበት በነሰይድ ዳና</u>፣**
መደሻችን (መደሰቻችን) ይሁን ያለንበት ዘመን፣
ቆሞ ቀር ሆነናል ባለንበት ዘመን፣
<u>እኩሉን ሞሸሩን እንዳንቀር ተርበን</u>”

ከአላህ ተዓምር ውስጥ ወንድ እና ሴትን ማጋባቱ በመካከላቸው ውዴታና መተዛዘንን ማድረጉ ነው። **<u>ነብዩን (ﷺ) እንኳን ትዳር የሰጣቸው አላህ ነው።</u>** ዛሬ ግን ይሄው እዚህ ላይ እንደምናየው **<u>“እኩሉን ሞሸሩን”</u>** ብለው ነብዩን (ﷺ) ዳሩን ሲል፤ ከአላህ ውጭ ይጠይቃሉ። አላህ ብቻ ሊያደርገው በሚችለው ጉዳይ ፍጡራንን መጥራት

ሺርክ እና ኩፍር ነው። የአላህ መልክተኛ (ﷺ) **“ከአላህ ውጭ ያለን እየጠራ የሞተ እሳት ገባ”** ብለዋል።

18. አላህ ከፍጡሮቹ ስልጣኑን አሳልፎ የሰጠው አለን?

የአላህ ጌትነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከላይ አሳልፈናል። አገራችን ላይ ካሉ መንዙማዎች ውስጥ ለምሳሌነት የሚከተሉት አላህ ስልጣኑን ለፍጡራኑ አሳልፎ እንደሰጠ ይዋሻሉ። ጥያቄው አላህ ምን ሆኖ ነው ስልጣኑን ለፍጡራኑ አሳልፎ የሚሰጠው? ጌታችን አላህ ማለት ህያው፣ የማይሞት፣ በራሱ የተብቃቃ ፍጡራኑን የሚያብቃቃ፣ አሸናፊ፣ የማይተኛ፣ የማያንቀላፋ፣ ቂሚ፣ ሻሪ፣ የፍጡራኑ ሁሉ መጠጊያ ነው። አላህ ከእርሱ ውጭ የሚመለኩት በሰማይም በምድርም ምንም እንደማይችሉ፣ ሽርክናም እንደሌላቸው፣ ኣጋዦቹም እንዳልሆኑ፣ እርሱ ከፈቀደ በኋላ ቢሆን እንጂ እንደማያማልዱም እንዲህ ሲል ይነግረናል፡-

﴿ قُلِ ٱدۡعُواْ ٱلَّذِينَ زَعَمۡتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِۖ لَا يَمۡلِكُونَ مِثۡقَالَ ذَرَّةٖ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا لَهُمۡ فِيهِمَا مِن شِرۡكٖ وَمَا لَهُۥ مِنۡهُم مِّن ظَهِيرٖ ٢٢ ﴾ سبأ: ٢٢

“እነዚያን ከአላህ ሌላ (አማልክት ብላችሁ) የምታሰቧቸውን ጥሩ። <u>በሰማያትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንንም ኣይችሉም</u>። <u>ለእነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም</u>። <u>ከእነርሱም ለእርሱ ምንም ኣጋዥ የለውም</u>።”
በላቸው።” [ሰበእ፡ 22]

﴿ وَلَا تَنفَعُ ٱلشَّفَٰعَةُ عِندَهُۥٓ إِلَّا لِمَنۡ أَذِنَ لَهُۥۚ حَتَّىٰٓ إِذَا فُزِّعَ عَن قُلُوبِهِمۡ قَالُواْ مَاذَا قَالَ رَبُّكُمۡۖ قَالُواْ ٱلۡحَقَّۖ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡكَبِيرُ ٢٣ ﴾ سبأ: ٢٣

<u>ምልጃም እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ እርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም።</u> ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጸም ጊዜ (ተማላጆቹ) "ጌታችሁ ምን አለ?" ይላሉ። (አማላጆቹ) "እውነትን አለ፤ እርሱም ከፍተኛው ታላቁ ጌታ ነው" ይላሉ። [ሰበእ፡ 23]

የሚከተሉት ስንኞች ላይ አላህ ስልጣኑን ለፍጡራኑ አሳልፎ እንደሰጠ ተደርጎ ይቀጠፍበታል። አላህ ላይ መዋሸት ደግሞ ከባድ ቅጥፈት ነው።

✂ **"<u>ላንተ ነው በማለት ከውኑን ያስረከበው፣</u>**
<u>ለዚህ ነው ሙሂቡ በዚህ የሚዋከበው።</u>"

እስኪ አላህ ይህንን እንዳለ ምን አሳወቀው?

﴿ أَطَّلَعَ ٱلْغَيْبَ أَمِ ٱتَّخَذَ عِندَ ٱلرَّحْمَٰنِ عَهْدًا ﴿٧٨﴾ ﴾ مريم: ٧٨

<u>"ሩቁን ምስጢር አወቀን ወይስ እሱ ከአርረሕማን ዘንድ ቃል ኪዳን ይዟል?"</u> [መርየም፡ 78]

✂ **<u>"ለኸልቁ ገበያ መድሀኒት ነበር</u>፣**
<u>የቸገረው ሄዶ የለውም ማፈር</u>፣
<u>ከሀያቱ በልጧል ውለታው በቀብር</u>፣
<u>ወዲያልኝ የሱ ጉድ አያልቅም ይቅር</u>"
✂ **"<u>ጌታው</u> ሰይድ አህመድ የደባቱ ኑር፣**
ዶላል ያስፈቀተው የዲኑ ጨረር፣
<u>ስፍር ቁጥር የለው ስንቱ በእጁ ሻረ</u>፣
አላህ ዘንድ ነበር ተናግሮ የማያፍር፣
<u>ቢያለብስም ቢገፋም ቢያደኸይ ቢያከብር</u>፣

<u>ይግባኝ የለበትም በፈረደው አምር፣</u>
<u>ተብሎ አላህ ዘንዳ በሻህው አብሽር”</u>

እንግዲህ ተመልከቱ የአላህ ባሪያዎች ሆይ! እነዚህ ስንኞች ለሙታን የተገጠሙ ናቸው። ይሄ ፍጥጥ ባለ መልኩ ወደ ሙታን አምልኮ መጣራት ነው። የሰው ልጅ ከሞተ ለሌላው ቀርቶ ለራሱም አይሆንም። አገልግሎቱ የማይቋረጥ ቅሪት ከተወ ብቻ ነው ምንዳው የማይቋረጠው። ነብዩ (ﷺ) ደግሞ እንዲህ ሲሉ ነው ያስተማሩት፡- **“የአደም ልጅ ሲሞት ስራው ይቋረጣል።”** [ሙስሊም፡ 2682] እዚህም ላይ የራሱን መልካም ስራ ለመጠቆም እንጂ ለሌሎች ይደርሳል ለማለት አይደለም።

ማልበስ ማጉረስ ማከበር፣ ማደህየት የአላህ ስልጣን ብቻ ነው። አላህ እንዲህ ይላል **“<u>ባሪያዎቼ ሆይ! ሁላችሁም የተራባችሁ ናችሁ እኔ ያበላሁት ሲቀር። አብላን በሉኝ አበላችኋለሁ። ባሪያዎቼ ሆይ! ሁላችሁም የታረዛችሁ ናችሁ እኔ ያለበስኩት ሲቀር። አልብሰን በሉኝ አለብሳችኋለሁ።</u>”** ኢማሙ ሙስሊም ዘግበውታል።

<u>በፈረደው እና በሚሰራው ነገር ይግባኝ የሌለበት አላህ ብቻ ነው</u>። አላህ አይደለም ይህን ግለሰብ ውዱን ነብይ (ﷺ) እንኳን ሞት እስኪመጣቸው ድረስ አላህን እንዲገዙት እንጂ በሌላ አላዘዘም።

✂ **“ጀማሉል አለም ﷺ፣ ወደ ጀይላኔ ቢወረውረው፣**
<u>ለውሀል መህፉዝን አስመረመረው፣</u>
<u>በአለም ተሹሞ[4] ብዙ ጉድ እያስወገዱ፣</u>

---

[4]ሱፍዬች ዘንድ አለምን የሚያስተዳድሩ 4 ቁጥቦች አሉ ብለው ያምናሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ ዐብዱል ቃድር ጀይላኒ ነው ይላሉ፡፡ ይህ አባባላቸው ክህደት ነው፡፡ ምክንያቱም ብቸኛ የፍጥረተ አለሙ አስተዳዳሪ እና አስተናባሪ ፍጥረቶቹን ያስገኘው አላህ ብቻ ነው፡፡

በባግዳድ ምድር ﷺ ፣ እሳት ነው ፍቅር”

ይሄ በጣም ከባድ አባባል ነው። ይሄ በኢስላም ላይ የሚፈፅ ከባድ ቅጥፈት ነው።

19. <u>ከአላህ አምላክነት ጋር የሚጋጩ ሰንኞች</u>

የአላህ አምላክነት ማለት እኛ ፍጡሮቹ ለእርሱ የምንፈፅመው ነው። አላህ ልክ በጌትነቱ ሁሉ አንድ እንደሆነው በአማላክነቱም እንደዚሁ አንድ ነው። እኛ የእሱ ባሪያዎች የእሱን ትእዛዝ በማክበር፣ የነብያትን ፈለግ በመከተል <u>**ፀሎታችንን፣ መመካታችንን፣ ፍራቻችንን፣ መተናነሳችንን፣ ውዴታችንን፣ ስግደታችንን፣ እርዳታን፣ ህይወታችንን፣ ሞታችንን እና ሌሎችንም አምልኮዎቹ ለእርሱ ብቻ ነው ልንፈፅም የሚገባን**</u>። ከእርሱም ውጭ ላለ ለማንኛውም አካል አምልኮን ልንፈፅም አይገባም። ከዚህ በታች ያሉት የቁርአን አንቀፆች አምልኮ ለአላህ ብቻ ማድረግ እንደሚገባን፣ የሺርክን አደጋ፣ የሙሽሪኮችን መጨረሻ የሚገልፁ ይሆናሉ። ጌታችን አላህ እንዲህ ይላል

﴿ وَٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَلَا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ ٣٦ ﴾ النساء: ٣٦

<u>አላህንም በብቸኝነት ተገዙ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ</u>።

﴿ وَأَنَّ ٱلۡمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدۡعُواْ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدٗا ١٨ ﴾ الجن: ١٨

እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውሰጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም)።

﴿ قُلۡ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحۡيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٢ ﴾ الأنعام: ١٦٢

"ሰግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው" በል።

﴿ لَا شَرِيكَ لَهُۥۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرۡتُ وَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ﴿١٦٣﴾ ﴾ الأنعام: ١٦٣

"ለእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ" (በል)።

የአላህ ውድ ባሪያ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ለራሳቸው ጥቅም ማምጣት፣ ከራሳቸው ላይ ጉዳትን መከላከል አይችሉም። የሩቅንም አያውቁም። አላህ ነብዩን (ﷺ) ይህን አስመልክቶ ግልፅ እንዲያደርጉ እንዲህ ሲል ያዛቸዋል

﴿ قُل لَّآ أَمۡلِكُ لِنَفۡسِي نَفۡعٗا وَلَا ضَرًّا إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۚ وَلَوۡ كُنتُ أَعۡلَمُ ٱلۡغَيۡبَ لَٱسۡتَكۡثَرۡتُ مِنَ ٱلۡخَيۡرِ وَمَا مَسَّنِيَ ٱلسُّوٓءُۚ إِنۡ أَنَا۠ إِلَّا نَذِيرٞ وَبَشِيرٞ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ﴿١٨٨﴾ ﴾ الأعراف: ١٨٨

"<u>አላህ የሻውን በሰተቀር ለእራሴ ጥቅምንም ጉዳትንም ማምጣት አልችልም</u>። <u>ሩቅንም (ምስጢር) የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ ነበር</u>። <u>እኔ ለሚያምኑ ሕዝቦች አስፈራሪና አብሳሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም</u>" በላቸው።
[አልአዕራፍ፡ 188]

﴿ وَإِن يَمۡسَسۡكَ ٱللَّهُ بِضُرّٖ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَۖ وَإِن يَمۡسَسۡكَ بِخَيۡرٖ فَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ﴿١٧﴾ ﴾ الأنعام: ١٧

"<u>አላህም በጉዳት ቢነካህ ለእርሱ (ለጉዳቱ) ከእርሱ በቀር ሌላ አስወጋጅ የለም</u>። <u>በበጎም ነገር ቢነካህ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው</u>።" [አልአንዓም፡ 17]

﴿ لَهُۥ دَعۡوَةُ ٱلۡحَقِّۖ وَٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ لَا يَسۡتَجِيبُونَ لَهُم بِشَيۡءٍ إِلَّا كَبَٰسِطِ كَفَّيۡهِ إِلَى ٱلۡمَآءِ لِيَبۡلُغَ فَاهُ وَمَا هُوَ بِبَٰلِغِهِۦۚ وَمَا دُعَآءُ ٱلۡكَٰفِرِينَ إِلَّا فِي ضَلَٰلٖ ١٤ ﴾ الرعد: ١٤

"እውነተኛ አምልኮ ለአላህ ብቻ ነው። እነዛ ከአላህ ሌላ የምትጠሯቸው በምንም ነገር ምላሽ አይሰጧችሁም። ከአላህ ሌላ የሚያመልኩ ሰዎች ምሳሌያቸው እጁን ወደ ውሀ እንደሚዘረጋ ወደ አፉ ለማድረስ ፈፅሞ ማድረስ አይችልም።" [አርረዕድ፡ 14]

አላህ አሁንም ለሰው ልጆች አዛኝ ነውና በሚገባቸው መልክ ከእርሱ ውጭ የሚመለኩት እንደ አምላኪዎቻቸው ፍጡር መሆናቸውን እንዲህ ሲል ይነግረናል

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ عِبَادٌ أَمۡثَالُكُمۡۖ فَٱدۡعُوهُمۡ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١٩٤ ﴾ الأعراف: ١٩٤

"እነዛ ከአላህ ውጭ የምትጠሯቸው እንደናንተው ባሪያዎች ናቸው ጥሯቸው እሰኪ በእውነት እሺ ይበሏችሁ።" [አእራፍ 194]

﴿ حُنَفَآءَ لِلَّهِ غَيۡرَ مُشۡرِكِينَ بِهِۦۚ وَمَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَكَأَنَّمَا خَرَّ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَتَخۡطَفُهُ ٱلطَّيۡرُ أَوۡ تَهۡوِي بِهِ ٱلرِّيحُ فِي مَكَانٖ سَحِيقٖ ٣١ ﴾ الحج: ٣١

"ለአላህ ታዛዦች በርሱ የማታጋሩ ሆናችሁ (ከሀሰት ራቁ) በአላህም የሚያጋራ ሰው ከሰማይ እንደ ወደቀና በራሪ እንደምትነጥቀው ወይም ነፋስ እርሱን በሩቅ ሰፍራ እንደምትጥለው ብጤ ነው።" [አልሐጅ 31]

የሚከተሉት ስንኞች መንዙማ ባዮች የአላህን ሙበት (አምልኮ) ከእሱ ላይ አንስተው ለነብዩ (ﷺ) እና ለሌሎች ፍጡራን የሰጡበት ነው። አንባቢ እነዚህን

የመንዙማ ስንኞች ብዙ ቦታ እንደሚሰማቸው እጠብቃለሁ። የኢስላም አካልም ተደርገው ይወሰዳሉ። ነገር ግን እንዲህ ዝርዝር ብለው ሲቀመጡ ምን ያህል ከምንወደው ጌታችን ጋር ሊያጣሉን እና ሊያራርቁን የሚችሉ በኢስላም ስም የመጡ ግን የሰይጣን ወጥመዶች መሆናቸውን እንረዳለን።

✂ **“በዝቶብኛልና አያሌ ነገር፣**
<u>አቤት ብየ ልጩህ እባሮቹ በር፣</u>
<u>ቀልቤን ወዳሳቸው አድርጌ ሰንዘር፣</u>
<u>አቤት ጮህኩባችሁ ጌቶቼ ዱስቱር፣</u>
<u>ከሙስጠፋ ይገፍ እስከ አቡል በሸር፣</u>
<u>አምቢያ ሙርሰልም አንድ እንኳን ሳይቀር”</u>

አማኝ የፈለገውን ያህል ችግር ቢበዛበት ሁሉን ነገሩን እንዲያገራለት የሚለምነው ሁሉን ቻይ የሆነውን አጋር የሌለው አንድ አምላክ አላህ ብቻና ብቻ ነው።

ተመልከቱ ይህንን ቆሻሻ ንግግር **“አቤት ብዬ ልጩህ እባሮቹ በር”** ሁሉም ባሪያዎች ከአላህ ከጃይ ደሃዎች ናቸው። ቢጮህባቸው ምንም ማድረግ የማይችሉትን በመለመን ሁለት አገር መከሰር ይልሃል ይህ ነው። **<u>“አቤት ጮህኩባችሁ ጌቶቼ ዱስቱር (ሁለንተናችንን ለእናንተ ተገዢ አድርገናል)”</u>** ሱብሃነላህ! ሁለንተናችንን አምልኮን ለእርሱ በማጥራት ልንሰጥ የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው። ነብያት ምን መልክት ይዘው እንደመጡ አያውቅምን? አኡዙቢላሂ ነብያት አይደለም ከአላህ ሌላ ሊያመለኩ፣ እነሱ እራሳቸው ከአላህ ሌላ አታምልኩ አላህንም በብቸኝነት አምልኩ በማለት ላይ ነው ህይወታቸውን ያሳለፉት።

ከዚህ ሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ታላቁን የተውሒድ አስተማሪ ነብዩን (ﷺ) እከተላለሁ እያሉ እሳቸው ይዘውት የመጡትን ዋና መልክት ማንኮታኮታቸው ነው።

✂ **“<u>በዘመን ያላችሁ ሳዳቶች አኽያር፣</u>**
<u>ቀኝ እጇን ጨብጡኝ ወድቄ እንዳልቀር፣</u>
<u>ሺሊላህ ጌቶቼ አርሂቡ ዱስቱር፣</u>
<u>መቼም ያለናንተ ሁሉም አያምር፣</u>
<u>በናንተ የሸሸ ምንም አያፍር፣</u>
<u>ጌቶቼ አትለፉኝ አደቤም ባያምር፣</u>
<u>አደበቢስ ቡልሀ እንደኔ ቢኖር፣</u>
<u>ባሪያ ሲባል ማጥፋት እለት ነው እድር፣</u>
<u>ለናንተ ይገባል ያጠፋን መማር</u>።”

ከአላህ ውጭ የሚለምን እማ ወድቆ የቀረ ውዳቂ ነው። ሁለት አገር ባርያዎቹን ጥሎ የማይጥለው አላህ ብቻ ነው። አዎን እንዲህ አይነት በሺርክ የተሞላ መንዙማን የሚል ሰው ከኢብራሂም መንገድ ያፈነገጠ ቂል እና አደበ ቢስ ነው። ከአላህ ውጭ ወንጀልን የሚምር የለም። የስነስርዓት ባለቤት የሆኑት ነብዩ (ﷺ) ጌታችንን አላህ እንዲህ ሲሉ ምህረትን ይለምኑታል

“አላህ ሆይ! <u>ነፍሴን ብዙ በደል በድያለሁ</u> <u>እነሆ ካንተ ውጭ ወንጀልን የሚምር የለም ማረኝ</u>”

✂ **“አልሀምዱሊላሂ ይመስገን ገፋር፣**
<u>ቀልቤን ያዞረልኝ ወደናንተ በር፣</u>
<u>በናንተ የሸሸ ያገኘል ሹም ሽር፣</u>
<u>ሊለግስ ነው መሰሌ ዳመናው ዟዟረ፣</u>
<u>የስልካችሁ ንባብ ይሰማ ጀመረ</u>።”

አላህ ልባችንን ወደሱ እንድናዞር ነው ያዘዘን። አላህ በሺርክና በኩፍር አያዝም። መንዙማ ባዩ አላህን እየወነጀለ ነው። አላህ ወደ እሱ እንድንሸሽ ነው ያዘዘን።

መሾም መሻር የአላህ ስልጣን ብቻ ነው። ሰጪውም ለጋሹ የሁሉ ባለቤት አላህ ብቻ ነው።

✂ **“<u>ሁሉም ባንድ ሆነው ከሙስጠፋ ጋር፣</u>**
<u>ዛሬ ይድረሱልን ላገኘን ችጋር”</u>

ነብዩ (ﷺ) እና የተቀሩት ነብያት በጠቅላላ ከመላእክቶች ከጂኖች ጭምር ቢሰበሰቡ ለማንም ሊደርሱ አይችሉም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَإِن يَمۡسَسۡكَ ٱللَّهُ بِضُرّٖ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَۖ وَإِن يُرِدۡكَ بِخَيۡرٖ فَلَا رَآدَّ لِفَضۡلِهِۦۚ ﴾ يونس: ١٠٧

“<u>አላህም ጉዳትን ቢያደርስብህ ከርሱ ሌላ ለርሱ ገላጭ የለውም። በጎንም ነገር ቢሻልህ ለቸሮታው መላሽ የለውም።</u>” [ዩኑስ፡ 107]

✂ **“<u>እብድ ብሎ እስኪሉ ቃድር፣</u>**
<u>እርዳታው አይውል አያድር።”</u>

አላህ ደግሞ ከሱ ውጭ የሚጠሩ አካላት እንኳን እንዲህ ፈጣን መልስ ሊሰጡ ይቅርና ዘላለም መልስ መስጠት አይችሉም። እንዲህ አይነት ዝንጉዎችን እንደሚማፀን ሰው ጠማማ የለም ይላል። ይሄውና፡-

﴿ وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّن يَدْعُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن لَّا يَسْتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَـٰمَةِ وَهُمْ عَن دُعَآئِهِمْ غَـٰفِلُونَ ﴿٥﴾ ﴾ الأحقاف: ٥

"<u>እሰከ ትንሳኤ ቀን ድረስም ለርሱ የማይመልሰለትን</u> ከአላህ ሌላ ከሚጣራ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማነው? <u>እነርሱም ከጥሪያቸው ዘንጊዎች ናቸው</u>።" [አልአሕቃፍ፡ 5]

✂ **<u>"ታመን ነበር ፈወሱን፣</u>**
<u>ተርበን ነበር አጎረሱን፣</u>
<u>ታርዘን ነበር አለበሱን፣</u>
<u>ነብዩ የኛ ወለላ፣</u>
<u>የፍጡራን ሁሉ ጥላ፣</u>
<u>ጨለማ ውስጥ ላሉ ብርሀን፣</u>
<u>በሽርክ ለተጎሳቆሉ ኢማን፣</u>
<u>ለተሰቃዩ መጠጊያ፣</u>
<u>ለዋለሉት ሁሉ መርጊያ፣</u>
<u>በርሳቸው ጭንቀት በረካ፣</u>
<u>ዓለም በእስልምና ፈካ።"</u>

የታመመን የሚያድነው አላህ ነው። የተራበን የሚያጎርሰው አላህ ነው። የታረዘን የሚያለብሰው አላህ ነው። አላህ እንዲህ ይላል **"ሁላችሁም የተራባችሁ ናችሁ እኔ ያበላሁት ሲቀር። አብላን በሉኝ አበላችኋለሁ። ሁላችሁም የታረዛችሁ ናችሁ እኔ ያለበስኩት ሲቀር። አልብሰን በሉኝ አለብሳችኋለሁ"**። የፍጡራን ሁሉ መጠጊያ አላህ ነው።

አላህ የሰማያትና የምድር አብሪ ነው። ጨለማ ውስጥ ያሉትን በሺርክ የተጎሳቆሉትን ወደ ብርሃኑ የሚመራው አላህ ብቻ ነው። የባርያዎች ልብ የሚገለባብጠው፣ የዋለሉትን በፍቃዱ የሚያረጋው አላህ ብቻ ነው።

- “አብሽር ወንድሜ ግባ በቶሎ፣
  ማነው ያፈረው ያነቢ ብሎ”
- “አንቱን ጠርቼ ምን አጥቼ፣ ልሙት ፈንድቼ ልዮትና፣
  አህመድ ሙሽራ የመዲና”
- “የቦረናው ደግየ፣ እርዱኝ አባብየ”
- “ሰለፍም ኸለፍም ማወረአል ባህር፣
  በሁለም ሸሸሁኝ አንድ እንኳን ሳይቀር፣
  ከዛፍ ከቅጠሉ በዝቶብኛል ነውር፣
  እሜዳው ላይ ሆኜ ወድቄ በዱር፣
  መግቢያ በር አጥቼ ታግቼ ባጥር፣
  አልሄድ ወደፊት ወደኋላ አልበር፣
  በቀኝ በግራየ እሳት ገደል ባህር፣
  አቤት ጠራኋችሁ ጌቶቼ ዱስቱር፣
  ረዳቴ ማንነው ከናንተ በቀር”
- “እኚህ የእኛ ወንድሞች ብዙ ነው ሲርራቸው፣
  እኚህ የእኛ ወንድሞች ሀያል ነው ትርፋቸው፣
  እኚህ የእኛ ቅምጥሎች እኚህ የእኛ ሉሎች ሃያል ነው ትርፋቸው፣
  ለቸገረን ሁላ ዛሬ ጠራናቸው፣
  በአምስት ተግዝቶ እልፍ አእላፍ ትርፋቸው።”
- “የአርባው ልጅሁ፣ ቆሚል ከደጅሁ፣
  ስጡት በእጅሁ፣ ከእዛ ከጉርጅሆ (ከካዝናዎ)”
- “ጀሚእ አውሊያ ሁላ ወልዮቹ ሁሉ፣
  በወራት ያላችሁ ወራት የኳላችሁ፣
  ቸግሮናል እና እርዱን እባካችሁ፣
  ለታመመው ወራት መድሃኒት ይዛችሁ፣

<u>ታጥቀን ተሸምረን ዛሬ ጠራናችሁ፣</u>
<u>መቼም ለእርዳታ ነው ጀሊል ሲፈጥራችሁ።”</u>

✂ **“<u>እኝህን ሳዳቶች ድረሱ አንበላቸው</u>፣**
እሱ ወደደና እሱ መረጣቸው፣
<u>እመሀባው ባህር ሺህ አመት አስዋኛቸው</u>፣
እሱ ወደዳቸው በፊት ሳይሰራቸው፣
ዩሂቡሁም ወዩሂቡነሁ አላቸው ጀባሩ፣
<u>አቤት እርዱኝ ይላል የቤት ልጅ አሸከሩ</u>፣
<u>በናንተ የሸሸ የቂን ነው ማማሩ</u>፣
<u>ጥላቸው ጠባቂ በሁለት አገር</u>”

✂ **“የፍቅርህን ጥም አይበርድም በውሃ፣**
አንተን የወደደ አይባልም ደሃ፣
<u>ትረዳ የለም ወይ ከየትስ በረሃ</u>፣
ሊጋባ ነህ አሉ ያረሱል ያጣሃ”

እነዚህን አካላት የሚጣራ ሁሉ ያለጥርጥር ጠላት ነው እያፈራ ያለው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَإِذَا حُشِرَ ٱلنَّاسُ كَانُواْ لَهُمۡ أَعۡدَآءٗ وَكَانُواْ بِعِبَادَتِهِمۡ كَٰفِرِينَ ٦ ﴾ الأحقاف: ٦

“ሰዎችም በተሰበሰቡ ጊዜ ለነሱ ጠላቶች ይሆናሉ። እነሱን መገዛታቸውንም ከሃዲዎች ይሆናሉ።” [አልአሕቃፍ፡ 6]

ነብዩን (ﷺ) በዘመቻዎቻቸው፣ በችግሮቻቸው ሲረዳቸው የነበረው አላህ ብቻ ነው። እርዳታን ሲለምኑ የነበረውም ከሱ ብቻ ነበር። ዛሬ “ከኛ ወዲያ ነብዩ (ﷺ) ወዳጅ

ላሳር" የሚሉ አካላት ግን በሸሪዐቸው ላይ ሸፍተዋል። **<u>እርዳታ የሚጠየቀው ከፍጡራኑ ሁሉ መጠጊያ ከአንድ አላህ ብቻና ብቻ ነው።</u>** ሱረቱል ፋቲሃ ላይ **<u>"አንተን ብቻ እናመልካለን። በአንተም ብቻ እንታገዛለን"</u>** እያልን ቃል ከገባን በኋላ ቃላችንን ብናፈርስ ተጎጂዎቹ እኛው ነን።

ኢና ሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂኡን። እስኪ የተውሒዱን አስተማሪ ነብዩን (ﷺ) የተከተለ ሰው፣ የተውሒዱን ሃይማኖት ኢስላምን የመረጠ ሰው እንዴት ብሎ ከአላህ ውጭ በዚህ መልኩ ይጣራል? "**<u>ረዳቴ ማን ነው ከናንተ በቀር?"</u>**፣ **<u>"በናንተ የሸሸ የቂን ነው ማማሩ"</u>**፣ **<u>"አቤት እርዱኝ ይላል የቤት ልጅ አሸከሩ"</u>**፣ **<u>"ለቸገረን ሁላ ዛሬ ጠራናችሁ"</u>**፣ **<u>"በሁሉም ሸሸሁኝ አንድ እንኳን ሳይቀር"</u>**

ይህን የሺርክ ዶፍ የሚያዘንብ ሰው **<u>"በአንተንም ብቻ እንታገዛለን"</u>** እያለ ዘወትር በየሶላቱ የሚገባውን ቃል ኪዳን እያፈረሰ ነው።

"በናንተ የሸሸ የቂን ነው ማመሩ" ይህም ሺርክ ነው። የሚሸሸው ወደ አላህ ብቻ ነው። ከአላህ ውጭ መሸሻ የለም። አላህም "**<u>ወደ አላህ ሽሹ</u>**" ብሏል። [አዝዛሪያት፡ 50]

✂ <u>ጠዋትም ማታ ጀበል ወትውቱ</u> (አጥብቃችሁ ጠይቁ)

ሺህ ጊዜ ቢወተውት የሞተ ፍጡር አይሰማውም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِن تَدۡعُوهُمۡ لَا يَسۡمَعُواْ دُعَآءَكُمۡ وَلَوۡ سَمِعُواْ مَا ٱسۡتَجَابُواْ لَكُمۡۖ وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يَكۡفُرُونَ بِشِرۡكِكُمۡۚ وَلَا يُنَبِّئُكَ مِثۡلُ خَبِيرٖ ١٤ ﴾ فاطر: ١٤

“ብትጠሯቸው ጥሪያችሁን አይሰሙም። ቢሰሙም ኖሮ ለእናንተ አይመልሱላችሁም። በትንሣኤም ቀን (እነርሱን በአላህ) ማጋራታችሁን ይክዳሉ። እንደ ውስጠ ዐዋቂው ማንም አይነግርህም።” [ፋጢር፡ 14]

✂ **“የአበራ ሙዝ አባት[5] የማይደፈር፣**
<u>አቤት ይታይልኝ ምነው የኔም ዱር፣</u>
<u>ዙሩልኝ ጌቶቼ በአውን በነስር፣</u>
<u>ከጃችሁ ከጅየ ቆሜያለሁ ከበር፣</u>
<u>በናንተ የሸሸ ምን ጊዜም አያፍር፣</u>
<u>ሀጃየን አውጡልኝ በዚሂር በሲር”</u>

የአብሬት ሸይኽ የደርግ መንግስት አፍኖ ወስዷቸው ይሄው እስካሁን ድረስ ያሉበት አይታወቅም። ደርግ እንደገደላቸው ይነገራል። እዚህ መንዙማ ላይ **<u>“የማይደፈር”</u>** ሲል ይጠራቸዋል። እውነታው ግን ሃይማኖት የለም የሚለው የሶሻሊዝም ተከታይ የነበረው ደርግ ወስዶ እርምጃ በመውሰድ ስንት ሰው እያመለካቸው ደፈራቸው።

ታድያ እንዴት ይሆን ከደርግ እራሳቸውን ማስጣል ያልቻሉትን የአብሬት ሸይኽ **“የማይደፈር”** የሚሏቸው **“ድረሱልን”** እያሉ የሚማፀኗቸው? ቢችሉ ከሌላው ቀድሞ ለራሳቸው በተረፉ ነበር። **“ከራስ በላይ ንፋስ”** ይላል ያገር ሰው።

---

[5] የአበራ ሙዝ አባት በመባል የሚታወቁት የአብሬት ሸይኽ ሁለተኛው ናቸው። ለእኝህ ግለሰብ እራሳቸውን ታመው በተኙበት ከሙሪዳቸው (ከተከታያቸው) አንዱ ሰባት ጊዜ እሳቸው የነበሩበትን ቤት ዞሮ **<u>“ፊዳ ልሁን እኔ”</u>** በማለት **<u>እራሱን አርዶ ገድሏል</u>**። በሸይኹ ላይ ከባባድ ድንበር ማለፎች ሰዎች ሲፈፅሙ ይታያል። በተለይ ጉራጊኛ ቋንቋ የሚችሉ የተውሒድ ተጣሪዎች አብሬት አካባቢ የሚሰራው ከባድ ሽርክ ሊያስጠነቅቁ ግድ ይላቸዋል።

“ዱርር” ማለት ጉዳት ማለት ነው። ጉዳታችንን እንዲያነሳልን የምንጠይቀው አላህን ብቻ ነው። ይህ ነው የነብያት አስተምህሮት። ብዙ መከራዎችን ስላስተናገዱት ነብዩላህ አዩብ (ዐለይሂ-ስሰላም) አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَيُّوبَ إِذْ نَادَىٰ رَبَّهُۥٓ أَنِّي مَسَّنِيَ ٱلضُّرُّ وَأَنتَ أَرْحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ﴿٨٣﴾ ﴾ الأنبياء: ٨٣

“አዩብንም ጌታውን “<u>እኔ መከራ አገኘኝ አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ</u>” ሲል በተጣራ ጊዜ (አስታውስ)።” [አልአንቢያእ፡ 83]

“<u>አውን</u>” “እርዳታ” ማለት ነው። **“<u>ነስር</u>”** ማለት ደግሞ “ድል” ማለት ነው። ሁለቱንም የሚሰጠው አንድየው ጌታ ብቻ ነው

- **“የሀድራ ጦያራ ይዞ የሚበር፣**
  <u>ሲጠሩት ፈጣን ነው ቶል የሚሀድር</u>፣
  <u>ተምኪን የተሰጠው ዚሂር ወባጢን</u>፣
  <u>እኔ ያለሁበት እከጀላ በር</u>፣
  <u>ቀድሬም አያደርሰኝ መቃም ለመቁጠር</u>፣
  <u>ስንቱን አሳደገው ገና በነዞር (በእይታ)</u>፣
  ፈይዱ ከአፍ ሲፈልቅ ይዐጂብ ነበር፣
  እንኳን ሰው መላኢካ ያደምጠው ነበር።”
- **“<u>አንቱን የሚጠራ እሱ ልቡ ጠራ</u>፣**
  <u>የለበት መከራ አኼራ ሲጥጠራ</u>”

ለጭንቅ ለችግር የሚጥጠራው አላህ ብቻ ነው። አላህን ትቶ ሌላን የሚጠራ ልቡ በሺርክ የቆሸሸ ነው። ከአላህ ውጭ ያለን እየጠራ የሞተ መኖርያው እሳት እንደሆነ ነብዩ (ﷺ) ነግረውናል።

✂ **“እንዳንቱ የሚሆነኝ መቼም አላገኝ፣**
ዘይኔ ቅረቡኝ ጣል አታድርጉኝ”

✂ **“ካንቱ ጋር የዋለ ምንኛ ታደለ፣**
ነቢ ነቢ እያለ ጭንቀቱ ቀለለ፣
እኔም ልጥራዎት ጨንቆኛልና፣
ያምስኪ መዲና ጋየተል ሙና”።

✂ **“ይጣራል ይጮሃል የናንተው ለፍላፊ፣**
የሊበኖቹ ልጅ ሙሀመድ ሻፊ፣
በዱንያም በአኼራም ሁኑልን ደጋፊ”

እውነት ይሄ ለፍላፊ ያለመውን ያገኛል? ሃያሉ ጌታ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَيُشْرِكُونَ مَا لَا يَخْلُقُ شَيْئًا وَهُمْ يُخْلَقُونَ ﴿١٩١﴾ وَلَا يَسْتَطِيعُونَ لَهُمْ نَصْرًا وَلَا أَنفُسَهُمْ يَنصُرُونَ ﴿١٩٢﴾ ﴾ الأعراف: ١٩١ - ١٩٢

“ምንም የማይፈጥሩትንና እነርሱም የሚፈጠሩትን (በአላህ ላይ) ያጋራሉን! <u>ለእነርሱም መርዳትን የማይችሉትን ነፍሶቻቸውንም የማይረዱትን (ያጋራሉን?!)</u>” [አልአዕራፍ፡ 191-192]

✂ **“<u>ና በሉት ኸይረል ወራ፣</u>**
<u>ሳልሞት ሳልሄድ አኼራ፣</u>
<u>ያቺን ረውዳ ዚያራ፣ የጀነትዋን አርዴ”</u>

✂ **“<u>ካልመጣሁኝ መዲና፣</u>**
<u>እኔስ የለኝም ጤና፣</u>
<u>እንድሆንሎት ደህና፣ ቶሎ ጥሩኝ አህመዴ፣</u>

<u>ኒዛሙል መደዴ</u>”

✂ **“<u>ዘይኔ ይበቃናል ኑ በሉን መዲና</u>፣**
ሀይ እንድናደርገው ሁሌ የርሶን ሱና”

✂ **“<u>ቀልቤ እኮ አንቱ ጋር ነው፣</u>**
<u>ፍላጎቱ ረውዳ ነው፣</u>
<u>ዘይኔ ና በሉት ፈጥነው፣ የቀረውን ጀሰዴን</u>”

✂ **“መካና መዲና በእሳትና በውሃ ቢታጠርም፣**
<u>እርሶ ይጥሩን እንጂ አንቀርም</u>።”

✂ **“ሃቢቢ ሃቢቢ ሃቢቢ፣ ሃቢቢ ሃቢቢ ሃቢቢ፣**
<u>መዲና ና ይበሉኝ</u>”

ነብዩ (ﷺ) ወደመቃብር ከገቡ በኋላ ይህን የማድረግ ስልጣኑ አላቸውን? በጭራሽ!! ስልጣን እና ድርሻ የላቸውም። አለምን ማስተናበር ህያው የሆነው የማይሞተው አላህ ስልጣን ብቻ ነው።

✂ **“የፍቅር ነጋሪ ዝም ብየ ልምጣ፣**
እባካችሁ ይቅር ሌላው ሀተታ፣
<u>ጠዋትም ማታ ጀበል ወትውቱ</u> (አጥብቃችሁ ጠይቁ)”

ምንም አይነት ሃተታ፣ ምንም አይነት ውትወታ አይፈይድም። ከኢስላም አምስቱ ማእዘናት አንዱ ሐጅ ነው። ነብዩ (ﷺ) ያስተማሩት **“የቻለ ሰው ቤቱን ይጎብኝ”** ብለው ነው እንጂ **“ያልቻለ ሰው እኔን ይማፀን”** ብለው አይደለም። ውትወታችን ሊሆን የሚገባው ወደ ሁሉን ቻዩ ጌታ ነው።

✂ **“የአላህ አፈ ንጉስ የአላህ ቢተወደድ፣**
ኧረ የት ይገኛል እንደ ሙሐመድ፣

<u>ወዳጅ የሚረዳው ሲገቡ በላህድ (በቀብር ውስጥ)</u>”

✂ **“እንተ የጠይባው ነጋዴ፣**
ሰላም በልልኝ አህመዴን፣
አንቱ የጅብሪል ጓደኛ፣
<u>አትርሱን ቀብር ስንተኛ</u>”

ቀብር ስንተኛ እራሳችን በነፍስ ወከፍ ለተጠየቅነው ጥያቄ መልስ እንሰጣለን እንጂ ነብዩ (ﷺ) ለማንም ቀብር ውስጥ ምንም ማድረግ አይችሉም። እያንዳንዱ ሰው ቀብር ውስጥ መልካምም ይሁን መጥፎ የራሱን ስራ ያገኛል።

✂ **“ያሙሀመዲ ያህቢቢ፣**
ያሙሀመዱ ኩን ጠቢቢ (ዶክተሬ ሁኑ)፣
<u>ወአጂርኒ ሚን ለሂቢ (ከሚንቀለቀለው እሳት ጠብቂኝ)</u>፣
<u>ኢነ አውዛሪ ሲቃል (ወንጀሎች ከባድ ናቸውና)</u>”

ነብዩ (ﷺ) ግን ዘመዶቻቸው ለሳቸው ባላቸው ቅርበት እንዳይሸወዱ ይልቁንም ተውሒድን በመያዝና ከሺርክ በመራቅ እራሳቸውን እንዲያተርፉ አላህ እንዲህ ሲል አሳስቧቸዋል፡-

﴿ وَأَنذِرْ عَشِيرَتَكَ ٱلْأَقْرَبِينَ ﴿٢١٤﴾ ﴾ الشعراء: ٢١٤

“ቅርብ የሆኑ ዘመዶችህን አሰጠንቅቅ!!” [አሸዕራእ፡ 214]

ይህቺ አንቀፅ በወረደች ጊዜ ነብዩ (ﷺ) ***“<u>የቁረይሽ ህዝብ ሆይ!</u> ነፍሳችሁን ከአላህ ግዙ። ከስተአላህ በኩል ምንም አልፈይዳችሁም። <u>የዐብዱል ሙጥሊብ ቤተሰቦች ሆይ!</u> ከስተአላህ በኩል ምንም አልፈይዳችሁም። <u>የዐብዱል ሙጥሊብ ልጅ ዐባስ ሆይ!</u>***

ከሰተአላህ በኩል ምንም አልፈይድህም። <u>የዐብዱል ሙጥሊብ ልጅ ሶፍያ ሆይ!</u> ከሰተአላህ በኩል ምንም አልፈይዳችሁም። <u>የመልእክተኛው ልጅ ፋጢማ ሆይ!</u> ከገንዘቤ የፈለግሽውን ጠይቂኝ። ከሰተአላህ በኩል ምንም አልፈይድሽም።” [ቡኻሪ፡ ሙስሊም፡ 206]

ወንድሜ ሆይ እህቴ ሆይ! ወገኖቼ ሆይ! ከሰማይ በወረደው ማሳሰቢያ መሰረት ነብዩ (ﷺ) ለቅርብ ቤተሰቦቻቸው ለኔ ባላችሁ ቅርበት እንዳትሸወዱ። በተግባር እራሳችሁን አትርፉ እያሉ ነው። ለአብራካቸው ክፋይ ለፋጢማ ረዲየላሁ አንሃ ያልፈየዱትን ላንተ የሚፈይዱ ይመስልሃልን? ከልብ ሁነህ አስተውል!!

- **“<u>ነቢ አንቱን እያለ፣</u>**
  <u>ቀልቤ ጥሎኝ ዋለለ፣</u>
  <u>ወዳሉበት ደወለ፣</u>
  <u>ሄሎ በሉት አሕመዴ</u>”
- **“<u>አንቱ ኖት ረሃቤ ጥሜ፣</u>**
  <u>ልንገሮት አስቀድሜ፣</u>
  <u>ያላንቱ አይሞቅም ደሜ፣</u>
  <u>ግቡልኝ በጀሰዴ</u>”
- **“ሰብርም የለኝም አለሁኝ ታምሜ፣**
  መንገዱ ጠፍቶብኝ አልቻለም አቅሜ፣
  <u>ጉልበቴ ብርታቴም ባንቱ ነው መቆሜ</u>”
- **“ሳዳቴ አደራ አሁን ለምነናል፣**
  <u>ሁላችን በጅምላ አድሉን ብለናል፣</u>
  <u>ዱስቱር ዱስቱር ብለን እዛው አፍጠናል፣</u>
  <u>አትጨክኑብን እርሶን ለምነናል፣</u>
  <u>ይኸው ደውለናል በቴሌ ግራሙ ግቡልን፣</u>

<u>ይኸው ለምነናል በቴሌ ግራሙ ግቡልን"</u>

ከደካማ ፍጡር ዘንድ የሚያፈጥ አካል ከለማኝ ፊት እንደቆመ ለማኝ ነው። ተለማኙ የማይሰማ የማይለማ፣ በቀብር ያውም በሩቅ ያለ ሙት ሲሆንስ? አሳዛኝ ነው። ጥሪን የሚሰማ፣ ተማፅኖን የሚቀበል ጌታ እያለ ይህን ያክል ከደካማ ፍጡሮች ያውም ከማይሰሙ ጋር ይህን ያክል ሙጭጭ ማለት ከፉ በሽታ ነው። በብቸኝነት ሊለመን የሚገባው አላህ ብቻ ነበር። ባርያዎቹ ሲለምኑትም መልስ የሚሰጠው እሱ ብቻ ነውና። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَقَالَ رَبُّكُمُ ٱدۡعُونِيٓ أَسۡتَجِبۡ لَكُمۡۚ ﴾ غافر: ٦٠

"<u>ጌታችሁም አለ ለምኑኝ እቀበላችኋለሁ።</u>" [ጋፊር፡ 60]

በጅምላም ይበሉት በችርቻሮ ከአላህ ውጭ የሚለመኑት ምንንም መስጠትም ሆነ መከልከል አይችሉም።

<u>ነፍሱ ላይ ጨክኖ ከአላህ ውጭ እያመለከ "አትጨክኑብን" እያለ መጮሁ ይገርማል።</u>

✂ **"ግቡልን በማለት ጠራ መሀይሙ፣**
አንተን በመውደዱ ሄደለት ህመሙ፣
ልቡ ተሸበረ እንዳየህ በህልሙ፣
<u>አንተ ነህ ፀሎቱ ስግደትና ፆሙ፣</u>
<u>መወትወት ጀመረ ቢፈላበት ደሙ"</u>

እኛ ስግደታችንን፣ እርዳችንን፣ ህይወታችንን እናም ሞታችንን የነብዩም (ﷺ) ይሁን የሌሎች ፍጡራን ጌታ ለሆነው ለአንድ አምላክ አላህ ብቻና ብቻ በእርሱም ላይ

ማንንም ሳናጋራ እንድንገዛው ነው የታዘዝነው። የፍጡራኑን ጥሪ ሰሚ አላህ ብቻ ነው። ከአላህ ውጭ ያሉትን ማንንም ይሁን ማን ቢወተውቱት ምንም መስጠጥም ሆነ መከልከል አይችልም።

✂ **“ሰላም አለይኩም ነቢ ያሰይደል አለሚን፣**
<u>እያዩ መባዘኔን ምነው ጨከኑ በእኔ</u>”

ነብዩ (ﷺ) የሱን መባዘን አያዩም። አያውቁምም። እሳቸውን በመጣራቱም ከጌታው ጋር የሚያጣላው ትልቁ ሺርክ ላይ ከመውደቁ ውጭ የሚያተርፍለት ነገር የለም። እሳቸውን **<u>“ጨከኑብኝ”</u>** እያሉ ማናገርም አደበ ቢስነት ነው። **<u>“ያላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል።”</u>**

20. <u>በጭንቀት ጊዜ ማንን ይለምናሉ?</u>

የድሮዎቹ አጋሪያን የሚታወቁት በሰላሙ ጊዜ በማጋራት እና በጭንቀት ጊዜ ለአላህ ሃይማኖትን ያጠሩ ሲሆኑ እሱን በብቸኝነት በማምለክ ነበር።

﴿ فَإِذَا رَكِبُواْ فِي ٱلۡفُلۡكِ دَعَوُاْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمۡ إِلَى ٱلۡبَرِّ إِذَا هُمۡ يُشۡرِكُونَ ٦٥ ﴾ العنكبوت: ٦٥

“በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው ይጠሩታል። ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ።” [አልዐንከቡት፡ 65]

የዛሬዎቹ አጋሪያን ግን በሰላሙም በችግሩም ጊዜ በአላህ ላይ ያጋራሉ። በዚህ ንኡስ ክፍል ላይ ይህንን እውነታ የሚያሳዩ የመንዙማ ስንኞችን እንመለከታለን፡-

✂ **“<u>ያ ሪጃለላህ ያሪጃለላህ፣</u>**
<u>የአህለል በይቲ አጊሱና ቢላህ</u>”

ትርጉሙም፡- “እናንተ የአላህ ወንዶች ሆይ! እናንተ የአላህ ወንዶች ሆይ! የነብዩ ቤተሰቦች ሆይ! **<u>በአላህ ይሁንባችሁ ከዚህ ጭንቀታችን ገላግሉን</u>**።”

✂ **“<u>ያ ረሱለላህ አል መደድ</u>”**

ትርጉሙም፡- “አንቱ የአላህ መልከተኛ ሆይ! **<u>እርዳታዎትን</u>**።” [6]

✂ **“<u>ሰላሚ አላ ገውሰል ሚባዲ፣</u>**
<u>ዳኢመን ቢላ ዐደዲ</u>”

ትርጉሙም፡- “**<u>የባሪያዎች የጭንቅ ገላጋይ የሆናችሁት ሆይ</u>**! ሰላም በናንተ ላይ ይሁን። ዘወትር ስፍር ቁጥር የሌለው።”

✂ **“<u>አጊሱና ገውሱ፣ አሊዩል ጎንደሪ</u>”**

ትርሙም፡- “**<u>የጭንቅ ገላጋይ የሆኑት አሊዩል ጎንደሪ ሆይ! ከጭንቀት ገላግሉን</u>**።”

---

[6] አንዳንዶች የዚህ ስንኝ መልእክቱ “በቂያማ ቀን ስለሚኖረው ትልቁ ሸፈዐ እንጂ እነሱ በአሁኑ ሰዓት ድረሱልን እያሉ አይደለም” ይላሉ። ለዚህ የሚሰጠው መልስ፡-

1. በመጀመሪያ ነገር የሚሉት ነገር ውሸት ነው። እንኳን ነብዩን እና ሌሎች ስንት ፍጡሮችን እየተማጸኑ አይደለምን?
2. እሳቸውን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ፍጡሮችን ለዱንያዊ ጭንቅና ችግሮች የሚማፀኑባቸው በርካታ ስንኞችን እዚሁ መፅሐፍ ላይ ተመልክተናል።
3. በተረፈ ሸፈዐውም ቢሆን ዛሬ ዱንያ ላይ እያለን የምንጠይቀው አላህን ብቻ ነው።

✂ **“<u>ገውሱን ተድራ ገውስ ወልዳ ነገሰች</u>፣**
<u>ኑሩን በኑሩ ላይ ደራርባ ለበሰች</u>”

በመጀመሪያው ላይ ገውስ ተብለው የተገለፁት (የቃጥባሪ ሸይኽ) ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ አቡል ጀበልን ነው። ገውስ ማለት የጭንቅ ገላጋይ ማለት ነው። የጭንቅ ገላጋይ ደግሞ አላህ ብቻ ነው። ኢስቲጋሳ ማለት ደግሞ በጭንቅ ጊዜ የሚደረግ ፀሎት ማለት ነው። በጣም የሚያሳዝነው ነሷራዎች እንኳን መርየምን **<u>“የጭንቅ አማላጇ”</u>** እንጂ የጭንቅ ገላጋዩዋ አላሏትም። ነብዩ (ﷺ) በድር ዘመቻ ላይ በጠላት ተከበው ጭንቅ ብሏቸው የጭንቀት ዱኣ አላህን ለመኑት። አላህም መልስ ሰጣቸው፡-

﴿ إِذْ تَسْتَغِيثُونَ رَبَّكُمْ فَٱسْتَجَابَ لَكُمْ أَنِّى مُمِدُّكُم بِأَلْفٍ مِّنَ ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ مُرْدِفِينَ ﴿٩﴾ ﴾ الأنفال: ٩

“ከጌታችሁ ርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ <u>“እኔ በሺህ መላእክት ተከታታዮች ሲሆኑ እረዳችኋለሁ” ሲል ለናንተ የተቀበላችሁን (አስታውሱ)</u>።” [አልአንፋል፡ 9]

﴿ أَمَّن يُجِيبُ ٱلْمُضْطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكْشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجْعَلُكُمْ خُلَفَآءَ ٱلْأَرْضِ ۗ أَءِلَٰهٌ مَّعَ ٱللَّهِ ۚ قَلِيلًا مَّا تَذَكَّرُونَ ﴿٦٢﴾ ﴾ النمل: ٦٢

“ወይም ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል፣ መከራንም የሚያስወግድ፣ በምድርም ላይ ምትኮች የሚያደረጋችሁ፤ (ይበልጣል? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? <u>ጥቂትንም አትገሠጹም</u>።” [አንነምል፡ 62]

21. <u>ምልጃን ከማን እንጠይቅ?</u>

በቅድሚያ ሊታወቅ የሚገባው ነገር ቢኖር ምልጃ ሁሉ የአላህ መሆኑ ነው። በመቀጠል አማላጆች ለተማላጆች ማማለድ የሚችሉት አላህ ለአማላጅ እንዲያማልድ ሲፈቅድለት ለተማላጅም እንዲማለድለት ሲወድለት ብቻ ነው። ይህን ምልጃ ዱንያ ላይ የሚጠየቀው በቀጥታ አላህ ብቻ ነው። **<u>ከአላህ ውጭ ያለን አካል ነብይም ይሁን መላኢካ ምልጃን መጠየቅ ሺርክ ነው።</u>** ምክንያቱም ይሄ እነሱን መለመን ነውና። ልመና ወይም ዱዓእ ደግሞ ዒባዳ ነው። ዒባዳን ለሌላ መስጠት ደግሞ ሺርክ ነው።

ከዚህ በታች የምታነቡት የአገራችን መንዙማዎች ይሄው ከአላህ ሌላ በቀጥታ ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) አማላጅ ሁኑን ሲሉ በአላህ ላይ የሚያጋሩበት ነው።

- **“<u>ያረሱለላሂ ሸፊዐ ይሁኑና</u>፣**
  የቢላል እኮ ነን በዲኑ የፀና”
- **“<u>እባኮት ሙሂየ</u>**
  <u>ሁኑልኝ ሸፈአየ።</u>”

22. <u>ከአላህ ውጭ መመኪያ አለን?</u>

በአላህ ላይ መመካት የአምልኮ ቁንጮው ነው። አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው።

﴿ رَبُّ ٱلۡمَشۡرِقِ وَٱلۡمَغۡرِبِ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَٱتَّخِذۡهُ وَكِيلٗا ٩ ﴾ المزمل: ٩

“(እርሱም) የምሥራቅና የምዕራብ ጌታ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። <u>መጠጊያ (መመኪያ) አድርገህም ያዘው።</u>” [አልሙዝዘሚል፡ 9]

ባለመንዙማዎች ጋር ያለው ግን ሌላ ነው። ጥቂት ምሳሌ እንመልከት፡-

- **“<u>አንቱ የገደፉት ማን ነው የወደቀው?</u>”**
- **“ያቀመረል መካ አሰላሙ አለይካ፣**
  <u>ልቤ ባንቱ በእርሶ ተመካ</u>”

ነብዩ ﷺ በጠላት ተከበው ከፊታቸው ብዙ አደጋ በተደቀነበት ሰአት እንዲህ ሲሉ መለሱ:-

﴿ ٱلَّذِينَ قَالَ لَهُمُ ٱلنَّاسُ إِنَّ ٱلنَّاسَ قَدۡ جَمَعُواْ لَكُمۡ فَٱخۡشَوۡهُمۡ فَزَادَهُمۡ إِيمَٰنٗا وَقَالُواْ حَسۡبُنَا ٱللَّهُ وَنِعۡمَ ٱلۡوَكِيلُ ١٧٣ ﴾ آل عمران: ١٧٣

“እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፦ “ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው” ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው “<u>በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ!</u>” ያሉ ናቸው።” [አሊ ዒምራን፡ 173]

﴿ وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱلۡحَيِّ ٱلَّذِي لَا يَمُوتُ وَسَبِّحۡ بِحَمۡدِهِۦۚ وَكَفَىٰ بِهِۦ بِذُنُوبِ عِبَادِهِۦ خَبِيرًا ٥٨ ﴾ الفرقان: ٥٨.

“<u>በዚያም በማይሞተው ሕያው አምላክ ላይ ተመካ</u>። ከማመሰገንም ጋር አጥራው። በባሮቹ ኀጢአቶችም ውስጠ ዐዋቂነት በእርሱ በቃ።” [አል ፉርቃን፡ 58]

እነዚህ መንዙማ ባዮች ህያውን ፈጣሪን ትተው የሞቱት ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) በአላህ ላይ ባላንጣ አድርገው ታላቁን መመካት የተባለውን አምልኮ አሳልፈው ይሰጧቸዋል። ይህ ታላቅ በደል ነው። አሳዛኙ ይህ አጥፊ መንዙማ በብዙ ሙስሊም ቤት የኢስላም አካል እየመሰላቸው ህፃናት ሳይቀሩ ሲያቀነቅኑት ይታያል።

23. ስንታመም የሚያድነን ማን ነው?

የሚከተለው የሺርክ መንዙማ ደግሞ በጉራጊኛ ቋንቋ ከአላህ ውጭ አቡል ጀበል የሚባለው ግለሰብ የእግርም ሆነ የእጅ ቁስላችንን ያድነናል ብለው የሚያምኑበት እና እሱን ሰውየውን በቀጥታ የሚለምኑበት ነው።

- **“አቡል ጀበል ሺሊላህ አቡል ጀበል ሺሊላህ፣**
  አሁን ትሆኝ እና መላ፣
  የእግርም ጭዛ የእጅም ጭዛ (የእግርም የእጅም ቁስላችንን አዳኝ)
  አሁን ትሆኝ እና መላ (እናንተ ናችሁ የምታሽሩኝ)”

የሚከተሉትም አማርኛ መንዙማ ስንኞች ከአላህ ውጭ በሽታን ነብዩ (ﷺ) እንዲያድኑ አድርገው ያቀረቡበት ነው።

- **“መሻር ባንቱ ነው ያደዋኡና፣**
  ያምስኪ መዲና ጋየተል ሙና”።
- **“የጀሊል ባለሟል የሆኑት ሃቀኛ፣**
  ምነው ብታሽረው ያንን በሽተኛ፣
  ሙሃባው ተነጥቆ የሆነ ደመኛ፣ ሀቢቢ ሀቢቢ ሀቢቢ”

አላህ ፍጹም ወዳጅ አድርጎ የያዛቸው ኢብራሂም (ዐለይሂ-ስሰላም) ግን አላህን አስመልክተው ለአጋሪያን ሲየስረዱ እንዲህ ይላሉ፡-

﴿ ٱلَّذِى خَلَقَنِى فَهُوَ يَهۡدِينِ ﴿٧٨﴾ وَٱلَّذِى هُوَ يُطۡعِمُنِى وَيَسۡقِينِ ﴿٧٩﴾ وَإِذَا مَرِضۡتُ فَهُوَ يَشۡفِينِ ﴿٨٠﴾ وَٱلَّذِى يُمِيتُنِى ثُمَّ يُحۡيِينِ ﴿٨١﴾ وَٱلَّذِىٓ أَطۡمَعُ أَن يَغۡفِرَ لِى خَطِيٓـَٔتِى يَوۡمَ ٱلدِّينِ ﴿٨٢﴾ رَبِّ هَبۡ لِى حُكۡمًا وَأَلۡحِقۡنِى بِٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٨٣﴾ ﴾ الشعراء: ٧٨ - ٨٣

"(እርሱ) ያ የፈጠረኝ ነው። እርሱም ይመራኛል። ያም እርሱ የሚያበላኝና የሚያጠጣኝ ነው። <u>በታመምኩም ጊዜ እርሱ ያሽረኛል</u>። ያም የሚገድለኝ ከዚያም ሕያው የሚያደርገኝ ነው። ያም በፍርዱ ቀን ጎጢአቴን ለእኔ ሊምር የምከጅለው ነው። ጌታዮ ሆይ! ዕውቀትን ሰጠኝ! በደጋጎቹም ሰዎች አሰጠጋኝ።" [አሽዑራእ፡ 58]

24. <u>በአላህ እና መልክተኛው ላይ መዋሸት</u>

በአላህ እና በመልክተኛው ላይ መዋሸት ከባድ ወንጀል ነው። እስልምና ሃይማኖት የተገነባው ከአላህ ቃል ቁርኣን፣ ከነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሀዲሶች ነው። ስለዚህ አላህ እና መልክተኛው (ﷺ) ያላሉትን ብለዋል ብሎ ማውራት በተለይ እንዲህ የሀይማኖት ሰዎች ናቸው እየተባሉ አላህ እና መልክተኛው (ﷺ) ላይ መዋሸት ኢስላምን መናድ እና ሙስሊሞችን ማወናበድ እና እምነታቸውን ማጭበርበር ነው።

ጥቂት ለትዝብት ያክል፡-

✂ **"መጀን በኑር ሁሴን በአሩሲው ኑር፣**
የአውሉያዎቹ ሻምበል የበርም የባህር፣
ከራማው ይፋ ነው አይደለም መስቱር፣

እጣው እንደ ነቢይ በርዳዳው ገበር፣ [7]
የሪጃሎች አባት የነዚያ ያብራር፣
የነአህመድ ኑረላህ ዚልፈይዲል ሚድራር፣
ተብሏል አላህ ዘንዳ በሻህው አብሽር፣
ጌታየ ኑር ሁሴን በለኝ የኔ አሸከር፣
በዱንያ በአኼራም እንዳልቸገር፣
በናንተ የሸሸ እንዲሁም አይቀር፣
አላህ ሰጥቷቸኋል ሳይሰፍር ሳይቆጥር።"

✂ **"ሸህ መሀመድ ፈቂህ ባለመነጠር፣**
የታደለው ገበር ከአላህ ዘንዳ ሲር"

✂ **"ለካ ገረዋ ላይ አብርቷል ጀምበር፣**
ሲፈቱ መለኪይ ዛቱ የበሸር፣
ተብሎ አላህ ዘንዳ በሺር ወአንዚር፣
ጎራ እማይጋርደው ይዟል መነጠር፣
ይናገር ነበረ የዚሂር የሲር፣
ይገልጠው ነበረ የኸልቁን ኸጢር"

✂ **"ለገሂዳም ጃማ ስንቱ ጉድ ነበር፣**
እነ ነብዩ ሀድራ የተባሉ አብሽር፣
ባልከው ይሁን ያለው ገና ሲፈጠር"

---

[7] **"እጣው እንደ ነቢ…" እስኪ ይህን ድፍረት ተመልከቱ፡፡** "ነብዩን (ﷺ) አትጣሩ" ሲባሉ "ከብራቸውን አጎደፋችሁ፡፡ እሳቸው እንደኛ ተራ ሰው አይደሉም" እያሉ ፈጥረው የሚወነጅሉ ሰዎች እዚህ ማን አንድን ተራ ምስኪን ከነብዩ (ﷺ) ጋር እያመሳሰለ ነው፡፡

እነዚህ ስንኞች በደካማ ፍጡሮች ላይ ድንበር ማለፍ፣ የጌታን ክብር ማጉደፍ፣ ፍጡሮችን ከፈጣሪ ጋር ማመሳሰል አለባቸው። በዚያ ላይ ያፈጠጡ ያገጠጡ ውሸቶች ታጭቀውባቸዋል። አላህ እሱ ላይ የሚዋሹ ሰዎችን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوْ كَذَّبَ بِـَٔايَٰتِهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٢١﴾ ﴾ الأنعام: ٢١

"<u>በአላህም ላይ ውሸትን ከቀጣጠፈ ወይም በአንቀጾቹ ካስተባበለ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? <u>እነሆ በደለኞች አይድኑም</u>።" [አልአንዓም፡ 21]

25. <u>ከኢልመል ገይብ ጋር የሚጋጩ ስንኞች</u>

"ኢልመል ገይብ" ማለት የሩቅ እውቀት ማለት ነው። የሩቅ እውቀት በጠቅላላ የአላህ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُل لَّا يَعْلَمُ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ٱلْغَيْبَ إِلَّا ٱللَّهُ ۚ وَمَا يَشْعُرُونَ أَيَّانَ يُبْعَثُونَ ﴿٦٥﴾ ﴾ النمل: ٦٥

"በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ሩቅን ምስጢር አያውቅም። ግን አላህ (ያውቀዋል)። መቼ እንደሚቀሰቀሱም አያውቁም" በላቸው። [አንነምል፡ 65]

عَنِ ابْنِ عُمَرَ ـ رضى الله عنهما ـ أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ

" مَفَاتِيحُ الْغَيْبِ خَمْسٌ لاَ يَعْلَمُهَا إِلاَّ اللَّهُ لاَ يَعْلَمُ مَا فِي غَدٍ إِلاَّ اللَّهُ، وَلاَ يَعْلَمُ مَا تَغِيضُ الأَرْحَامُ إِلاَّ اللَّهُ وَلاَ يَعْلَمُ مَتَى يَأْتِي الْمَطَرُ أَحَدٌ إِلاَّ اللَّهُ، وَلاَ تَدْرِي نَفْسٌ بِأَىِّ أَرْضٍ تَمُوتُ، وَلاَ يَعْلَمُ مَتَى تَقُومُ السَّاعَةُ إِلاَّ اللَّهُ ".

ከዐብደላህ ኢብን ዑመር (ረድየላሁ ዐንሁማ) የአላህ መልክተኛ እንዲህ ብለዋል **"የሩቅ ሚስጥር ቁልፍ አምስት ናቸው። አላህ እንጂ ማንም የማያውቃቸው። <u>ነገ ምን</u>**

<u>እንደሚከሰት አላህ እንጂ ማንም አያውቅም</u>። <u>ሆድ ውስጥ (የተረገዘው) ምን እንደሆነ አላህ እንጂ ማንም አያውቅም</u>። <u>አላህ እንጂ መቼ እንደሚዘንብ ማንም አያውቅም</u>። <u>ነፍስ የት እንደምትሞት ማንም አያውቅም</u>። <u>የምፅዓት ቀን መቼ እንደምትቆም አላህ እንጂ ማንም አያውቅም</u>።" ኢማሙ አል ቡኻሪ ዘግበውታል።

የአላህ መልክተኛ (ﷺ) **"<u>የሩቅን ሚስጥር (ነገር) ከአላህ ውጭ የሚያውቅ የለም</u>"** ብለዋል። ኢማሙ ጠበራኒ ዘግበውታል።

አላህ ከመልክተኞቹ ለፈለገው የፈለገውን የሩቅ ሚስጥር ያሳውቃል። ይህ ሆኖ ሳለ እውነታው ተመልክቱ የሚከተሉት ስንኞች እንዴት ከእስልምና አስተምህሮት እንደሚጋጩ፡-

✂ **"አልዩ ሀይደር፣**
ነበረ ለነቢ ማኖሪያ ሚስጥር፣
<u>ኢልመልገይብ ከሱ ይጠየቅ ነበር</u>።"

ማን ነበር ጠያቂው? የታለስ ማስረጃው?

✂ **"ሺሊላህ ኢማሙ ግቡልን፣**
መተኮስ ጀመረ የፍቅር ተኳሹ፣
በወዳጆቹ ልብ እንደ ምንጭ ፈሳሹ፣
<u>የረሱል ምስለኔ አላጋውን ወራሹ፣</u>
<u>የልብን መርማሪ እሱ ነው ፈታሹ</u>"

✂ **"ሺሊላህ ሸህ ሙሃመድ ባህሩ፣**
<u>ለጠራው ደራሽ ነው ምን ቢርቅ አገሩ፣</u>
እኔስ ይገርመኛል የሰው ነገር፣

<u>ይላል እንዘይር ቀልቡን ሳያጠራ፣</u>
<u>የማያውቁ መስሎት የቀልቡን የሰድሩን"</u>

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٥﴾ هود: ٥

"እርሱ በደረቶች ውስጥ ያለውን ሁሉ ዐዋቂ ነውና።" [ሁድ፡ 5]

✂ **"ሰይድ ቡሽራ ገታ ቀምጣላው ገበር፣**
<u>ከልካይ የለበትም ሲዘልቅ እልፍኝ በር [8]፣</u>
<u>ጨወታው ነበር ቀዲ ቀደር ጋር</u>፣"

አዐዙ ቢላህ!! ሰዎቹ ድፍረታቸው የት እንደደረሰ ተመልከቱ። ጭራሽ ቀዲና ቀደር እስከመቀያየር ስልጣን ነው የሚያንጋጥጡት። ሰዎቹ እዚሁ ላይ በቃ ካልተባሉ ለጥፋታቸው ለከት የላቸውም። ተናጋሪዎቹስ ሰውነታቸው ጥፋትን ተላምዷል። ሙስሊም የሆነ ሰው ይህን ሲሰማ አይሰቀጥጠውም? በማዳመጡ ብቻ አላህ እንዳይጠይቀው አይፈራምን?

አላህ ከመልክተኞቹ ለወደደው ብቻ ነው የሩቅን ሚስጥር ያውም ከፊሉን የሚሳውቀው።

---

[8] ለይለተል ኢስራ ወል ሚእራጅ የመጀመሪያው ሰማይ ጠባቂ ጂብሪልን ዐለይሂ ሰላም **"ማን ነህ?"** ሲል ጠየቀው፣ እሱም፡ **"ጂብሪል ነኝ"** አለ። **"ማን አብሮህ አለ?"** ሲል ጂብሪልም፡ **"ሙሐመድ"** አለ። **"ተጠርቷልን?"** ብሎ ሲጠይቀው **"አዎ"** አለ። ከዛም ተከፈተልን ገባን። በእያንዳንዱ ሰማይ ይህንን ጥያቄ ተጠየቅን።

﴿ عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ فَلَا يُظۡهِرُ عَلَىٰ غَيۡبِهِۦٓ أَحَدًا ٢٦ إِلَّا مَنِ ٱرۡتَضَىٰ مِن رَّسُولٖ فَإِنَّهُۥ يَسۡلُكُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَمِنۡ خَلۡفِهِۦ رَصَدًا ٢٧ ﴾ الجن: ٢٦-٢٧

"(እርሱ አላህ) ሩቁን ምስጢር ዐዋቂ ነው። <u>በምስጢሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም።</u> <u>ከመልክተኛ ለወደደው ቢሆን እንጅ (ለሌላ አይገልጽም)።</u> እርሱም ከሰተፊቱም ከሰተኋላውም ጠባቂዎችን ያደርግለታል። [አልጂን፡ 26-27]

ለምሳሌ ለነብዩ (ﷺ) ቂያማ መቼ እንደሚከሰት አላሳወቃቸውም። ነገር ግን ምልክቶቿን አሳውቋቸዋል። ስለዚህ መልክተኞች እንኳን ከሩቅ ሚስጥር አላህ የወደደላቸው እና ከፊል የፈለገውን ብቻ ነው የሚያሳውቃቸው። እዚህስ?

- **"እነሽሁ ሀቢብ ጓደኛው ገበር፣**
  <u>ከአርሽ እስከ ሰራ ይታየው ነበር</u>፣
  <u>አላህ አርጎት ነበር የሚስጥር ሰፈር</u>"
- **"እንደ ሁሴን ጂብሪል ደግሞ ማን ነበር፣**
  <u>የከሸፉ መነጠር አይኑ ላይ ነበር</u>፣
  <u>የፊቱን የኋላን ይናገር ነበር</u>፣
  <u>ሁሉም ተገላልጦ ይታየው ነበር</u>።"
- **"መጂት ሀጅ ቡሽራ የራቀው ገበር፣**
  <u>አገላባጭ ነበር የቀዷ ደብተር</u>፣
  <u>ለውሀል መህፉዝ አይቶ ነበር ሲናገር</u>።"

ኢና ሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂዑን።

26. ውሸቶች እና ተረተረቶች

እነዚህ መንዙማ ባዮች **"ወልይ"** የሚሏቸውን ሰዎች በውሸት እና በተረተረቶች የሚክቡት ሰውን የነሱ (የሸሆቹ) ባሪያ ለማድረግ ነው። ሰዎቹን ከደረጃቸው በላይ ከፍ ከፍ በማድረግ ሰዎች እንዲያመልኳቸው በርን ለመክፈት የሚደረግ ጥረት ነው። ማንኛውም ሙስሊም ወሬን ማጣራት አለበት። አላህ እንዲህ ይላል

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِن جَآءَكُمۡ فَاسِقُۢ بِنَبَإٖ فَتَبَيَّنُوٓاْ أَن تُصِيبُواْ قَوۡمَۢا بِجَهَٰلَةٖ فَتُصۡبِحُواْ عَلَىٰ مَا فَعَلۡتُمۡ نَٰدِمِينَ ٦ ﴾ الحجرات: ٦

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በሰሀተት ላይ ሆናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጸቾች እንዳትሆኑ አረጋግጡ።" [አልሑጁራት፡ 6]

እነዚህ መንዙማ ባዮች ከላይ እንዳሳለፍነው አላህ እና መልክተኛው ላይ ሲዋሹ ምንም ያልመሰላቸው ሌሎች ግለሰቦች ላይ አይዋሹም አንልም። እነሱ "ወልይ" የሚሏቸው ላይ ድንበር አልፈው ያልሰሩትን ሰሩ እያሉ ሲናገሩ በሸሪዓ ሚዛን ወሬውን ልናጣራው ይገባል። የሚከተሉት ስንኞች ቅጥፈቶች ናቸው።

- **"ጌታው ሀሰን ለሚ በራራ ነበር፣**
  <u>ሙት የሚቀሰቅስ ጉድ ያለው ገበር</u>፣
  ለሰሚው ይአጅባል የሰሩት ነገር"
- **"የጌታው ስጦታ ስፍር የለው ቁጥር፣**
  ለሸህ አሊ ጎንደር፣ አድርጎት ነበር ባለመነጠር፣
  ለበረካው ያህል ጥቂት ልናገር፣
  አንዲት ላም ኮሬብ ላይ ስትበላ ሳር፣
  <u>እላይዋ ላይ ወጥታ በናትዎ ቀብር</u>፣

ጎንደር ሆነው አዩዋት የሚያጅብ ነገር፣
ተዛ ተቆጡና ሸህ አሊ ጎንደር፣
ሆዷን ቢሏት ሞተች ወርውረው ጢጠር፣
ምነው አይባልም የወልይ ነገር፣
ለባለቤቲቱ ሰደዱላት ብር፣
አፉ በይኝ አሏት ሀቋም እንዳይቀር፣
እየው የአላህ ስራ ከባሮቹ ጋር”

“ምነው” የማይባለው አላህ ነው። ስለዚህ እንጠይቃለን፡- ማገናዘብ የማትችለውን ላም እንዴት ቀብር ላይ ወጣች ብለው ከጎንደር ወሎ ወርውረው ገደሏት? በዚህ መልኩ ነፍስ ማጥፋት ይፈቀዳል? ለነገሩ የብዙ **“ወልዮች”** ገድል በነፍስ ማጥፋት ታሪክ የተሞላ ነው። **“እከሌ ወልይ እከሌ የሚባሉትን በመዐና ገደሏቸው”**፣ **“አርባውን አባወራ ድንጋይ አደረጉት”**፣... አይነት ታሪኮች ብዙ ናቸው። እነዚህን ታሪኮች እውነት ብለን ከተቀበልን እነዚህ ሰዎች ነፍሰ በላዎች ናቸው። ስለዚህ ልናከብራቸው ሳይሆን ልንፀየፋቸው ነው የሚገባን። ታሪኩን ውሸት ነው ብለን ከመለስን እንዲህ አይነት ተረት የሚያወሩ የዲን ነጋዴዎችን ልንርቅ ይገባል።

✂ **“የሂዲ ሸህ ደግሞ ጋላቢው ነብር”**

አብዛሀኛዎቹ የሃገራችን የአውሊያእ ጀብዱዎች ከአሉ አሉ ባለፈ ይሄ ነው የሚባል ማረጋገጫ የማይቀርብባቸው ተረቶች ናቸው። ይህን የምለው ከራማን ለመቃወም አይደለም። በአላህ፣ በዲኑ እና በመልእክተኛው ላይ የሚዋሽ አካል ገበያ ለመፍጠር ሲል ድንበር በሚያልፍባቸው አካላት ላይ አይዋሽም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ስለዚህ በደፈናው ባንቃወምም ያለ አስተማማኝ ሰነድ የሚወሩ ወጣ ያሉ ቂሷዎቻቸውን ያለተጨባጭ ማስረጃ ልንቀበል አይገባም። የት አለ ውሸታቸው ከተባለ ለምሳሌ ያክል ይሄውና፡-

✂ **“ሸህ ሙሀመድ ሸሪፍ የርጎየው ገበር፣**
<u>ሲመድህ ሙስጠፋን እያየ ነበር</u>።”

ነብዩ (ﷺ) መዲና ቀብር ውስጥ ነው ያሉት። ታዲያ እንዴት ነው የሚያያቸው? ከሞቱ በኋላ በህልም እንጂ ማንም በአካል አያያቸውም። ሌላ ውሸት ይሄውና!

✂ **“ረቢአል አወል የገባ ጊዜና፣**
<u>በሀኢሙ (እንስሳው) ሁላ ያቀርባል ምስጋና</u>፣
<u>ለመውሊድ አድርገን እያለ መውላና</u>”

ሐቅ የያዙ ሰዎች በሚያንቀላፉበት ምድር ውሸታሞች ይህን ያክል በድፍረት ይሰብካሉ። መረጃ አጥቶ የሚልፈሰፈሰውን መውሊድ እንዲህ በቅጥፈት ሊያቆሙት የውሸት ክራንች ያቀብሉታል። አሁንም ሌላ ውሸት ይሄውና!

✂ **“ጌታው አባ ረህማ የአውልያ መምህር፣**
<u>ጨዋታው ነበረ ሰይድ ከድር ጋር</u>፣
ሁሉም ከሀድራው ይቀስም ነበር።”

ኸዲር ሙተዋል። በየት አግኝቷቸው ነው ከሳቸው ጋር የሚጫወተው?

27. <u>ጫት እና መንዙማ</u>

ጫት ህዝባችንንም አገራችንንም ወደኋላ እየነተተ ያለ አደገኛ አደንዛዥ ቅጠል ነው። ከሁሉ በጣም የሚያሳዝነው ይህ እርኩስ ቅጠል በአውቆ አጥፊዎች፣ እውቀት በሌላቸው ሰዎች እና ከእስልምና ሃይማኖት ውጭ ባሉ ሰዎች ውስጥ እንደ ትልቅ

የኢስላም አካል ተደርጎ መወሰዱ ነው። የጫትን መጥፎነት ማወቅ የፈለገ በተጨባጭ አገራችን ላይ በተለይ ሙስሊሙ ላይ ያደረሰውን ጉዳት መመልከት ይችላል።

እነዚህ መንዙማ ባዮች ግን ምን ያክል ጫትን እያንቆለጳጳሱ ዲናዊ ቅብ እንደሰጡት እንመልከት።

- **“ጁሉሱ ሰላቲን ጥቂት ቃቅምና**
  ንገረው ለመውላህ እበሩ ቁምና”
- **“እነሱ ይበራሉ በመቶ ሃምሳ ጀት፣**
  እኛ ቀደም ናቸው በአንድ ዘርባ ጫት”
- **“ተአስር ሺህ መትረየስ አጥምዶ ተቆመ፣**
  ከሺህ ፈረሰኛ ተባብሮ ለጉሞ ከቆመ፣
  ይበልጣል ደግበል አድቅቆ የቃመ፣
  ጠላቱንም ጎድቶ ወዳጁን ጠቀመ።”

ሰውየው ጫት በመቃሙ እራሱን እና ለእርሱ ጥሩ የሚያስቡትን መልካም ወዳጆቹን ይጎዳል። በተገላቢጦሹ እውነተኛ ጠላቱ የሆነውን ሸይጧን አላማ በማሳካት ሸይጧንን ይጠቅመዋል። ከዚህ ውጭ ሰው ጫትን አይደለም አድቅቆ ቢቅም ጁስ አድርጎ ቢጠጣው እንኳን እራሱን መጥቀምም ይሁን ጠላቱን መጉዳት አይችልም።

- **“ፍየል ቅጠል በልታ ትወልዳለች መንታ፣**
  መቼም እርባን የለው በጫት የተመታ”

ይልቅ እራሱ ጤናውንም፣ ገንዘቡንም፣ ዲኑንም በጫት ከሚያስመታ በጊዜ ቢማር ይሻለው ነበር። በተረፈ “ጫት ቅመን በቀልባችን ነደፍናቸው” እያሉ የሚያሰሙት

ፉከራ ተረተረት ነው። ይልቅ እርባና የሌለው ቅጠል እያኘከ የአላህን፣ የሚስቱን፣ የልጆቹን፣ የቤተሰቦቹን እና የፍጡራንን መብት ጀዝቦ የማያሟላው ነው።

✂ **“ዝናቡ ዘነበ ጫቱ ለመለመ፣**
<u>የሚቅመው ቢያገኝ እያጉረመረመ</u>”

ኡመተል ኢስላምን ያሸመደመደው፣ ያጀዘበው፣ የአላህንም የፍጡራንንም ሀቅ እንዲያጓድል ሰበብ የሆነው ይህን አደንዛዥ ቅጠል እንዲህ እያሉ ያስተዋውቁታል። አላህ ወንድም እና እህቶቻንን ከዚህ ሱስ ያውጣልን።

✂ **“ወጣቶች ዘፈኑ በስልት እያዜሙ፣**
<u>እያሉ ይጠሩሃል ሺሊላህ ኢማሙ፣</u>
<u>ይመጅኑብሃል ቂምሃ እየቃሙ</u>[9]<u>፣</u>

28. <u>ሌሎች</u>

✂ **“<u>ቶሎ በል ቶሎ በል፣ አንድየ ቶሎ በል</u>፣**
<u>እንደ ዘመኑ ሰው ነገ ዛሬ አትበል</u>”

ኢናሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂዑን!! ተመልከቱ የዚህ መንዙማ ባይ ድፍረትና መሃይምነት። ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ይላሉ ***“ማንም ሙስሊም በወንጀል እና ዝምድናን በመቁረጥ ዱዓ እስካላደረገ ድረስ አላህ ከሶስት አንዱን ይሰጠዋል። ወይ የለመነው***

[9] ጫት ኡማው ከጌታው ወይንም ከቤተሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት አቆርፋጅ፣ አደንዛዥ ቅጠል፣ ትውልድ ገዳይ፣ ቤተሰብ በታኝ፣ አገር አበላሽ፣ ተውልድ አኮላሽ ነው። በተለይ በተለይ ሙስሊሙን ከጎዱ top 5 ከሚባሉት ነገሮች ውስጥ ዋናው ነው። እንዲህ አይነት ደፋር መንዙማ ባዮች እና የሃይማኖት አባት ነን ባዮች ሙስሊሙን በተለይ ወጣቱን ለማደንዘዝ ጫትን የእስልምና አካል አድርገው ያቀርቡታል። አላህን ይፍሩ። እስልምና ከእንዲህ አይነት አደንዛዥ እፅ የፀዳ ነው።

ይደርሰዋል፣ ወይ ለአሼራ ያዘገይለታል፣ ወይም አምላያውን በላ ያነሳለታል"። አሁንም ነብዩ (ﷺ) በዱዓ እንዳንቻኮል ነገረውናል። አላህን እንዲህ አድርጎ ከፍጡር ጋር በማመሳሰል መግለፅ ምን የሚሉት በሽታ ነው? አላህ አደብ እና እውቀት ይስጠን።

- **"እጫጭሱላቸው በሁለቱ ገል (ማጨሻ)፣**
  <u>አንዱም የአብዶዮ ነው፣ አንዱም የኸድር</u>"

ልብ በሉ ብዙ እናቶች እና አባቶች ቡና ይፈላ ይባል እና ቁርስ ጀባ ቃሃ ጀባ እየተባለ እጣን ይጨሳል። እጣኑም ሲጨስ እንዲህ ከአላህ ውጭ ያሉን የሚጠሩበት ሁኔታ አለ። አንድ ሰው ቤቱ ላይ ቤቱ ጥሩ ሽታ እንዲኖረው ማጨስ ይችላል። ይህን የሚያጨሰው ግን ለጥፋት በመደገስ ከሆነ ከአላህ ጋር ነው የሚያጣላው።

- **"ተግርዶው ነው ወይ፣ ወይንስ ከቡኑ፣**
  ነው ወይንስ ከጫቱ፣ ወይስ ከጉዝ ጓዙ፣
  ወይስ ከመጀን፣ ነው ወይንስ ከመጀን፣
  <u>ሌላውን በጮማ እኛን በጎመን</u>፣ ወይንስ ከመጀን፣
  ወይንስ ከወንድም፣ ወይንስ ከእህት፣
  <u>ሌላውን በጮማ እኛን በጎመን</u>"
- **"እያረግክላቸው እያየሁህ (ኝ) ባይኔ፣**
  <u>የበደል መሰለኝ አረ ምነው እኔ</u>"
- **"<u>ሲበሉ አልበላሁም፣ ሲለብሱ አለበስኩም፣</u>**
  <u>ሲያጌጡ አላጌጥኩም፣ ሲያገቡ አላገባሁ፣</u>
  <u>ሲሰሩ አልሰራሁኝ፣ ሁል ጊዜ ሁል ጊዜ ሃያቴን ፈጀሁት</u>።"

ሰይጣን ምን እንዳለ አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል

﴿ ثُمَّ لَآتِيَنَّهُم مِّنۢ بَيۡنِ أَيۡدِيهِمۡ وَمِنۡ خَلۡفِهِمۡ وَعَنۡ أَيۡمَٰنِهِمۡ وَعَن شَمَآئِلِهِمۡۖ وَلَا تَجِدُ أَكۡثَرَهُمۡ شَٰكِرِينَ ١٧ ﴾
الأعراف: ١٧

"(ሰይጣንም) "ከዚያም <u>ከሰተፊቶቻቸው ከኋላቸውም ከቀኞቻቸውም ከግራዎቻቸውም በእርግጥ እመጣባቸዋለሁ። አብዛኞቻቸውንም አመሰጋኞች ሆነው አታገኛቸውም</u>" (አለ)።" [አልአዕራፍ፡ 17]

﴿ وَإِذۡ تَأَذَّنَ رَبُّكُمۡ لَئِن شَكَرۡتُمۡ لَأَزِيدَنَّكُمۡۖ وَلَئِن كَفَرۡتُمۡ إِنَّ عَذَابِي لَشَدِيدٞ ٧ ﴾
إبراهيم: ٧

"ጌታችሁም "<u>ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ ብትክዱም (እቀጣችኋለሁ) ቅጣቴ በእርግጥ ብርቱ ነውና</u>" በማለት ባሰታወቀ ጊዜ (አሰታውሱ)።" [ኢብራሂም፡ 7]

29. <u>"ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል"</u>

እነዚህ የሺርክ መንዙማ ባዮች ሌት ተቀን ከአላህ ሌላ ያለን ነብይ፣ ወሊይ እና ወሊይ ተብየዎችን ሲጠሩ አይተው ጴንጤዎችም ሙስሊሙን አላህን ትቶ ወደ ነብዩላህ ኢሳ አምልኮ እንዲገባ ጥሪያቸውን በመንዙማ በማቀናበር እያቀረቡ ነው። ለጊዜው እጇ የገባው መንዙማ እንዲህ ይላል፡-

✂ **<u>"ዘይኔው ነብዬ፣</u>**
<u>ኢሳ አላህዬ"</u>

ሙስሊሙ የጴንጤዎቹን መንዙማ ሲሰማ ያሳየው አቋም እና ቁጣ በጣም የሚመሰገን ነው። ከባዱ ጥያቄ መንዙማው ተቃውሞ ያስነሳው ኩፍር ስለሆነ ነው ወይንስ ጴንጤዎች ስለዘመሩት? ኩፍር ስለሆነ ከሆነ በጣም ያስደስታል። አብሮ ግን የሚነሳ በጣም ወሳኝ ጥያቄ አለ። እሱም ከላይ ያየናቸው የክህደት፣ የሺርክ፣ የቢድዓ እና

ሌሎችም መንዙማ እና ነሺዳዎች ሲዘመሩስ ይቆጣሉ ወይንስ አይቆጡም? ካልተቆጡ ከባድ አደጋ ውስጥ ኖት። ምክንያቱም ዋናው ጠብ ከሺርክ ጋር ነው። ለምሳሌ ከአላህ ውጭ አንድ ሰው መርየምን ቢያመልክ ሺርክ ነው። ልክ እንደዚሁ አንድ ሰው ከአላህ ውጭ ነብዩን (ﷺ) ቢያመልክም ሺርክ ነው።

አንድ የማውቀውን እውነተኛ ታሪክ ልጥቀስ። ልጅቷ ሙስሊም ነበረች። ታሪኳ እንዲህ ነው። አባቷ እሮብ እሮብ በየሳምንቱ የሚያርድ እና በጣም ብዙ ሰዎች ፈርተውት የሚሰግዱለት ግለሰብ ነበር። ይህች ልጅ ይህን ተግባር ህይወቷን ሙሉ ትመለከት ነበር። ስለ ኢስላምም ብዙ እውቀት የላትም ነበር። ከዚያም ጄንጤ ሆነች። ዘመዶች አግኝተው ሲያናግሯት **"<u>አይደለም ለእየሱስ ለእኔ አባትም ሰው ይሰግዳል</u>"** የሚል አስደንጋጭ መልስ ሰጠች።

በርግጥ በአሁኑ ሰዓት ልጂቱ ወደ እስልምና ተመልሳለች። አላህ ፅናቱን ይለግሳት። ሆኖም ግን ከስተቱ አንድ ቁም ነገር ያስጨብጠናል። እሱም እኛ ሙስሊሞች ጄንጤ እንዲህ አደረገ ብለን ከማለታችን በፊት ሙስሊሙን ማህበረሰብ ከምንም በፊት በተውሒድ ላይ ማነፅ ይገባናል። ያለበለዚያ በመሀላችን የሚገኙ ድንበር ዘለል አክብሮቶች በራሳቸው በቂ ጥፋት ከመሆን አለፈው ሰፋፊ የጥፋት ሽንቁሮችን ይከፍታሉ።

30. <u>ነብዩን (ﷺ) ማሞገስ ለንግድ መጠቀም</u>

የሚከተለው ጥያቄ ለታላቁ አሊም ሙሐመድ ሷሊህ አል-ኡሰይሚን (ረሂመሁላህ) ቀረበላቸው

ጥያቄ፡- ነብዩን (ﷺ) ማሞገስን በንግድነት መጠቀም እንዴት ይታያል?

መልስ፡- ይህ ሐራም ነው። የነቢዩ (ﷺ) ሙገሳ በሁለት እንደሚከፈል መታወቅ አለበት፡-

አንደኛው፡- ሳያጋንኑና ከልክ ሳያልፉ በሚገባቸው ነገር ማሞገስ ነው። ይህ ችግር የለውም። ነቢዩ (ﷺ) ከስነ ምግባራቸው በሚገባቸው ነገር ቢሞገሱ ችግር የለውም።

ሁለተኛው፡- ከልክ ያለፈ ሙገሳ ነው። ይህን ነቢዩ (ﷺ) እንዲህ በማለት ከልክለዋል። ***"ክርስቲያኖች የመርየምን ልጅ እንዳላቁት (ከደረጃው በላይ ከፍከፍ እንዳደረጉት) አታልቁኝ እኔ ባሪያ ነኝ የአላህ ባሪያና መልእክተኛው በሉኝ"*** ብለዋል።

ነቢዩ (ﷺ) እርዳታ የጠየቃቸውን የሚረዱ (የሚደርሱለት) ናቸው። የተቸገረን ሰው ዱዓ ይቀበላሉ። የአዱንያና የአኺራ ተቆጣጣሪ ናቸው። ገይብን ያውቃሉ እና የመሳሰሉትን በማለት ነቢዩን ማሞገስ ሐራም ነው። ከኢስላም ወደ ሚያስወጣው ሽርኩል አክበር ደረጃም ሊደርስ ይችላል። ነቢዩን (ﷺ) ከልክ አሳልፎ ማሞገስ አይቻልም። ነቢዩ (ﷺ) ከልክለውታልና።

ወደ ጥያቄው ጭብጥ እንመለስና የሚፈቀደውንም ሙገሳ ቢሆን በንግድነት መጠቀም ሐራም ነው። ምክንያቱም ነቢዩን (ﷺ) ከስነ ምግባራቸው፣ ምስጉን ከሆነ ባህሪያቸውና ቅኑን መንገድ ከመምራታቸው በሚገባቸው ነገር እሳቸውን ማሞገስ ኢባዳ ነው። ዒባዳ ደግሞ ወደ አላህ የሚቃረቡበት መንገድ ነው። ስለዚህ ለዓለማዊ ጥቅም መፈለጊያ መዋል የለበትም። አላህ እንዲህ ይላል።

﴿ مَن كَانَ يُرِيدُ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيۡهِمۡ أَعۡمَٰلَهُمۡ فِيهَا وَهُمۡ فِيهَا لَا يُبۡخَسُونَ ١٥ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَيۡسَ لَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ إِلَّا ٱلنَّارُۖ وَحَبِطَ مَا صَنَعُواْ فِيهَا وَبَٰطِلٞ مَّا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٦ ﴾
ሁድ: ١٥ – ١٦

"ቅርቢቱን ሕይወትና ጌጧን የሚሹ የሆኑትን ሰዎች ሥራዎቻቸውን (ምንዳዋን) በእርሷ ውስጥ ወደነሱ እንሞላላቸዋለን። እነሱም በርሷ ውስጥ ምንም አይጎድልባቸውም። እነዚያ እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ለእነርሱ ከእሳት በቀር የሌላቸው ናቸው። የሠሩትም ሥራ በርሷ ውስጥ ተበላሸ። (በቅርቢቱ ዓለም) ይሠሩት የነበሩትም በጎ ሥራ ብልሹ ነው።" [ሁድ፡ 15-16]

የሸይኽ ኡሰይሚን (ረሂመሁላህ) ንግግር እዚህ ጋር አበቃ።

ስለዚህ ወገኖቼ! በነቢዩ (ﷺ) ስም የሚዜሙ **"ሶለዋቶችን"** በየካፍቴሪያው፣ በየምግብ ቤቱ እየከፈትን ማሻሻጫ አናድርጋቸው።

31. <u>ማጠቃለያ</u>

እስካሁን ባሳለፍነው **<u>እነዚህ አገራችን ላይ ያሉ መንዙማ እና ነሺዳ እየተባሉ ቁርኣንን አዘናግተው የሚዘመሩ መዝሙሮች ምን ያህል ሙስሊሙን ከባድ አደጋ ውስጥ እንደከተቱት አይተናል</u>**።

ይህን ኪታብ አጠር ብሎ እንዲዘጋጅ ስለፈለግኩ በጣም ብዙ የሚባሉ ስንኞችን ትቻቸዋለሁ። ምክንያቱም እነዚህ እራሱ ከበቂ በላይ ናቸውና። አገራችን ላይ እነዚህን አጥፊ እና ሃይማኖት አፍራሽ የሆኑ መንዙማ እና ነሺዳ ባዮች ለማህበረሰባችን እያስተዋወቁ ያሉ ተቋማትም ይሁን ግለ ሰቦች አላህን ፈርተው ለሰዎች መበላሸት ሰበብ ከመሆን ሊመለሱ ይገባቸዋል። ዐሊሞች፣ ዱዓቶች፣ የዲናችን ጉዳይ ያገባናል የምትሉ

ሁሉ እባካችሁን ሃላፊነታችንን በአግባቡ እንወጣ። በነዚህ የፈጠራ መንገዶች “ኢስላምን እናስተምራለን” ብላችሁ የተነሳችሁ ወገኖች ደግሞ እባካችሁን ሸሪአዊ መሰረት ባላቸው የማስተማሪያ ስልቶች ላይ ተገደቡ። ከጥፋት ሃይሎች ጋር አትመሳሰሉ።

የአላህ ባሪያዎች ሆይ! ሁላችንም ሀላፍትናችንን እንወጣ። ቤታችን፣ ሱቃችን፣ ምግብ ቤት እና ካፌ ውስጥ እነዚህን መንዙማ እና ነሺዳዎች አንክፈት። ለኢስላም ውለታ እየዋልን መስሎን ኢስላምን የሚያፈርስ ተግባር እየሰራን እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል።

የእውቀት ባለቤቶች ሆይ! አላህን ፍሩ ህዝቡን ወደ ተውሒድ እና ሱና ተጣሩ፣ ከሺርክ፣ ከቢድዓ፣ እንዲሁም ከመተላለፊያ መንገዶቻቸው ሁሉ አስጠንቅቁ። አላህ በተውሒድና በሱና ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘን በህብረት የምንጓዝ ያድርገን።

﴿ رَبَّنَا تَقَبَّلۡ مِنَّآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ١٢٧ ﴾ البقرة: ١٢٧.

“ጌታችን ሆይ! ከእኛ ተቀበል። አንተ ሰሚውና ዐዋቂው አንተ ነህና።”

ነፍሴንም እናንተንም እስከ ህይወት ፍፃሜ ድረስ አደራ በተውሒድ፣ አደራ በሱና፣ አደራ የመልካም ቀደምቶቻችንን መንገድ አጥበቆ በመያዝ እላለሁ። **<u>አላህ ሆይ! መጨረሻችን አሳምርልን።</u>**

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላትና ሰላም በነብያት ሁሉ መደምደሚያ በሙሐመድ፣ በቤተሰባቸው፣ በባልደረባዎቻው እና ሃቅን በተከተለ ላይ ሁሉ ይሁን።

ተጠናቀቀ።